# የሥነ - ጥበባት ትምህርት
# የተማሪው መጽሐፍ
# 8ኛ ክፍል


## አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች

ደነደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

## አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች

ዳሜ ቶሊና

ሉባባ ጀማል

ታደሰ ድንቁ

## አፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች

ደቀቦ ጉዬ

ድርባ ማሞ

እስማኤል ሀሳን

## ተርጓሚዎች

ደቀቦ ጉዬ

ሙሉቀን አብራሀም

እስማኤል ሀሳን

ድርባ ማሞ

## የጥራት ቁጥጥር

ደቀቦ ጉዬ

## ግራፊክስ

ታደሴ ድንቁ



© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022



ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡



የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምዕራፍ 1 የስነ-ጥበባት ግንዛቤዎች ..........1
1.1 የቅርፃ ቅርፅ አሳባውያን ድርሻ እና ጥቅሞች..........2
1.2የኢትዮጵያሙዚቃአይነቶች፣የሙዚቃመሳሪያዎችቅኝትናውዝዋዜ..........12
1.1.3. የትያትር እና የፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አሳባውያን ..........15
ምዕራፍ 2 የፈጠራ ችሎታ ..........37
2.1. ሶልፌጅዮን በኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት (በአንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰል)..........38
2.2ባህላዊውዝዋዜ..........47
2.3 የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን)..........51
2.4 የህትመት እና ቅርፃ ቅርፅ ስራ (የሸክላ አፈር፣ፔፐር ማሼ) ..........58
ምዕራፍ 3 የስነ-ጥበባት ባህልና ታሪክ ..........84
3.1 የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያዎችና ውዝዋዜ..........85
3.2. የቅርፃ ቅርፅ (ሃዉልት) እና የጥንት ዘመን የእጅ ሙያ ታሪክ..........88
3.3 በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም ጥበብ መልክ ማቅረብ..........93
ምዕራፍ 4 የስነ-ጥበብ መስህብነት ..........98
4.1. የስነ-ጥበባት ስራዎችን በተግባር የማስተማር ጥቅሞች..........99
4.2. በተግባር የምታዩ ስነ-ጥበባትን ማነጻጸር (ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትር እና የፊልም ስነ-ጥበብ)..........99
4.3 የሃዉልትእና የእጅ ስራ ሙያ ምልክቶች መልዕክት ..........102
ምዕራፍ 5 የስነ-ጥበብት ትስስር ..........112
5.1 የስነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉዳይ ጋር..........112

# ምዕራፍ 1
# የስነ-ጥበባት ግንዛቤዎች

## የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤቶች:

ከዚህ ትምህርት በኋላ:

- የቅርፃ ቅርፅ ምንነት እና ትርጉም ትገልፃላችሁ ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ አሳባውያንን በመለየት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራባቸው ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ስለ ኢትዮጵያ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ቅኝትና ውዝዋዜ ታብራራላችሁ፡፡
- የትያትርና ፊልም ጥበብ ፕሮደክሽን ሂደት ትግልፃላችሁ፡፡
- አጭር የፈጠራታሪክ ለትያትርና ፊልም ጥበብ ትፅፋላችሁ፡፡

### መግቢያ

የቅርፃ ቅርፅ ሥራ የስነ-ጥበብ ስራዎች ከሚሠሩባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡ እንደ አሁኑ ጊዜ በስልጣኔ ዕድገት ምክንያት የቴክኖሎጂ ውጤት ከመስፋፋታቸው በፊት የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ኑሮውን ለመምራትና ለመሻሻል በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተለያዩ ነገሮችን በመስራት ይገለገልበት ነበር፡፡ የቅርፃ ቅርፅ ጥበብ እድገትም ከዚሁ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

በሰበተኛ ክፍል የስነ-ጥበብ ትምህርት ውስጥ ስለ ሙዚቃ ባህሪያትና ባህላዊ ውዝዋዜ፣ ስለ ሶልፌጅዮና የሃገራችን የሙዚቃ ቅኝት፣ ስለ ኦሮሞ ሙዚቃ ታሪክ፣ ስለ ሃገራችን አንጋፋ ሙዚቃዎችና ተወዛዋዦች፣ እንዲሁም ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችና በሙዚቃና በሌሎች የትምህርት መስኮች ያለውን መስተጋብር ተምረቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል ትምህርት ውስጥ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ሶልፌጅዮ፣ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝትና የሙዚቃ ባህላዊ አቅጣጫ ምን እንደሆነ ትማራላችሁ፡፡ ባለፈው ትምህርት ውስጥ ስለ ትያትር፣ የትያትር አጀማመርና ዕድገት እንዲሁም ትያትርና ድራማ ያላቸውን ልዩነት ተረድታችሁ ነበር፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ የስነ-ትያትርና የስነ-ፊልም ፕሮደክሽ ሂደቶችን ትማራላችሁ፡፡

## 1.1 የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ድርሻ እና ጥቅሞች

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ :

- ቅርፃ ቅርፅ ምን እንደሆነ ታብራራላችሁ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ ባህርያትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንና ያላቸውን ጥቅም ትገልፃላችሁ፡፡

### 1.1.1. የቅርፃ ቅርፅ ትርጉምና ባህሪያት

**ተግባር 1**

የሸክላ አፈር ወይም ካርቶን እና የመሳሰሉትን በመጠቀም የሰው፣ የእንስሳት፣ የመኪና፣ የቤት እና የሌሎች ነገሮችን ቅርፅ ወይም መስል ሰርታችሁ ታውቃላችሁ? ሰርታችሁ ከሆነ የሠራችሁትን ቅርፅ (ምስል) በምን ዘዴ እንደሠራችሁ በቡድን በመወያየት ለመምህራችሁና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የቅርፃ ቅርፅ ስራ የስነ-ጥበብ ስራዎች ከሚሰሩባቸው ዘዴዎች አንዱ ሆኖ፤ የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ዕለት ተዕለት የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች ለመስራት፣ አካባቢውን ለማስዋብ፣ ሚፈልገውን መልዕክት ለማስተላለፍና ለመሳሳሉት ምክንያቶች ከአከባቢ ማግኘት የሚችላቸዉን ቀላል የሆኑ ነገሮችን በመጠቀም የተለያዩ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን ሲሰራ ነበር፡፡

ይህም የሰው ልጅ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እንደ አሁኑ ስልጣኔ ሳይስፋፋና የተለያዩ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ሰርቶ መጠቀም ከመጀመሩ በፊት፤ በአከባቢ የሚገኙ ቀላል የሆኑ ነገሮችን በመቅርፅ እና በመጥረብ ስጠቀምበት ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ድንጋይ፣ የእንስሳት አጥንት፣ የእንስሳት ቀንድ፣እንጨት እና የመሳሰሉትን ቀርፀዉ (ቅርጽ በማዉጣት) እንደ ጦር፣ ብለዋ፣ የመመገቢያ ዕቃዎች፣ የማጌጫ ዕቃዎችና የመሳሳሉትን ሠርተው ይጠቀሙበት ነበር፡፡

በአጭሩ የቅርፃ ቅርፅ ታሪክ እና አመጣጥንስንመለከት ረጅም ዕድሜ ያለውና እና ጣሪካዊ አመጣጡ ከሰው ልጅ ሂደታዊ ለውጥ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሰዎች ሃሳብን፣ስሜትን፣ምኞትን፣ታሪ ክን፣ባህልን፣እሴትን፣ሃይማኖታዊ መልዕክትን፣ሃዘንን፣ደስታን እና የመሳሰሉትን ለመግለፅ ቅርፃ ቅርፅን ሲጠቀሙበት እንደኖሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም በሰው ልጅ እና የቅርፃ ቅርፅ አመጣጥ መሀል ጠንካራ ትስስር መኖሩን ያሳያል፡፡

እንደ አንድ የጥበብ ሥራ ቅርፃ ቅርፅ የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ በስፋት መታወቅ የጀመረና ስለ ፅንሰ-ሃሳቡ ግልጽና ሰፊ ትርጉም (ማብራሪያ) መሰጠት የተጀመረው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የሰጥ የነበረው ትርጉም ከቴክኖሎጆ ዕድገት ጋር የተያያዙ አዳዲስ መሳሪያዎችና ቅርፃ ቅርፅ የሚሰሩባቸው የተለያዩ የአሰራር ዘዴዎችን/ሂደቶችን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ስለ ቅርፃ ቅርጽ የሚሰጣውን ሃሳብ አነስተኛና ውስን እንዲሆን አድርጎታል፡

፡ ስለ ቅርፃ ቅርፅ በስፋት መግለፅ የተጀመረው ፅንሰ-ሃሳቡን ከመሠረታዊ ትርጉሙና ከአሰራር ዘዴዎች ጋር በመያያዝ ሃሳብ መሰጠት ከተጀመረ ወዲህ ነው፡፡ እንደሚታወቃው በጥንት ዘመን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሳይስፋፋ የቅርፃ ቅርፅ ሥራዎች ቀላል በሆኑ ነገሮች እና በቀላል መንገድ ሲሰሩ ነበር፡፡ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን አብዛኛዉ ጊዜ በልምድ ወይም በመለማመድ የሰሩት ነው እንጂ፣ ስለ ቅርፃ ቅርፅ ምንነት እና የሚሰራበት የአሰራር ዘዴዉን በደንብ አጥንተዉ ሲሰሩ አልነበሩም፡፡ ሰዎች እስከ 20ኛዉ ክፍለ ዘመን ደረስ በባህላዊ ወይም በልምድ ለቅርፃ ቅርፅ ሲሰጡ የነበሩ ትርጉም እና ማብራሪያ በአራት (4) ይከፈላል እነርሱም፡-

1ኛቅርፃ ቅርፅ ከስነ-ጥበብ ስራዎች አንዱ ሆኖ፣ ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ብቻ ያለው ነው፡፡

2ኛ ምስል ወይም የተፈጥሮ ምልክት ነው፡፡ ነገር ግን የቅርፃ ቅርፅ ስራዎች ሁሉም ሙሉ በሙሉ የተፈጥሮ ነገሮች ተወካይ (ምስል የሆነ ነገር) ብቻ ሳይሆኑ የተፈጥሮ ምስል ያልሆኑትም ልሆኑ ይችላሉ፡፡ ምልክትስንል በቀላሉ ልንረዳ የሚንችል ማለት ነው፡፡

ስዕል ያልሆነ ደግሞ አንድ ነገር በተፈጥሮ ያለዉን አካል ሙሉ በሙሉ ወይም በጭራሽ የማያሳይ፣የሚያስተላልፈዉ መልዕክት በቀላሉ መረዳት የማይቻል ነው፡፡

3ኛቅርፃ ቅርፅ እንደ አንድ የስነ ጥበብ ዘርፍ ጠጣር ሆኖ የሚታይ ነው፡፡

ቅርፃ ቅርፅ ጠጣር የሆነ አካል ያለዉ ነው ሲባል፣ በሚሰራ ነገር መሃከል ለሚታይ ባዶ ቦታ ወይም በሚሰራ ነገር አከባቢ ለሚቀር ቦታ ትኩረት አይሰጥም ማለት ነው፡፡ስለዚህ በሚሰራ ነገር መሃከል የሚታይ ባዶ ቦታ ወይም በሚሰራ ነገር አካባቢ የሚቀር ቦታ እንደማይጠቅም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ይህ ደግሞ የሚሰራው ነገር አካላዊ እንቅስቃሴ አያሳይም ማለት ነው፡፡ በቅርፃ ቅርፅ ስራ ደግሞ እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ እና አስፈላጊ ነው፡፡ የሚሰራ ነገር እንቅስቃሴ ከለሌዉ፣ መስዕቡ/የዉበት መጠኑ አናሳ ይሆናል፡፡

4ኛ የቅርፃ ቅርፅ ስራ የሚሰሩ ሰዎች በሁለት ዘዴ ብቻ የሚጠቀሙ ሲሆን እነሱም መላግ እና መጥረብ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በጥንት ዘመን ሰዎች ለቅርፃ ቅርፅ ስራ በብዛት ሲጠቀሙባቸው የነበሩት መጠረብ የሚችሉ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህም እንጨት፣ ድንጋይ፣ የእንስሳት አጥንትና የመሳሳሉት ሲሆኑ በሸክለ አፈርም ይጠቀሙ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ስለ ቅርፃ ቅርጽ ስራ የአሠራር ሂደትና ዘዴ ላይ በመመስረት ቅርፃ ቅርፆች የሚሰሩባቸው መንገዶች በአራት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

ሀ. መላግ እና መጥረብ
ለ. መበየድ እና ማቅለጥ
ሐ. መቅረፅ እና
መ.ማምረት/casting ናቸው፡፡

## ሀ. መላግ እና መጥረብ

### ተግባር 2

በአከባቢችሁ ሰዎች እንጨትበመጥረብና በመላግ ቀንበር፣ሙቀጫ፣ወንበር እና የመሳሰሉትን ስጠርቡ አይታችሁ ታውቃላችሁ? አይታችሁ ከሆነ እንጨት በመጥረብና በመላግ ከነዚህ ከተጠቀሱት ነገሮች አንዱን ወይም ሌላ ነገር እንዴት እንደሚሠሩ ለክፍል ተማሪዎች ግለፁ፡፡

የመጥረብ/የመላግ ሙያ ቅርፃ ቅርፅ ከሚሰሩባቸው መንገዶች አንዱ ሆኖ ይህም መጠረብ ወይም መላግ የሚችሉ ነገሮችን በመጠቀም የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች መስራትን ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ፣ ድንጋይ፣ እንጨት፣ የዝሆን ጥርስ፣ አጥንትና የመሳሳሉትን በመጥረብ ወይም በመላግ ቅርፃ ቅርፆች መስራትን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ሂደትም ሰዎች የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀምና እነዚህን ነገሮች በመጥረብ ወይም በመላግ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን ይሠራሉ፡፡



ስዕል 1.1.የመጥረብ/ የመላግ ሙያ ተሰረ ቅርጻ ቅርፅ

## ለ. መበየድ/ማቅለጥ

የማቅለጥ ጥበብ ሙያ በ20ኛ ክፍለ ዘመን ከሚሰሩትአዲስ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን፤ በቀላሉ ከአከባቢያችን ማግኘት የሚንችላቸዉ የተለያዩ ነገሮችን በማቅለጥ/በመበየድ እና በማያያዝ የተፈለገውን ቅርፃ ቅርፅ ለመስራት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የዛገ ብረት መጠቀም ይቻላል፡፡



ስዕል 1. 2. በማቅለጥ/በመበየድ ሙያ የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ

## ሐ. መቅረፅ

መቅረፅ ቅርፃ ቅርፅ ለመስራት የሚያስችል ሌላ ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ለስላሳ ወይም በቀላሉ መቀረፅ የሚችሉ ነገሮችን በመጠቀም ቅርፃ ቅርፆችን መስራት ወይም የአንድ ነገር ፎርም ማውጣት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- የሸክላ አፈር፣ ሰም እና የመሳሰሉት ነገሮችበመጠቀም ቅርፃ ቅርፅ መስራት ይቻላል፡፡



ሥዕል1.3. ከሸክላ አፈር በመቅረፅ የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ የሚያሳይ ሥዕል


## መ. ማምረት/casting

ቅርፃ ቅርፅን በማምረት ሙያ መስራት በ20ኛ ክፍለ ዘመን በስፋት መሰራት የጀመረ ስራ ነው፡፡ ይህም ተሰርቶበተዘጋጀዉ ቅርፃ ቅርፅላይ ፈሳሽ ነገሮችን በማፍሰስ/በመጨመር የሚሰራ ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ - የቀለጠ ብረት፣ ፕላስትክ፣ ሲሚንቶ፣ ጄሶ እና የመሳሰሉትን በመጨመር ይሰራል፡፡

ይህ ዘዴ ከሸክላ አፈር ወይም ከሰም የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ ወደ ብረት ወይም ሲሚንቶ የሚቀየርበት ሂደት ነው፡፡



ሥዕል 1.4ሀ. በማምረት ጥበብ የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ



ሥዕል 1.4ለ. በማምረት ጥበብ የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ



ሥዕል 1.4ሐ . በማምረት ጥበብ የተሰራ ቅርፃ ቅርፅ

በአጠቃላይ ከላ የተገለፁት ቅርፃ ቅርፅን መስራት የሚያስችሉ ዘዴዎች የተለያዩ የአሰራር ሂደቶችን በመከተል ቅርፃ ቅርፅን ከተለያዩ ነገሮች (ግብዓቶች) ለመስራት ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡

አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን ለቅርፃ ቅርፅ የሚሰጥ ትርጉም ከ20ኛ ክፍለ ዘመን ጋር ሲነፃፃር በተወሰነ ደረጃ ልዩነት አለው፡፡ ይህም ቅርፃ ቅርፅማለት“Sculptura”ከሚል ከላቲን ቃልየመጣ ሲሆን ትርጉሙም፡-

- በማጉበጥ/መጠምዘዝ
- በማቆራረጥ እና
- በመላግ/መጥረብ አንድን ነገር መስራት ማለት ነው፡፡

ቅርፃ ቅርፅ በጥበብ ስራ ከሚሰሩ ስራዎች አንዱ ሲሆን፤ በስነ-ጥበብ(fine arts) ስር የሚመደብ ነው፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ቁመት፤ወርድ እና ርዝመት ያለዉ የጥበብ ስራ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በጥበብ ስራዎች ከሚሰሩከሌሎች ጠፍጣፋ ከሆኑ ስራዎች/ነገሮችማለትም እንደ ቀለም ቅብ፣ ንድፍ፣ ህትመት እና ከመሳሰሉትን ለመለየት ያገለግለናል፡፡

ቅርፃ ቅርፅ ቁመት፣ ወርድና ርዝመት ያለው በመሆኑ የሚያዝ እና በሁሉም አቅጣጫ በመዞር መመልከት የሚቻል ጠጣር ነገር ነው፡፡

ስለዚህ ቅርፃ ቅርፅ እንደ ቀለም ቅብ ወይም ንድፍ የሚታይ ብቻ ሳይሆን ጠፍጣፋ በሆነ ነገር ማየት የማንችለዉን አቅጣጫ ማሳየት ያስችላል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ተጨባጭ እና የሚታይ ፎርም ነው፡፡ ስለሆነም በተፈጥሮ ማየት የተሳናቸው ሰዎች እንኳን በተወሰነ ደረጃ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ማድነቅም ሆነ፣መለየት እና መስራት ይችላሉ.

## 1.1.2. የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን

### ዉይይት 1

የቅርፃ ቅርፅ አላባዉያንማለት ምን ማለት ነው? የቅርፃ ቅርፅ አላባዉያን የሚባሉት ምንምን እንደ ሆኑ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

በጥቅሉ ሲታይ የሥነ-ጥበብ አላባዉያን ለአንድ ጥበብ ስራ መፈጠር ምክንያት እንደሚሆኑ ሁሉ፤ የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንም ለቅርፃ ቅርፅ ወይም ፎርም መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ አንድን ቤት ለመስራት ድንጋይ፣ ጭቃ፣እንጨት፣ብረት፣ሲሚንቶ፣አሸዋ፣ቆርቆሮ ወይም ሳር እና የመሳሰሉት አስፈላጊ እና ወሳኝ እንደሆኑና ከነዚህ ነገሮች ዉጪ ቤት መስራት እንደማይቻልይታወቃል፡፡ እንደዚሁ ከቅርፃ ቅርፅ አላባዉያን በስተቀር የቅርፃ ቅርፅ ስራ ወይም ፎርም መስራ አይታሰብም፡፡ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎች የሆኑት ለቤተ-እምነት፣ ለመስዕብ፣ለመታሰቢያ፣ገቢ ለማስገኘት፣ታሪክን ለመግለፅ እና ለመሳሰሉት የተሰሩ ነገሮች ሁሉ የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን ዉጤት ናቸው፡፡ የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:-

- ቦታ
- ይዘት/ መጠን
- መስመር
- ገፅታ/የገፅ አካል
- ቅርፅ
- የቀለም ንጣት እና መደብዘዝ/ value/
- ሸካራነት እና ለስላሳማነት
- ቀለም ናቸው፡፡.


ከነዚህ ከላይ ከተዘረዘሩት የቅርፃ ቅርፅ አላባውያንውስጥ መሰረታዊ የሆኑት ቦታ እና መጠን/ ይዘት ናቸው፡፡እነዚህ የቅርፃ ቅርፅ አላባውያን እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡፡

### 1. ይዘት/መጠን

የቅርፃ ቅርፅ አካል እና በገፅ የታቀፉ ጠጣር ነገሮችን ያሳያል፡፡ ማንኛዉም የቅርፃ ቅርፅ መጠን ያላቸዉ እና በእጅ ከሚዳሰሱ ማነገሮች የሚሰራ ነው፡፡ ዙሪያ ድንበር ያለዉ፣ እራሱን ችሎ የሚቆም እና ሙሉ በሙሉ በቦታ የተከበበ ነው፡፡

### 2. ቦታ

ቦታ ማለት በቅርፃ ቅርፅ መሃል ወይም በዙሪያ የሚገኝ እና የቅርፃ ቅርፅ ዳር/ጠርዝ የሚገልፅ ነው፡፡ እንዲሁም በቅርፃ ቅርፅ የሚታቀፍ እና ክፍት ቦታ የሚፈጥር ማለት ነው፡፡



ሥዕል 1.5፡ ቦታን የሚያሣይ ሥዕል

## 3. መስመር

በቅርፃ ቅርፅ ስራ ውስጥ መስመር ማለት፣ የፎርም እና የሚነካካ ገፅ አካል ዳር/ጠርዝ ነው፡፡ በንድፍ ውስጥ መስመር በእርሳስ፣ ከሰል እና በመሳሰሉት ይሰራል፡፡ በቀለም ቅብ ደግሞ እርሳስ ወይም ብሩሽ በመጠቀም መስራት ይቻላል፡፡እንዲሁም .በቅርፃ ቅርፅ ውስጥ በቀጫጭን ነገሮች ለምሳሌ፡- ሽቦ፣እንጨት፣ክር/ገመድ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም መስራት ይቻላል፡፡.



ስዕል 1.6፡ በሽቦ የተሰራ ቅርጻ ቅርጽ

## 4.ገፅታ/የገፅ አካል

በቅርፃ ቅርፅ ስራ ውስጥ የገፅ አካል ሲባል፣ እኩል የሆነ ገፅ ማለት ነው፡፡ ይህም የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን ውስጥ በደንብ ተጠንተዉ እና ለስለስ ተደርገው እንዲሰሩ የሚያስችል ነው፡፡

## 5. ቅርፅ

የተለያዩ ቅርፆችሲቀናጁ ፎርም ይፈጥራሉ፡፡ የፎርም ቅንጅት ደግሞ ቅርፃ ቅርፅ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በቅርፃቅርፅ ስራ ውስጥ ቅርፅ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነርሱም አወንታዊ ቅርፅ እና አሉታዊ ቅርፅናቸው፡፡

## ሀ. አወንታዊ ቅርፅ

በአጠቃላይ በሚሰራ ቅርፃ ቅርፅ መሀከል የሚገኝ መጠን ነው፡፡በሌላ በኩል በአንድ ነገር የሚያዝ ቦታ ነው ማለት ይቻላል፡፡



ስዕል 1.7.ሀ . አዉንታዊ ቅርፅ

## ለ. አሉታዊ ቅርፅ

በአንድ ነገር ያልተያዘ ባዶ ቦታ የሚገለፅ ወይም ነፃ ሆኖ የሚቀር ቦታ ነው፡፡ በቅርፃቅርፅ ወይም በፎርም ስራ ውስጥ እንደ አሉታዊ ቦታ የሚታይ ቅርፅ፣ ቅርፃቅርፁን በሚያይ ሰው አቋቋም ጋር የሚቀያየር ነው፡፡ ምክንያቱም ቅርፃቅርፅ ወይም ፎርም የቁስአካል ያለዉና ዙሪያዉን ዞረን ማየት የሚንችል ነው፡፡ ቆመን የሚናይበት ቦታ ስንቀይር፣ የሚታይ ቅርፅም በአይናችን እይታ ጋር ይቀያየራል፡፡



ስዕል 1.7ለ. አሉታዊ ቅርፅ

## 6. የቀለም ንጣት እና መደብዘዝ/ቫሊዩ/

ይህ ማለት የአንድን ነገር ንጣት እና መደብዘዝ የሚያሣይ ነው፡፡ በቅርፃቅርፅ ቫሊዩ የብርሃን መጠን ወይም የፎርም ገፅ ጥላ እና በሚፀባረቅ ብርሀን መጠን ነው፡፡ የቅርፃቅርፅ ወይም የፎርም ገፅ ቫሊዩ የተቀባ ቀለም ሲቀየር መቀየር ይችላል፡፡.

## 7. ሸካራነት እና ለስላሳማነት

ሸካራነት እና ለስላሳማነት ማለት የአንድን ቅርፃቅርፅ አካል መለስለስ እና መጠንከር ወይም የቅርፃቅርፅ ገፅ ንፃትነው፡፡ ንፃት፣ለስላሳማነት፣ቀለም እና የመሳሰሉት በአንድየቅርፃቅርፅ ስራ

ውስጥ በፀሃይ፣ዝናብ፣የአየር ሁኔታ መቀያየር ተፅዕኖ ሊቀያየሩ ይችላሉ፡፡.

በስነ-ጥበብ ሸካራነት እና ለስላሳማነት የሚታየዉን የገፅታ ጥራት የሚገለፅ የጥበብ ስራ ሲሆን በአካል በመዳሰስ ወይም በእይታ እንዲሁም በሁለቱም ሊታወቅ ይችልል፡፡ ለምሳል፡- በመስመር፣ በመፋቅ፣በማጎድጎድ እና በማለስለስ ከሚሰሩ የጥበብ አለባዉያን አንዱ ነው፡፡



ስዕል 1.8.ሸካራነት እና ለስላሳማነት የሚያሳይ ሥዕል፡፡

### 8. ቀለም

ቅርፃቅርፅ የሚሰራባቸዉ ነገሮች የተፈጥሮ የራሳቸዉ ቀለም አላቸዉ፡፡ ቅርፃቅርፅ ስንሰራ በትክክል ነገሩ የሚሠራበትን ቀለም ብንጠቀም መልካም ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የአባ ገዳ ቅርፃቅርፅ ቅርፃቅርፅ የምንሠራ፤ ባህላዊ ልብስ፣ ትጥቅ እና አባ ገዳ የሚይዛቸዉ ነገሮችን ሁሉ አስመስለን ከሰራን ቦኋለ፤ ያ የባህል ልብስ ያለዉን ቀለም አቀባብ ተከትለን እሳቸዉ የሚይዙአቸውን ነገሮች ሁሉ እንደየቀለማቸዉ ከቀባን የስራችንን ጥራት ልቀንስ ይችላል፡፡ ስለዚህ በተለያዩ ነገሮች ተጠቅመን ቅርፃቅርፅ ስንሰራ፤ ቀለም መቀባት አስፈላጊ አይደለም፡፡ቀለም መቀባት አስፈላጊ ሆነው ከተገኘ ተመሳሳይ የሆነውን ቀለም መቀባት አለብን እንጂ እንደ ቀለም ቅብ የተለያዩ ቀለማትን ተጠቅመን የቅርፃቅርፅ ስራዎችን ለማሳመር መሞከር አስፈላጊ አይደለም፡፡

## 1.1.3. ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራባቸዉ ነገሮች

**ተግባር 3**

በአካባቢያችሁ ተሠርተው የሚገኙ የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆች አሉ?ካሉ እነዚህ ቅርፃ ቅርፆች ከምን ከምን እንደተሠሩ በቡድን ተወያዩና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ያላቸዉ ነገሮች ሆነው፤ በሁሉም አቅጣጫ መታየት የሚችሉ ነገሮች ሁሉም የቅርፃቅርፅስራዎችን ለመስራት ያገለግሉናል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ቅርፃቅርፅ የሚሰራባቸዉ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- ድንጋይ
- ብረት
- ብር
- ወርቅ

- ነሃስ
- ሸክላ አፈር
- ሰም
- እንጨት
- ፕላስትክ
- ወረቀት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ልምምድ 1

በዚህ ምዕራፍ ከቀረባው ትምህርት ስለ ቅርፃቅርፅ ትርጉም እና ምንነት፣ ባህሪያት፣ አለባውያን እንዲሁም ቅርፃቅርፅ ስለሚሰራባቸዉ ነገሮች ተምረቸዋል፡፡ በአከባቢያችሁ ማግኘት የሚትችሉትንና ቅርፃቅርፅ ሚሰራባቸዉ ነገሮችን በመጠቀም መኪና፣ቤት፣ሰው፣እንስሳት እና የመሳሰሉትን በግላችሁ ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ ከአቀረባችሁ በኋላ የስራችሁን ጠንካራ እና ደካማ ጎን ከመምህራችሁ እና ከክፍል ተማሪዎች ጋር በመወያየት ማስተካከያ ሃሳብ ተቀበሉ፡፡ የምትቀበሉት የማስተካከያ ሃሳብ ለሚቀጥለዉ ስራ እንደ ግብዓት ያገላግላቸዋል፡፡

## 1.2 . የኢትዮጵያ ሙዚቃ አይነቶች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቅኝትና ውዝዋዜ

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ :

- የሀገራችንን የሙዚቃ ዓይነቶችትዘረዝራላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ቅኝት ትለያላችሁ፡፡

የግንዛቤ ጥያቄ

አንድን ዘፈን ለመስራት ወይም ለማቀናጀት ዋና እና አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

### 1.2.1 ትላልቅ የኢትዮጵያ ሙዚቃ ዓይነቶች

**ተግባር 4**

በሀገራችን የሚታወቁ የሙዚቃ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ በቡድን በመወያየት ከለያችሁ በኋለ መልሳችሁን ለመምህራችሁና ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

የኢትዮጵያ ሙዚቃ ለብዙ ዓመታት የህዝቦችን ባህልና ወግ ይዞ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ መሆኑን ከታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨባጭ ሁኔታ የት እና እንዴት እንደተጀመረ በፅሑፍ መልክ ባይኖርም በኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃን ለተለያዩ ጉዳይ ይጠቀሙ እንደነበር በዚህ መስክ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ በዘመቻ ጊዜ እርስ በረሳቸው ለማበረታታት፣ ያላቸዉን የፍቅር ቅርበትና ስሜት ለመግለጽ፣ ለአምልኮ ስርዓት፣ጭቆናና ሀዘንን ለመግለጽ፣ እንዲሁም የህብረተሰቡን ባህልና ታሪክ ለማሳደግና ለመዘከር ሙዚቃን ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ አሁን በዘመናዊ መልክ በመቀጠል ስራ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅል ሃሳብ እንደ መነሻ በመውሰድ በኢትዮጵያ በብዛት የሚታወቁ የሙዚቃ አይነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የገዳ ዘፈን : የገዳ ዘፈን የገዳ ስርዓት በሚፈጸምበትና በሚከበርበት ጊዜ ቅደም ተከተል ባለዉ ስርዓት ሁኔታዉን ጠብቆ የሚዘፈን ነው፡፡
2. የአቴቴ ዘፈን: ይህ ዘፈን ድርቅ በሚረዝምበት ጊዜ፣አቴቴ በሚዘፍበት ጊዜ፣አራስ ሴት በምትመታበት ወይም በምትገረፍበት እና በመሳሳሉት ጊዜ የሚቀርብ ነው፡፡
3. ማህበራዊ ዘፈን: ይህ ዘፈን አንድ ማህረበረሰብ ማህበራዊ የሆኑ ሁኔታዎችን በሚያካሄድበት ጊዜ የሚዘፈን ነው፡፡ይህም ለሰርግ ፣ ለልደት ፣በበዓላት ፣ በዘን እና በመሳሰሉት ጊዜ የሚቀርብ ነው፡፡
4. የስራ ዘፈን: ይህ ሰዎች በስራ ላይ በሚረዳዱበት ጊዜ የሚቀርብ ዘፈን ነው፡፡

ለምሳሌ፤

- እህል ሲያጭዱ
- ቤት በሚሠሩበት ጌዜ
- ቡና በሚለቀምበት፣ ሴቶች ተሰብስበው እህል በሚወቅጡበት ጊዜና ሰዎች በጋራ በመሆን የተለያዩ ስራዎችን አብረዉ በሚሰሩበት እና በሚፈጽሙበት ጊዜ የሚዘፈን ነው፡፡

5. የፖለቲካ ዘፈን፡ይህ ዘፈን ሰዎች ፖለቲካንለመቀስቀስ ለመደገፍ ወይም ለመቃወም የሚጠቀሙበት ነው፡፡
6. ዜማ: የተለያዩ የዜማ ዓይነቶች ብኖሩትም አብዛኛዉን ጊዜ በቤተ-ዕምነቶች ውስጥ፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለትምህርት ጉዳይ ፣ስለ ሀገር ለማዜም፣ከብቶችን ሲጠብቁ እና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚጠቀሙበት ነው፡፡
7. ጌረርሳ/ቀረርቶ: ጌረርሳ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በአብዛኛዉ የሚታወቅና ለየት ባለ መልክ የሚጫወቱት ነው፡፡ጌረርሳ የአንድን ሰው ጀግንነት ወይም ብርታትን ለመግለጽ የሚጫወቱት ነው፡፡ እንደ ኦሮሞ ባህል ጌረርሳ የሚዜመዉ /የሚቀርበው አዋቂ በሆኑ ሰዎች ሲሆን እሱም ከአንድ ምክንያት ጋር በማያያዝ ይዜማል፡፡ ጌረርሳ አብዛኛዉን ጊዜ የሚዜመዉ በጦር ግንባር ተዋጊዎችን ለማበረታታት፣ የራሳቸዉን ጀግንነት ለመግለጽ፣ የራሳቸዉን ጎሳ (ዘር)ለማወደስ ወይም ለመግለጽና ለመሳሰሉት ነው፡፡

8. ዘመናዊ ዘፈኖች:ዘመናዊ ዘፈኖች በዘመናዊ መልክ ለተለዩ ጉዳዮች ለምሳሌ ለንግድ፣ ለመዝናናትና ለመሳሰሉት በሙዚቃ መሳሪያ ተቀነባብረዉ የሚቀርቡ ናቸው፡፡

## 1.2.2. የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ዓይነት

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዓለም ላይ ስራ ላይ መዋል ከጀመሩ ዓመታትን አስቆጥረዋል፡፡ እንዲሁም በሃገራችን ውስጥም ለብዙ ዓመታት ለጥቅም እየዋሉ የነበሩና ያሉ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በቁጥር ብዙ ናቸው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በሀገራችን የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያች በሶስት ትላልቅ ቦታዎች ይካፈላሉ፡፡

እነርሱም፤

ሀ. የምት(በመምታት ድምጽ የሚያወጡ)

ለ. የትንፋሽ (በመንፋት ድምጽ የሚያወጡ)እና

ሐ. የክር(በመገዝገዝ ወይም መምቻን በመጠቀም ድምጽ የሚያወጡ)ናቸው፡፡

ሀ. የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች

የምት ሙዚቃ መሳሪያ የሚባሉት የተለያየ ቅርጽና መጠን ያላቸዉና ለተለያዩ ጉዳዮች በተለያዩ ጊዜያት የሚጠቀሚባቸዉ ናቸው፡፡ ይህ ማለት በበዓላት ፣በሠርግ ፣በአምልኮና ለመሳሰሉት ጊዜያት እንጠቀምባቸኋለን፡፡ እነኚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች ቀጭንና ወፍራም ድምጽን ማዉጣት በሚችሉ መልክ የተሰሩ ናቸው፡፡ከእነዚህ ዉሰጥ ጥቂቶቹን እናያለን፡፡

## 1. ነጋሪት

ነጋሪት ከምት ሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡ይህ የሙዚቃ መሳሪያ በአብዛኛዉ ከቆዳና ትልቅ እንጨት ውስጡ ተቦሪቦረው ወይም በገበታ መሰል ይሰራል፡፡ የምፈለጋውን ድምፅ እንድኖረው ቆዳውን በመወጠሪያ ገመድ ወይም ክር በደምብ መወጠር አለበት፡፡ይህ ነጋሪት የሚመታዉ በእጅ ሳይሆን በመምቻ እንጨት በሚባለዉ አጠር ባሉ ሁለት እንጨቶች ለዚህ መሳሪያ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

ነጋሪት የከበሮ ዓይነት ሆኖ በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው ብቻውን መሸከም አይችልም፡፡ አገልግሎቱም ህዝብን የሚያስተዳድሩ ነገስታት የተለያዩ መልዕክቶችን ለማስተላላፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌ፤ህዝብን ለጦርነት ማዘጋጀት፣ግብርን እንዲከፍሉ ለማሳሰብ፣ስብሰባ እንዲመጡ ለማሳወቅ ከፈለጉ ትልቁ ነጋሪትን በአህያ ላይ በማስጫን እየመቱ የፈለጉትን መልዕክት ለማሰተላለፍ ይጠቀሙበት ነበር፡፡



ስዕል 1.9 ሀ፡ የነጋሪት ምስል

## 2. ከበሮ

ከበሮ በሀገራችን ከሚገኙ የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱና ዋናኛዉ ነው፡፡ በሀገራችን የተለያዩ የከበሮ ዓይነቶች አሉ፡፡እነርሱም ነጋሪት፣አታሞ እና የመሳሰሉት በመባል ይታወቃሉ፡፡. የሚሰሩትም ከቆዳና እንጨት፣ ቆዳና ብረት፣ ቆዳና ሸክላ እና ከመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡

ከበሮ ባህልዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሆኖ ከነጋሪት ጋር ቅርበት ያለዉ ነው፡፡ይሁን እንጂ ከበሮ በመጠን ከነጋሪት ያነሰ ስለሆነ ከፍየል ቆዳና ከትንሽ ገበታ የሚሰራ ነው፡፡ በአብዛኛዉ የሚገለገሉበትም የተለያዩ ዝግጅቶች ላይ እንደ ሠርግ፣ የተለያዩ የእምነት በዓላት ላይ፣ በሁለት ትናንሽ እንጨቶች ወይም በእጅ በመጫወት የተፈለገዉን ሙዚቃ በማጀብ ወይም በማሳመር ነው፡፡



ስዕል 1.9ለ፡ የከበሮ ምስል

### 3. አታሞ

አታሞ ባህላዊ ሙዚቃ በሚጫወትበት ጊዜ በማገልገል ይታወቃል፡፡ አታሞ ትንሽ ስለሆነ በእጅ ወይም በጉያ ስር እየያዙ በመምታት ይጫወታሉ፡፡ አታሞ የሚመታዉ በእጅ ወይም በእንጨት ሲሆን የአመታቱ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡ አጨዋወቱ ከእምነት ጋር የማይያያዝ እና ባህላዊ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎችን ለማሳመር ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፤ ሴት ልጆች በሚጨወቱት የጳጉሜ ዘፈኖች፣ በሠርግ እና  በመሳሰሉት ጊዜ ይጠቀሙበታል፡፡



ስዕል1.9ሐ.፡የአታሞ ስዕል

### 4.ትንሿ ድቤ

ትንሿ ድቤ በወለጋ አከባቢ በሠርግ ዘፈን፣በበዓል ዘፈንና በመሳሰሉት ጊዜ ላይ  ይጠቀሙበታል፡፡ እርሱም ሴቶች በእጃቸዉ በመያዝ እየመቱ ይዘፍናሉ/ይወዛወዛሉ፡፡



ስዕል1.9መ.፡የትንሿ ድቤ ምስል

## 1. ቡንሾ

ቡንሾ ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱሲሆን፣ የከብትቀንድ ውስጡን በመቦርቦር ላዩ ላይ የፍየል ቆዳ በማሰር ከደረቀ በኋላ በትንሽ እንጨት በመምታት ድምጽ የሚያወጣ ነው፡ ፡ በዚህ የሙዚቃ መሣሪያ ብዙ ጊዜ የምጠቀሙበት በአብዛኛዉ የአርሲና የባሌ አከባቢ ሴቶች መሆናቸዉን መረጃዎች የሚገልጹ ሲሆን የሚገለገሉበትም በሠርግና በባዓላት ጊዜ ነው፡፡



ስዕል 1.10፡ሀ የቡንሾ ምስል

## 2. ከበላ

ይህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡ ከበላ በአብዛኛዉ በአንዳንድ አካባቢዎች (ዞኖች) ለምሳሌ፣ አርሲ፣ባሌና ቦረና ውስጥ ይጠቀሙበታል፡፡በአብዛኛን ጊዜ የሚጠቀሙበት ሴቶች ሲሆኑ በሠርግ ጊዜ፣በበዓላት ጊዜ በሹመት ጊዜና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበታል፡፡ ይህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ከእንጨት በመጥረብ የሚሰራ እና እርስ በርሱን በማምታት የሚጫወቱት ነው፡፡



ስዕል 1.11 ፡ የከበላ ምስል



ስዕል1. 11ለ ፡ ከበላን በመጠቀም የሚዘፈንበት ጊዜ የሚያሳ ምስል

## 3. መረካሻ

መረካሻ  በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ቅልን በማድረቅ በውስጡ ትናንሽ ጠጠሮችን ወይም የደረቀ ቆሎ በውስጡ በማስገባት በማንከሻከሽ፣ ከዘፈኑ ወይም ሙዚቃዉ ምት ጋር የሚሄድ ይሆናል፡፡



ስዕል 1.12፡ የመረካሻ ምስል

## ለ. የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች

እነኝህ መሳሪያዎች በአከባቢያችን ረዥም ዓመት ያላቸዉ ናቸው፡፡ የሀገራችን ማህበረሰብ ከድሮ ዘመን ጀምሮ እነኝህን መሣሪያዎች በኑሮዉ ዉጣ ዉረዶች ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ይጠቀምበት ነበረ፡፡

ለምሳሌ፤ በሰርግ ጊዜ፣ በተለያዩ ዋዜማዎች መጠራራት፣ በስብሰባ ጊዜ፣ በሀዘን ጊዜ፣ ከብቶችን በሚጠብቁበት ጊዜ እና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበት ነበረ፡፡አሁንም እየተጠቀሙበት ነው፡፡

ከእነዚህ መሳሪያዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የምከተሉት ናቸው፡፡

## 1. ዋሽንት

ይህ መሳሪያ ከሀገራችን ማህበረሰብ ስራ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአብዛኛዉ ጊዜ የሀገራችን ወጣቶች ከብቶች በሚጠብቁበት ጊዜ፣ እህልን በሚጠብቁበት ጊዜ፣ ማታ ቤተሰብ ስሰበሰብ እርስ በርሳቸዉ በማዝናናት ይጫወታሉ፡፡ የራሳቸዉን ፍቅረኛ ለመሳብና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበታል፡፡ ዋሽንት ከትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ ስሆን በተለምዶ አራት ቀዳዳዎች ያለዉና አሚሰት ድምፆችን የሚያወጣ ነው፡፡

ታዋቂ የሆኑ ቅኝቶችን እንደ ትዝታ፣ ባቲ፣ አንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰልን መጫወት ይቻላል፡፡ በሚናዘጋጅበት ጊዜ ከሸምበቆ፣ ከብረት፣ ከፕላስቲክ እና ከመሳሰሉት ነገር ማዘጋጀት እንችላለን፡፡



ስዕል 1.13፡ ዋሽንትና የአጨዋወቱን ሁኔታ የሚያሳይ ምስል

## 2. ፋጋ

ፋጋ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ ከህዝብ ጋር የነበረ ነው፡፡ ፋጋ በትንፋሽ በመንፋት ድምፅ የሚወጣ ሲሆን በአከባቢያችን ውስጥ ለተለያዩ ነገሮች ይጠቀሙበታል፡፡

ለምሳሌ እህልን በሚጠብቁበት ጊዜ እንስሳትን ለማስፈራራት፣ የዘፈንን ዋዜማ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ለመጠራራት፣እሳትን ለመንፋት እና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበት ነበር፡፡በአሁኑ ጊዜ ከሃገራችን ውስጥ እየጠፉ ካሉት አንዱ ነው፡፡ፋጋ ውስጡ ክፈት ከሆነ እንጨት እንደ ቀርከሃ ከሚባል እንጨትና ከአጋዘን ቀንድ ይሰራል፡፡



ስዕል 1.14፡ የተለያየ ቅርጽ ያለዉ ፋጋ

### 3. ጡሩምባ

ይህ መሳሪያ ከፋጋ በመሻሻል የመጣ ሲሆን በመጀመሪያ የተሰራም ከቅል ነው፡፡በአሁኑ ጊዜ ግን ከብረት ይሰራል፡፡ የሀገራችን ማህበረሰብ በሰርግ፣ በአጨዳ፣ በስብሰባ፣ በሀዘን በለቅሶ ጊዜ መልዕክትን ለማስተሰላለፍ ይጠቀሙበታል፡፡



ስዕል1.15፡ የጡሩምባ ስዕል

### 4. ፊንጌ

ፊንጌ ከባህላዊ ትንፋሽ መሳሪያ አንዱ ሆኖ አንድ ድምጽን በማዉጣት የሚታወቅ ነው፡፡. ፊንጌ የሚሰራዉ ውስጡ ክፍት ከሆነ እንጨት ሆኖ ከስሩ ሰፋ የሚል ነው፡፡ፊንጌ ከከብቶች ቀንድ ወይም ከኮተር ይሰራል፡፡ይህ የሙዚቃ መሳሪያ ልዩ ዝግጅት ባለበት ጊዜ ከነጋሪትና እምቢልታ ጋር ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ፤ የአንድ ሀገር ንጉስ ወይም አንድ ታዋቂ ሰው እየመጣ ያለ መሆኑን ለመግለጽና አቀባበል ለማድረግ ይጠቀሙበታል፡፡





ስዕል 1.16፡ የፊንጌ ምስል

## ተግባር 5

1. የምትና የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል ያለውን ልዩነት በቡድን ሆናችሁ ከተመካከራችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡
2. በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ነገሮች በመጠቀም ዋሽንት፣ ፊንጌ ወይም ጡሩምባ አንዱን ሰርታችሁ በመጫወት አሳዩ፡፡

### ሐ. የክር ሙዚቃ መሳሪያዎች

የክር ሙዚቃ መሳሪያዎች ክራቸዉ በማርገብገብ ድምጽ የሚወጡ ስሆን ክራቸዉን በመገዝገዝ ወይም በመምቻ የምንጫወታቸዉ የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ከእነርሱ ውስጥ በብዛት የሚታወቁት፤

### 1. መስንቆ

ይህ መሳሪያ በብዙ ቦታ ማስንቆ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአንድ ክር አምስትና ከአምስት ድምጽ በላይ ማዉጣት ይችላል፡፡ ማስንቆ ከሀገራችን ባህለዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታዋቂዉና ተወዳጅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ክልሎች ይጠቀሙበታል እነዲሁም በኦሮሚያ ክልል በአንዳንድ ቦታዎች ማስንቆን በመጠቀም የሚጫወቱት በተለምዶ አዝማሪ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ማስንቆ ለመስራት የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች እንጨት፣ ክር/የፈረስ ጭራ፣ ምስማር፣ ቆዳ ወይም ስስ የሆነ እንጨት ነው፡፡



ስዕል1.17፡ የማስንቆንና የማስንቆ አጨዋወትን የሚያሳይ ምስል

## 2. ክራር

ክራር ከሀገራችን ሙዚቃ መሳሪያ  እንደ መስንቆ ታዋቂዉና ተወዳጅ ነው፡፡ክራር

ከአምስት እስከ ስድስት ክር ያለዉ ነው፡፡ በሚንጫወትበት ጊዜ በሁለት መልክ መጫወት እንችላለን፡፡ አንደኛዉ በጣታችን በመደርደር ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ደግሞ መምቻን በመጠቀም በመግረፍ ነው፡፡ ክራር ለመስራት የሚያስፈልጉን ነገሮች እንጨት፣ ጎድጓዳ ሳህን ወይም ትንሽ ገበታ፣ ምስማር፣ ቆዳና ክር ናቸው፡፡



ስዕል 1.18፡ ክራርና የአጨዋወቱ ሁኔታ የሚያሳይ ምስል

### ተግባር 6

1. ክራር የሚሰራባቸውን ነገሮች በመዘርዘር  የአሰራሩን ሁኔታና እንዴት መስራት እንደሚቻል ተመካከራችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## 3. በገና

ይህ መሳሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው፡፡ ቅርጹ ከክራር ጋር ይመሳሰላል፡ ፡ በአካል ግን ከክራር ረዥምና ክሩ ወፍራም የሆነና ወፍራም ድምጽ(ቤዝ) የሚያወጣና አስር ክሮች ያለዉ ነው፡፡ በገና የሚሰራዉ ከእንጨት፣ ክሩ ደግሞ ከፍየል ጅማት ተገምዶ የተዘጋጀና

በምስማር ናቸው፡፡



ስዕል 1.19፡ በገናና የአጨዋወቱ ሁኔታ የሚያሳይ ምስል

## 1.2.3 የኢትዮጵያ የሙዚቃ ቅኝቶች ባህሪያትና አይነቶች

### ሀ. የሀገራችን ቅኝቶችና ያላቸዉ ባህሪያት

**ተግባር 7**

በሀገራችን ያሉት ታዋቂ የሆኑ ቅኝቶች ስንት ናቸው? እነርሱም እነ ማን ናቸው? እንዴትስ ይመሰረታሉ ወይም ይደረደራሉ? በሶሰት ወይም በአራት ሆናችሁ በመመካከር ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ የሙዚቃ እስኬሎች እንዳሉ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ካሉት እስኬሎች ውስጥ ፔንታቶኒክ እስኬል በስፋት ይታወቃል፡፡በዚህ እስኬል ስር ታዋቂ የሆኑ አራት ቅኝቶች  አሉ፡፡እነርሱም፤

1. የትዝታ ቅኝት
2. የባቲ ቅኝት
3. የአምባሰል ቅኝት
4. የአንቺሆዬ ለኔ ቅኝት በመባል ይታወቃሉ፡፡

#### 1. የትዝታ ቅኝት

የትዝታ ቅኝትበሀገራችን ዉሰጥ አንዱና አምስት ድምጽ ያለዉ ነው፡፡ እነርሱም ትዝታ ሜጀርና ትዝታ ማይነር ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ትዝታ ሜጀር በስፋት የሚታወቀዉና የምንገለገልበት ሆኖ የአወቃቀሩ ሁኔታ ሰባቱ ከሙዚቃ ድምጾች ከመጀመሪያዉ ጀምሮ አራተኛና ሰበተኛን ድምጽ በማዉጣት/በማስቀረት የቀሩትን አምስቱ ድምጾችን በመጫወት ይሆናል፡፡


እንዲሁም ትዝታ ማይነር ደግሞ አራተኛዉና ሰባተኛዉ ድምጽ እንድወጣ ሆኖ፣ በተጨማሪ ሶስተኛና ስድስተኛ ድምጽን በግማሽ ድምጽ ወደ ኋላ በመመለስ/በመቀነስ በመጫወት ይሆናል፡፡

የ C ትዝታ ሜጀር አጨዋወት ሁኔታ በሙዚቃ መሳሪያ ላይ እንመልከት

(C, D, E, __, G, A,__, C)


(ዶ,ሬ,ሚ,__, ሶል,ላ,__, ዶ)

እናንተም በትንሹ ፒያኖ ሙዚቃ መሳሪያ ላይ ድምጹን ተለማመዱ




የትዝታ ሜጀር ቅኝትን የሚያሳይ ስዕል

ለምሳሌ የትዝታ ማይነርን አጨዋወት ሁኔታ በሙዚቃ መሳሪያ ላይ በማየት ተለማመዱ፡ ፡




የትዝታ ማይነርን አወቃቀር የሚያሳይ ስዕል

## ተግባር 8


✍ ከዚህ በላይ ያለዉን የፒያኖ/ሲንትሳይዘር ሙዚቃ መሳሪያ ስእል ከካርቶን ወይም ከትልቅ ወረቀት በቡድን በመደራጀት ውብ በሆነ ሁኔታ በመሳል ለመምህራችሁና ለክፍል ተማሪዎቻችሁ በማሳየት ተወዳደሩ፡፡

## 2. የባቲ ቅኝት

የባቲ ቅኝት ከሀገራችን ባሉት ቅኝቶች አንዱ ሆኖ እንደ ትዝታ ቅኝት ከአምስት ድምፆች የተመሰረተ ነው፡፡እርሱም ባቲ ሜጀርና ባቲ ማይነር በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡


ባቲ ሜጀር፡-የባቲ ሜጀር አወቃቀር ሁኔታ ከሰባቱ የሙዚቃ ድምጾች ከመጀመሪያ ጀምረን ሁለተኛና ስድስተኛ ድምጽን በማዉጣት የቀሩትን አምስት ድምጾችን እንጠቀማለን፡፡

ባቲ ማይነር ደግሞ ሶስተኛዉንና ሰባተኛዉን ድምጽ በግማሽ ድምጽ በመቀነስ የሚንጫወት ነው፡፡ ለምሳሌ C, __, E, F, G,__, B, C ወይም




የባቲ ሜጀር ቅኝት የሚያሰይና የድምጾቹን ቦታ የሚያሳይ ስዕል


የባቲ ማይነር ቅኝት አወቃቀር ምሳሌ




የባቲ ማይነር ቅኝት አወቃቀር የሚያሳይ ስዕል

## 3. የአምባሰል ቅኝት

አምባሰል ከሀገራችን ቅኝቶች ውስጥ አንዱ ስሆን ከሰባቱ ድምጾች መጀመሪያ ጀምረን ሶስተኛና ሰባተኛን ድምጽ በማዉጣት ሁለተኛና ስድስተኛን ድምጽ በግማሽ ድምጽ በመቀነስ የምንጫወት ነው፡፡ ለምሳሌ: C-$D^b$-F-G-$A^b$-C





የአምባሰልን ቅኝት አወቃቀር የሚያሳይ ስዕል

## 4 የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት

ይህ ቅኝት በአብዛኛዉ ጊዜ በሠርግና በበዓል ላይ ይዜማል፡፡ የሙዚቃ ባለሙያዎች የአንችሆዬ ለኔ ቅኝት የኢትዮጵያ ቅኝት ብቻ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት እንደ አምባሰል ከሰባቱ ድምጾች ሶስተኛና ሰባተኛ ድምጽን በማዉጣት ሁለተኛና አምስተኛ ድምጾችን በግማሽ ድምጽ በመቀነስ የምንጫወት ነው፡፡

ለምሳሌ C-$D^b$-F-$G^b$-C ወይም በሙዚቃ መሳሪያ ላይ የአጨዋወቱ ሁኔታ፡-




የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት አወቃቀር ከዚህ በላይ ባለዉ ሁኔታ በማየት ተለማመዱ፡፡

በሀገራችን ውስጥ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸዉ በስፋት የሚጠቀሙበት ፔንታቶኒክ ሲሆን ምታቸዉን ልዩ በማድረግ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ በተወሰኑ አከባቢዎች ውስጥ እንደ ምሳሌ ከወሰድን በአብዛኛዉ የትኛዉ ቅኝት እንደሚዘፈን ወይም በማዜም ስራ ላይ እንደሚዉል እንመልከት፡፡ በኦሮሚያ ውስጥ በአብዛኛዉ ስራ ላይ በመዋል የሚታወቁ ቅኝቶች፤ በአብዛኛዉ የትዝታ ሜጀር ቅኝት ሆኖ ባቲ ማይነርም ከእርሱ ቀጥሎ ያለ ነው፡፡

## 1.3. የትያትር እና የፊልም ጥበብ ፕሮዳክሽን አላባውያን

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

ከዚህ የትምህርት ርዕስ በኋላ ፡

- ለትያትርና ፊልም ጥበብ ዝግጅት የሚያስፈልጉ አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- በትያትር ጥበብ ውስጥ የልብስ እና የመብራት ሚናን ትገልጻላችሁ፡፡
- የትወናን የልምምድ ዘዴ ትገልጻላችሁ፡፡
- የፊልም ጥበብ ዝግጅት ሂደትን ትናገራላችሁ፡፡

*መግቢያ*

ባለፉት ትምህርቶች የትያትር ምንነት፣ አጀማመር፣ እድገት እንድሁም የትያትር እና የድራማ ልዩነት ተምራቿል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የትያትር እና የፊልም ጥበባት አዘገጃጀት ሂደቶችን ትማራላችሁ፡፡

**ተግባር 9**

1. ባለፈዉ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለ ትያትር ጥበብ የተማራችሁትን ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩ፡፡
2. ትያትርን ለማዘጋጀት ምን ምን እንደሚያስፈልጉ በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

### 1.3.1. የትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባውያን

የትያትር ጥበብ ተዘጋጅቶ በመድረክ ላይ ለተማልካቾች ለመቅረብ ብዙ ሂደቶች አሉት፡፡ ይህም ማለት የትያትር ጥበብ ዝግጅት በአንድ ሰውና በአንድ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ ሳይሆን በቡድን የሚሠራና ጊዜን የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ የትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባውያን ማለት አንድ ትያትር ከዝግጅቱ ጀምሮ ለተመልካች ለመታየት እስኪበቃ ድረስ በውስጡ የሚያካትተቸዉ ናቸው፡፡ በትያትር ጥበብ ዝግጅት አላባዉያን ውስጥ መድረክ ላይ ወጥተዉ ትወናን ከሚያከናዉኑ ሰዎች ዉጪ ለዝግጅቱ የቴክኒክ ሥራ እንደ ተመረጠዉ የፈጠራ ሥራ ድረሻቸዉን በአግባቡ የሚወጡ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህም በትያትር ጥበብ ዝግጅት ውስጥ ደጋፊዎች ተብለዉ ይጠራሉ፡፡

በሌላ በኩል የትያትር ጥበብ ዝግጅት ወይም ፕሮዳክሽን ማለትአንድትያትር በብቃት ተቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያልፍበት ሂደት ማለት ነው፡፡ ይህም ሥራ ሁሉም ተወንያን በሙያቸዉ አንፃር የሚሳተፉበት ነው፡፡አንድ የትያትር ጥበብ ዝግጅት በሚሠራዉ ዝግጅት ላይ ተመረኩዞ የሚከተሉት ነገሮች ያስፈልጉታል፡፡

- አልባሳት፣
- ሜክ አፕ/ገፅ-ቅብ ፣
- ድምፅ፣

- የመድረክ መልክ፣
- ተዋንያን፣
- ተራኪ
- ከመድረክ በስተጀርባ ያሉ ባለ ሙያዎች፣
- ደጋፊዎች እና
- መብራት ናቸው፡፡

## ሀ. አልባሳት

ባለፈው ክፍለ-ትምህርትውስጥ ስለ ትያትር ጥበብ አጀማመር ታሪክ እንደተማራችሁ፣ ትያትር ሲጀምር በግሪክ ሀገር ውስጥ የዲትረም መዝሙር ቡዲን የዳይኖሰስ ሥርዓት ትዕይንትን ስያቀርቡ ከፍየል ቆዳ የተዘጋጀ ልብስ ለብሰው ስያቀርቡ ነበር፡፡ የትያትርጥበብ ዝግጅት አልባሳት ታሪክም ከዚህ ከፍየል ቆዳ ከተዘጋጀ ልብስ ታሪክ ይጀምራል፡፡

በሮማዉያን ትያትር ጥበብ አጀማመር ታሪክ ውስጥም ተወንያን ቀሚስ እና ሽርጥ በመልበስ ትያትር ያቀርቡ ነበር፡፡ እንደዚሁ በመካከለኛ ዘመንም ትያትር ስቀርብ ለትያትሩ የሚያስፈልግ ቀሚስ በማሰፋት ይጠቀሙበት እንደነበር ታሪክ ይናገራል፡፡

በ1500-1600 ዓ. ም የኤልዛቤት ትያትር በመድረክ ላይ ሲቀርብ እንግሊዛዉያን በፋብሪካ የተመረተ አልባሳት ለብሰው ትያትሩን ስያቀርቡ ሌሎች አቅማቸዉ ለፋብሪካ ልብስ የማያበቃቸው በምፈለገው ልክ የሚያምር ልብስ መልበስ የማይችሉ ሰዎች የዘወትር ሥራ ልብሳቸዉን ለብሰው ትያትር ስያቀርቡ ነበር፡፡

ባጠቃላይ፣ የትያትር አልባሳት በልብስ ዲዛይን ጥበብ በተካነ ሰው እና በመድረክ ላይ ለሚቀርበዉ ትያትር ተካፋይ በሆነ ሰው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ስለዚህ የትያትር ልብስ ዲዛይነር የሚከተሉት ድርሻዎች ይኖሩታል፡፡

- ተዋንያን ለብሰው የሚያቀርቡትን ልብስ መለየት
- ልብስ ማዘጋጅት (ዲዛይን ማድረግ)እና
- ሰሰየተዋንያን  ልብስ ማቅረብ ናቸው፡፡

## ለ. ገፅ-ቅብ /መዋቢያ

ገፅ-ቅብ/መዋቢያ በተዋናይ ፊት ላይ የሚሰራ ነገር ነው፡፡ ይህም በዝግጅቱ ላይ ተመስርተው የሚሰራ ነው፡፡ የተዋንያንን የአቋቋም ሁኔታ ለመቀየር የሚያግዝ ነው፡፡ አብዛኞቹ ዝግጅቶች መሰረታዊ የመዋቢያ ሜካፖች የሚጠቀሙ ቢሆንም አንዳንዶቹ እርጅና ለማሳየት፣ ህመምተኛ ለማስመሰል እና ለመሳሰሉት ሁኔታዎች ልዩ ሜካፕ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የመዋቢያ/ሜካፕ ጥቅሞች

- በተዋናይ ፊት ላይ ጠባሳ ከተገኘ ለማጥፋት
- የተዋናይ ፊት በደምብ እንዲታይ
- ፊትን በመግለጽ ከድረጊት ጋር ለማወሃድ
- ተዋንያንን ማራኪ ለማድረግ

- ተዋንያን የሚፈልጉትን ድርሻ በነፃነት እንዲተዉኑ ለማድረግ

## ሐ. መብራት

መብራት ልክ እንደ አልባሳት በመብራት በለሙያ ለትያትሩ እንደሚመች ተደርጎ ይዘጋጃል፡፡ መብራት በመድረክ ላይ ተዋንያን ከመሳየት ጀምሮ የትያትሩን ታሪክ እዉን ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለዉ፡፡

የመብራት በለሙያ ድርሻ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ተዉኔቱን ስክሪፕቱን) በማንበብ የሚያስፈልገዉን መብራት መለየት፡፡
- ትያትሩ የሚቀርብበት ቦታ በመሄድ መጋረጃና ለመብራት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት፡፡
- ለመብራት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት፣

  ለምሳሌ፡- አስፈላጊዉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም በመብራት ላይ እንዲጨመሩ ማድረግ፡፡

## መ. ግባዓተ-ድምፅ

የድምፅ ባለሙያ ስክሪፕቱን በማንበብ ለታሪኩ የምስማማን ድምፅ በመለየት ያዘጋጃሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በእስክሪፕቱ ውስጥ የንጋት /የጎህ መቅደድ/ ታሪክ ተጽፎ ከተገኘ ንጋትን የሚገልጹ ድምፆች እንደ የወፎች ጫጫታ፣ በከተማ አከባቢ የፀሎት ድምፅ እና የመሳሰሉትን ከሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች ጋር ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፡፡

## ሠ. የመድረክ መልክ

የመድረክ መልክበትያትር ፕሮዳክሽን ውስጥ የትረካዉን ቦታ በሚገልጽ ስሜት የሚገነባ ነው፡ ፡ የመድረክ መልክበትረካዉ (ስክሪፕቱ) ላይ መቼቱ በተደራጀ መልክ የሚገለጽበት ሁኔታ ነው፡፡ የመድረክ መልክከወንበር ጀምሮ ድራማዉ የተከናወነበትን ቦታ፣ የተገነባ ቤትን ጨምሮ በመድረክ ላይ የየምንጠቀምባቸውን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡

በአጠቃላይ የመድረክ መልክማለት አንድ ድራማ ተፈጥሮአዊ ሆኖበሚያምር መልክእዉናዊ መስሎ እንዲቀርብ የሚደረግበት ጥበብ ነው፡፡

## ረ. ተዋንያን

ተዋንያንማለት በትያትር ዝግጅት ውስጥ የተሰጣቸዉን ገፀ-ባሕርይወክለዉ በአንድነት መድረክ ላይ ወጥተዉ የሚያሳዩ ሰዎች ናቸው፡፡ ተዋንያን ወንድም ሴትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ሰ. ትወና

ትወና በትያትር፣ በፊልም፣ በራዲዮ ድራማ እና በሌሎችም ጭውውትውስጥ የአንድ ኩነት ታራኪ በተዋንያን ከተለማመዱ በኋላ፣ ታሪኩን ከማስመሰል ወደ እውነተኛ ኩነት መስሎ ማቅረብ መቻል ነው፡፡

ትወና አርቆ የማሰብ ትንታኔ፣ ስሜትን መግለጽ፣ ትርጉም ያለዉ የአካል እንቅስቃሴ፣ ከፍ ያለ ድምፅ፣ በደንብ የሚሰማ ንግግር እና እስክሪፕቱን የመተርጎም ጥበብን ያካተተ ጥበብ ነው፡፡

እንዲሁም ትወና የተለያዩ ቃለቶችን፣ ንግግሮችን፣ ድንገቴ ፈጠራ፣ ጭዉዉቶችን፣ ማይምክ፣ የመድረክ ግጭቶችን እና የመሳሰሉትን ጥበባት ያካትታል፡፡ ስለዚህ ተዋንያን ደጋግመው መለማማድ አለባቸዉ፡፡ በትወና ልምምድ ውስጥ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋና የሆኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ. የሜይስኔሪ ዘዴ

የሜይስኔሪ ዘዴበእውነተኛ ትወና ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ተዋንያን በዉስጣቸዉ የሚሰማዉን ስሜት እንዲጫወቱ ያበረታታል፡፡ በአዕምሮ ከሚብሰለሰል ይልቅ ልባቸዉ የሚናገራቸዉን ሆነው እንዲሰሩ የሚያሳይነው፡፡

### ለ. የእስታንስላቭስኪ ዘዴ

የእስታንስላቭስኪ ዘዴተዋንያን ያለፈ ትዝታቸዉን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፡፡ ተዋንያን በህይወታቸዉ ያሳለፉትን፣ ማስታወሻቸዉን ወደ ኋላ ተመልሰው እንዲያሰላስሉ ይጠይቃል፡፡ ወይም ተዋንያን "ይህ ኩነት በእውነት እኔ ላይ ቢፈጸም እንዴት ሊተዉን እችላለሁ?" ብለዉ ራሳቸዉን እንዲጠይቁ የሚያደርግ ነው፡፡

የእስታንስላቭስኪ ዘዴአራት አላባውያንአሉት፣

- ትኩረት
- ነፃ አካልና ሃሳብ
- የትዝታ ስሜት
- እውነተኛነት

### ሸ. ደጋፊዎች

ደጋፊዎች ማለት በቀጥታ መድረክ ላይ የማይታዩ ግን በሚዘጋጀዉ ትያትር ውስጥ በቴክኒክ ሥራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚደግፉ ናቸው፡፡

### ቀ. መብራት

መብራት በትያትር ፕሮዳክሽን ውስጥ የታሪኩን መቼት እውን እና ሙሉ ለማድረግ የሚንጠቀምበት ሆኖ በመጠንና በአይነት የተለያዩ ናቸው፡፡

## 1.3.2. የትያትር ጥበብ ፕሮዳክሽን ደረጃዎች

የትያትር ጥበብ ፕሮዳክሽን ደረጃዎች ማለት በአንድ ጥያትር ዝግጅት ውስጥ የሚታለፉ ደረጃዎች ማለት ነው፡፡ እነዚህም ደረጃዎች በሦስት ትላልቅ ቦታዎች ይከፈላሉ፡፡

እነሱም፡

1. ከዝግጅት በፊት
2. የዝግጅት ጊዜ
3. ከዝግጅት በኋላ

### 1. ከዝግጅት በፊት ደረጃ

ይህ ደረጃ የመጀመሪያዉ የትያትር ዝግጅት (ፕሮዳክሽን) ቅድመሁኔታነው፡፡ ይህም፤አንድ ታሪክ (ተዉኔት) ተመርጦ ከሚዘጋጅበት ጊዜ አንስቶ የተዋንያን መረጣ፣ የቦታ መረጣ፣ የበጀት እና የቁሳቁስ መረጣ እንዲሁም የልምምድ ጊዜና ሁሉንም የቴክኒክ ዝግጅት ያጠቃልላል፡፡

### 2. የዝግጅት ጊዜ

ይህ ደረጃ ደግሞ አንድ ትያትር ልምምድ ከተጠናቀቀ በኋላ መድረክ ላይ ለእይታ ሲቀርብ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ተዋንያን በመድረክ ላይ የሚያሳዩትን ተግባር፣ የተመልካቾች ስሜት፣ የመድረክ አያያዝ ሁኔታ፣ የልብስና ሜካፕ፣ የተዋናይ ስሜት፣ የመብራት እና ድምፅ አጠቃቀም ይጠቃልላል፡፡

### 3. ከዝግጅት በኋላ

ይህ ደረጃ አንድ ትያትር ልምምዱ ተጠናቅቆ ለመድረክ ክፍት ሲሆን፣ የማስታወቂያ እና ማከፋፈያ ጊዜን ያጠቃልላል፡፡ ይህም ትያትሩ ለህዝብ እንዲቀርብ ቦታ መምረጥ፣ ተመልካቾችን መምረጥ እና በቀጥታ ማሳየትን ያካትታል፡፡

## 1.3.3. የፊልም ጥበብ ዝግጅት አላባውያን

የፊልም ጥበብ ዝግጅት አላባውያን የሚባሉት በአንድ የፊልም ዝግጅት ውስጥ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የሚታቀፉት ነገሮች ናቸው፡፡ እነርሱም፣ ገጸ-ባህሪይ (የተወናይ ድርጊት)፣ መቼትና ቁሳቁስ፣ ካሜራ፣ መብራት፣ ቀለም፣ ድምፅ፣ ሙዚቃ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ሀ. ገጸ-ባህሪይ ትወና

ገጸ-ባህሪይ በአንድ ፊልም ውስጥ አንድን ታሪክ ተዋናይ ተካፍሎ ስያከናዉን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም በፊልም ጥበብ ቴክኒክ ዝግጅት ውስጥ የተዋናይ ድርጊት ወደ ቀረፃ እንዴት እንደሚመጣ ከካሜራ ማዕዘን ጋር በማቀናጀት የሚያሳይ ነው፡፡

### ለ. መቼትና ቁሳቁሶች

በፊልም ጥበብ ዝግጅት ውስጥ አንድ ታሪክ መቼና የት እንደተፈጸመ፣ በዝግጅቱ ውስጥ ምን አይነት ቁሳቁስ በመጠቀም የታሪኩን እዉነታ ለመግለፅ እንደሚገባ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህም ታሪኩ መቼና የት እንደተፈጸመ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማህበረሰብ ውስጥ ካለውእውነታ ጋር አቀናጅቶ የሚያቀርብና ታሪኩ በተፈጸመበት ዘመን የነበሩትን ቁሳቁስ እና በዘመኑ የነበሩትን ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚገልጽ ነው፡፡

### ሐ. ካሜራ

ካሜራ የአንድ ፊልም ታሪክ ተዋንያን ልምምድ ከተዘጋጁ በኋላ የሚቀረጽበት እና ቪዲዮዉን ወደ ፊልም በመቀየር የሚቀርብበት መሳሪያ ነው፡፡ ይህም በፊልሙ የታሪክ ግንባታ ላይ በሚገኝበት ሁኔታ ሪቀት፣ መዕዘን እና የተለያዩ እንቅስቃሴ ያለዉና የቀረበዉን ታሪክ እዉነታን ለመግለጽ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

### መ. መብራት

መብራት በፊልም ጥበብ ዝግጅት ውስጥ እይታን ለማሳመር፣ መቼትን እውን ለማድረግ፣ እንዲሁም የተዋንያንን ስሜት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅም ነው፡፡ ይህም በፊልሙ ታሪክ ላይ በመመስረት አይነት እና አቅጣጫ፣ እንዲሁም በተለያዩ ጥንካሬ ወደ ፊልም ጥበብ የሚጨመር ነው፡፡

### ሠ. ቀለም

በፊልም ውስጥ ቀለም ተዋናዩ ያለበትን ስሜት ለመግለጽ ያገለግላል፡፡ ይህም ጸሃፊዉ በፊልሙ ውስጥ ታሪኩን አቀናጅቶ ባስቀመጠዉ መሰረት ይሆናል፡፡ የተለያዩ ቀለማትን እንደሚንጠቀም ሁሉ የተዋናይ ስሜትም በቀለሙ ውስጥ እውናዊ ይሆናል፡፡

### ረ. ግበዓት ድምፅ እና ሙዚቃ

ድምፅ እና ሙዚቃ በፊልሙ የታሪክ ጽሁፍ ላይ በመመስረት የተዋናይን ስሜት እውን ለማድረግ፣ እውናዊዉን መቼት ለመፍጠር፣ እንዲሁም የአንድን የፊልም ጥበብ መልዕክት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ይህም ከፊልሙ ታሪክ ጋር የሚገናኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ድምፆችን በመጠቀም የተዋንያንን ስሜት በሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም መግለጽ፣ የፊልሙን መልዕክት ሙሉ ማድረግ እና የተዋንያንን የትወና ብቃት ሙሉ ለማድረግ የሚጠቅሙ ናቸው፡
፡

## 1.3.4. የፊልም ፕሮዳክሽን ደረጃዎች

አንድ ፊልም ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻዉ በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ በማለፍ ይዘጋጃል፡
፡ ፊልም ከትያትር ይልቅ የተለያዩ ባለሙያዎችንና የሰው ጉልበትን ይጠይቃል፡፡ በፊልም ዝግጅት ሂደት ውስጥ ሶስት ትላልቅ ደረጃዎች አሉ፡፡ የሶስቱ ደረጃዎች ክፍፍልም በሚሠራው ስራና አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እነርሱም፡

- ቅድመ ፊልም ዝግጅት
- የዝግጅት ጊዜ እና
- ከዝግጅት በኋላ ይባላሉ፡፡

### ሀ. ቅድመ ፊልም ዝግጅት

በቅድመ ፊልም ዝግጅት ጊዜ የሚሰሩ ሥራዎች፣ አብሮ የሚሰሩትን ተዋንያን መለየት፣ ቁሳቁስና የልምምድ ጊዜን ማሳወቅ፣ የልምምድ የጊዜ ሰሌዳን ማዘጋጀት፣ የሚያስፈልገውን በጀት ማዘጋጀት፣ ፊልሙን ከሚደግፉት አከላት ጋር ለመሥራት ዝግጅት ማድረግ፣ ተዋንያን ስክሪፕቱን እንዲያነቡ ማድረግ፣ ተዋንያን ከአዘጋጁና አብሮ ከሚሰሩት ማለትም ከመብራት ባለሙያ፣ ከድምፅ አሳማሪ ባለሙያ፣ የአልባሳት ባለሙያ፣ እና ሌሎችም የቴክኒክ ሥራ ከሚሰሩት ጋር መተዋወቅ፡፡

በተጨማሪም በፊልሙ አሰራር ላይ አስፈላጊዉን ገለጻ መሰጣጠት፣ ታሪኩን መከፋፈል፣ በተከፋፈሉት ታሪክ ላይ ሊያጋጥሙቸዉ የሚችሉትን ችግሮች መለየት እና ተዋንያን ፊልሙን ከሚያዘጋጀዉ አካል ጋር ዉል መፈራረም እና ወደ ሥራ መግባትበዚህ ደረጃ ውስጥ የሚጠቃላሉ

ናቸው፡፡

## ለ. የዝግጅት ጊዜ

የዝግጅት ጊዜ ፊልሙ የሚሰራበት ጊዜ ማለት ነው፡፡ የሚያስፈልጉ ነገሮች ተዘጋጅቶ የልምምድ ጊዜ የሚደረግበት እና ፊልሙ በየእይታዉ ተከፋፍሎ የሚቀረጽበት ጊዜ ነው፡፡ በፊልሙ ፕሮዳክሽን ጊዜ ሁሉም ተዋናይና ደጋፊዎች የድርሻቸዉን የሚወጡበት ጊዜ ነው፡፡ በአጠቃላይ በፕሮዳክሽን ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎችየሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፊልም መቅረጽ
- የተቀረጸዉን ፊልም ግድፈቱን በመለየት አንደገና እንድቀረፅ ማድረግ
- ከተቀረጸዉን ፊልም ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችንለይቶ ማዉጣት

## ሐ. ከዝግጅት በኋላ

ከዝግጅት በኋላ የሚሰራዉ ሥራ የተሰራዉን ፊልም መሰብሰብ፣ አስፈላጊውን አርትኦት ማድረግ፣ የማያስፈልጉትን ነገሮች ማስቀረትእና በትክክል መሰራቱን በማረጋገጥ ማዘጋጀትን የጠቃልላል፡ ፡ በአጠቃላይ ከዝግጅት በኋላ የሚሰራ ሥራየሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- የአርትኦት ስራ መሥራት
- ፊልሙን ማስተዋወቅ
- ለገበያ ማቅረብና
- ለተመልካች ማቅረብናቸው፡፡

## የዚህ ትምህርት ርኢስ ማጠቃለያ ሃሳብ

- ቅርፃቅርፅ ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ካላቸዉ እና ቀለል ባሉ ነገሮች መሰራት ይቻላል፡፡
- የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቅርፃቅርፅ ስራዎችን ሲሰራ ነበር፡፡
- ቅርፃቅርፅ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ እና ከሰው ልጅ ጋር እኩል እድሜ ያለዉ ነው፡፡.
- ለቅርፃቅርፅ የተሰጠዉ ትርጉም እና ማብራሪያ በፊት ከሚታወቀዉ፤ በ20 ኛዉ ክፍለ ዘመን ስስፋፋ ነበር፡፡
- በቅር ፃቅርፅ ስራ ውስጥ እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ እና አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው፡፡
- ቅርፃ ቅርፅ/sculpture/የሚባል ቃል በላቲን ቋንቋ "Sculptura" ከሚልቃል የመጣ ነው፡፡
- ቅርፃ ቅርፅ የአንድን ነገር እውናዊ የሆነ ቁስ አካል ማሰያት የሚችል ሲሆን ስዕል በሆኑ ነገሮች (በቀለም ቅብ እና ንድፍ)ማሳየት የማይቻል ነገር ማሳየት የሚችል ነው፡፡.
- የቅርፃ ቅርፅ አለባውያን ለቅርፃ ቅርፅ እና ፎርም ላላቸዉ ነገሮች መፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡
- የትያትር ፕሮዳክሽን ማለት አንድ ትያትር ማለፍ ያለበት ሂደት አልፎ መድረክ ላይ ለተመልካች ማቅረብ ማለት ነው፡፡
- አንድ የፊልም ጥበብ ከጅምሩ አንስቶ እስከ መጨረሻዉ ደረጃ የተለያዩ ሂደት ውስጥ በማለፍ ለእይታ ይበቃል፡፡
- የዝግጅት ጊዜ የሚባለዉ ፊልሙ የሚሰራበት ጊዜ ማለት ነው፡፡
- የመድረክ መልክ በትያትር ሮደክሽን ውስጥ የታሪኩን ስሜት መግለፅና መፍጠር በሚችለዉ ማዕዘን ይሰራል፡፡
- የሚይስኔር ስልት በእውነተኛ የትወና ስራ ላይ ይመሰረታል፡፡

## የምዕራፍ 1 መልመጃ

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች የተሰጠው ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ቅርፃ ቅርፅ የጥበብ ስራዎች ከሚሠሩባቸው ዘዴዎች አንዱ ሲሆን፤ የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲሰራ የቆየ ነው፡፡
2. የሰው ልጅ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎችን ይሰራል፡፡
3. የቅርፃ ቅርፅ ታሪክ እና አመጣጥ ሲንመለከት፤ ረጅም እድሜ ያስቆጠረ አይደለም፡፡
4. በቅርፃ ቅርፅ ሥራ እና በሰው ልጅ መሃከል ጠንካራ ትስስር አለ፡፡.
5. ለቅርፃ ቅርፅ የሚሰጠዉ ትርጉም እና ማብራሪያ በፊት ከነበረበት ሁኔታ በስፋት መሰጠት የጀመረው ከ18ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው፡፡
6. ሁል ጊዜ ቅርፃ ቅርፅ የተፈጥሮ ነገሮችን የሚመስል ወይም የሚተካ ነገር ብቻ ያሳያል፡፡
7. ስዕል ያልሆኑ የቅርፃ ቅርፅ ስራዎች አንድ ነገር በተፈጥሮ የሚይዘውን አካል ሙሉ በሙሉ የሚያሳዩ ናቸው፡፡
8. በቅርፃ ቅርፅ ስራዎች ውስጥ እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ እና አስፈላጊ ነው፡፡
9. ፊንጌ ከክር የሙዚቃ መሳሪያ  አንዱ ነዉ፡፡
10. የትዝታ ቅኝት ከሜጀር እስኬል ድምጾች ዉስጥ 4ኛ እና 7ኛን በማዉጣት ይጫወታል፡፡
11. የባህል ሙዚቃ የስራ ዘፈኖችን አያካትትም፡፡
12. እንደ ሃገራችን የሙዚቃ መሳሪያ ዓይነቶች  በሁለት ቦታ ይካፈላሉ፡፡
13. በኦሮሚያ በስፋት ሥራ ላይ እየዋለ ያለዉ የሙዚቃ ቅኝት  እንቺሆዬ ለኔ ነዉ፡፡
14. የሜይስኔሪ ዘዴ አራት አለባውያን አለዉ፡፡
15. ከዝግጅት በኋላ የሚሰሩ ስራዎች የተሰራዉን ፊልም መሰብሰብ፣ አረትኦት ማድረግና የማያስፈልጉትን ነገሮች ማስቀረት ናቸው፡፡
16. አንድን የፊልም ጥበብ ሥራ ከጅምሩ እስከ መጠናቀቂያ በአንድ በለሙያ ብቻ ይሠራል፡፡
17. በትወና ድርጊት የእስታንስላቭስኪ ዘዴ ገፀ-ባህሪያት የራሳቸዉን የስሜት  ትዝታ እንድጠቀሙ ያበረታታቸዋል፡፡

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት መሳሪያዎች ውስጥ የሰው ልጅ በስልጣኔ ከማደጉ በፊት ያልተጠቀመበት የቱ ነው?
   ሀ. ድንጋይ
   ለ. ብረት
   ሐ. የእንስሳት አጥንት
   መ. የእንስሳት ቀንድ

2. ከሚከተሉት ውስጥ የቅርፃ ቅርፅ ስራ የቱን ይገልፃል?

   ሀ. ስሜት ለ. ታሪክ

   ሐ. ባህል መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

3. ስለ ቅርፃ ቅርፅ ስራዎች በፊት ሲሰጥ የነበረዉ ዉስን ሃሳብ ቀርቶ፤ ሰፊ ሃሳብ መሰጠት የተጀመረዉ በምን ምክንያት ነው?

   ሀ. የቴክኖሎጂ እድገት

   ለ. የአዳዲስ መሳሪያዎች መሠራት

   ሐ. ለቅርፃ ቅርፅ ስራ አዳዲስ ዘዴዎች ተግበራዊ መሆን

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

4. ከሚከተሉት ውስጥ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ማካተት የሚገባው የቱ ነው?

   ሀ. ወርድ ለ. ቁመት

   ሐ. ርዝመት መ. መልስ አልተሰጠም፡፡

5. ቅርፃ ቅርፅን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ቁስ አካላዊ ነው፡፡ ሐ. ጠጣር ነው፡፡

   ለ. በሁለት እይታ ብቻ የሚገለፅ ነው፡፡ መ. በእጅ ይዳሰሳል፡፡

6. ከሚከተሉት ቅርፃ ቅርፅ ከሚሰራበት ዘዴዎች የጥንት ያልሆነ የቱ ነው?

   ሀ. መጥረብ ለ. መላግ

   ሐ. መበየድ መ. መልስ አልተሰጠም፡፡

7. “Sculptura” የሚለው የላቲን ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?

   ሀ.ማጉበጥ/መጠምዘዝ ለ. መቆራረጥ

   ሐ. ከላይ መላግ መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

8. ከሚከተሉት ውስጥ ቅርፃ ቅርፅ ከድንጋይ በየትኛዉ ዘዴ ሊሰራ ይችላል?

   ሀ. መላግ ለ. መበየድ

   ሐ. መጥረብ መ. ማምረት

9. ከሚከተሉት ሙዚቃ ልዩ የሆነው የቱ ነዉ?

   ሀ. ዉዝዋዜ ሐ. ጭፋራ

   ለ. ኢስክስታ መ. ዳንኪራ

10. የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነዉ ?

   ሀ. ኪራር ለ.ፋጋ ሐ. አታሞ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸዉ

11. የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነዉ ?

   ሀ.ከበሮ ሐ.ጡሩምባ

   ለ.መስንቆ መ.መልስ አልተሰጠም

12. ከሚከተሉት አንዱ የሙዚቃ መሳሪያ አይደለም፡፡

ሀ. ከበሳ ሐ. ፋጋ

ለ. ዳንኪራ መ. ከበሮ

13. C, __E, F, G,___ B, C ይህ ቅኝት......... ነዉ

ሀ. ባቲ ሜጀር ሐ. አመባሰል

ለ. ትዝታ መ. አንቺሆዬ ለኔ

14. ከሚከተሉት በፊልም ጥበብ ዝግጅት ጊዜ የሚሰራው የትኛዉ ነው?

ሀ. ፊልሙን ማስተዋወቅ

ለ. የማብራት እና ድምፅ አጠቃቀም

ሐ. የልምምድ ጊዜን ማስተዋወቅ

መ. በጀት መዘጋጀት

15. ከሚከተለዉ አንዱ የጥበብ አልባሳት በለሙያ ድርሻ አይደለም፡፡

ሀ. አልባሳትን ማዘጋጀት ሐ. ትወናን መረዳት

ለ. የተዋንያን ልብስ መለየት መ. የቀረፃ ማዕዘናትን መምረጥ

16. ከሚከተለዉ አንዱ በመድረክ ላይ የሚታየዉን ሁሉ ያከትታል፡፡

ሀ. የተዋንያን ትወና ሐ. ድምፅ

ለ. ሲነሪ መ. መብራት

17. የመብራት ጥበብ በለሙያ ሥራ የሆነው የትኛዉ ነው?

ሀ. የተዋንያን ማቅረብያ አልባሳትን መለየት

ለ. አልባሳትን መቅረፅ

ሐ. ስክረፕትን በማንበብ የሚያስፈልገዉ ንብራት መለየት

መ. ሁሉም

## ሐ. ከዚህ በታች ለሉተ ጥያቄዎች በጹሁፍ መልሱ

1. የምት ሙዚቃ መሰሪያዎችን ዘርዚሩ ?
2. የእትዮያ የባህል ሙዚቃ መሰሪያዎች በስንት ይካፈላሉ?
3. በኦሮሚያ በብዛት የምንጠቀመዉ የሙዚቃ ቅኝት የቱ ነዉ?

# ምዕራፍ 2
# የፈጠራ ችሎታ

## የምዕራፉ ትምህርት ውጤት፡

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡

- የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸዉን ኖታዎች ታነባለችሁ፡፡
- የአንቺሆዬ ለኔ እና የአምባሰልን ቅኝቶች ለይታችሁ ትገልፃላችሁ፡፡
- በአንቺ ሆዬ ለኔ እና በአምባሰል ቅኝት በመጠቀም ቀለል ያለ ሙዚቃን ትጫወታላችሁ፡፡
- ባህላዊ ውዝዋዜን በተግባር ታሳያላችሁ፡፡
- ለትያትር ፊልም ፕሮዳክሽን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- አጭር የፈጠራታሪክ ለትያትርና ፊልም ጥበብ ትፅፋላችሁ፡፡
- የግራፊክስ ትምህርት ምንነት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የፔፐር ማሼ ስራ ሂደት ትለያላችሁ፡፡
- የሸክላ ስራ ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡

### መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስለ ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሳሪያ ዓይነቶች፣ጠቀሜታ እና ድርሻ፣ስለ ቅኝትና ዉዝዋዜ ተምራቿል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሶልፌጅዮ ምንነት እና አጠቃቀም እንዲሁም የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝቶችን (አንቺሆዬ ለኔ እና አምባሰልን)እንዴት መጨወት እንደሚቻል ከባህላዊ ዉዝዋዜ ጋር አያይዞችዉ ትማራላችሁ፡፡ በምዕራፍ አንድ ዉስጥ የስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም ፕሮዳክሽን ተምራቿል፡፡ እንዲሁም በተዉኔት ዘዴዎች ውስጥ የሚፈጸሙትን ስራዎች ተረድታቸዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ደግሞ ለትያትር እና ፊልም ፕሮዳክሽን ምን እንደሚያስፈልግ እና ሂደቱን የምትማሩ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም፣የትያትር እና ፊልም አጭር ታሪክ ፈጠራ እና አንድ የትያትር ጥበብ ለመመዘን እንድትችሉ አስፈላጊውን ክህሎት የሚትጎናጸፉ ይሆናል፡፡

የሸክላ ስራ ሙያ የቅርጻ ቅርጽ ሙያ የሚሰራበት ስራ ነው፡፡ የሸክላ አፈር ዓይነቶች፣ ለሸክላ ስራ ሙያ የሚውሉ ከቦታ ቦታ ልዩነት አሏቸው፡፡ የሸክላ አፈር፣ የፔፐር ማሼ እና የህትመት ስራ ውጤቶች ለተለያዩ ነገሮች አገልግሎት ለማስዋቢያ ስራ ይዉሉ ነበር፡፡

## 2.1. ሶልፌጅዮን በኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት (በአንቺ ሆዬ ለኔ እና አምባሰል)

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ :

- የሶልፌጅዮ ትርጉም እና ጥቅምን ለይታችው ትናገራላችሁ፡፡
- የአንቺ ሆዬ ለኔ እና የአምባሰል ቅኝቶችን ለይታችው ትገልጻላችሁ፡፡

የግንዛቤ ጥያቄ

ሙዚቃን ለመጫወት ሶልፌጅዮ የጀርባ አጥንት ነው ሲባል ምን ማለት ነው? የተበላበት ምክንያት ምንድን ነው?

### 2.1.1 ሶልፌጅዮ

**ተግባር 1**

1. ሶልፌጅዮ ምንድን ነው ?
2. ሶልፌጅዮ በሙዚቃ ውስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ሶልፌጅዮ ማለት ከሙዚቃ ሳይንስ አንዱ ሆኖ ሙዚቃን ማዳመጥ፣ መፃፍና ማንበብ ውስጥ ባለዉ ችሎታ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የተለያዩ የሙዚቃ ምቶች፣የኖታዎችን ድምጽ በጆሮ ሰምቶ መለየትና የተጻፌዉን ዜማ ማንበብ እና መማር የሚቻለው በሶልፌጅዮ ነው፡፡

ሶልፌጅዮ እንደ ሌሎች የትምህርት መስኮች በሂደት ወይም በልምምድ መማር ይቻላል፡፡ በሙዚቃ ሳይንስና የሙዚቃ ችሎታን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ያለዉ አስተዋጽዎ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደሚታወቀዉ በሙዚቃ ውስጥ የተለያዩ ዘፌኖችና ዜማዎች በተቀናጀ እና ዉበት ባለዉ መልክ የሰዉን ስሜት እንዲማርክ ለማድረግና እና በሰው ውስጥ ተነሳሽነትን የሚፈጠረው በሶልፌጅዮ አማካኝነት ነው፡፡ ስለዚህ ሶልፌጅዮ ለተለያዩ ምቶችና ዜማዎችን ከዋናዉ እስከ ላይ ድረስ ለመማር የሚያስችል ነው፡፡


### ምቶችን የማንበብ ልምምድ

ኖታዎችን ስናነብ ወይም ስንለማመድ እጃችንን በማጨብጨብ ወይም በእግራችን መሬትን በመርገጥ፣ ኖታዎች በተጻፈላቸው ዋጋ ምት ልክ ቆጥረን እንለማመዳለን፡፡

**ልምምድ 1**

1.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች በተሰጠው የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመስረት "ታ" በማለት ተለማማዱ፡፡


ሀ.




ለ.




ሐ.




መ.





ሠ.



ረ.







## ልምምድ 2

2.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች በተሰጠው የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመስረት "ታ" በማለት ተለማማዱ፡፡





## ልምምድ 3

3. ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች በተሰጠው የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመስረት "ታ" በማለት ተለማማዱ፡፡



## ልምምድ፡4

4.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች በተሰጠው የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመስረት “ታ” ወይም “ላ” በማለት ተለማማዱ፡፡



## ልምምድ፡5

5.ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች በተሰጠው የጊዜ መለኪያቸዉ ላይ በመመስረት “ታ” በማለት ተለማማዱ፡፡



### 2.1.2. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ቅኝት

ባለፈዉ ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተማራችሁ ሃገራችን የራሷ የሆነ የሙዚቃ ቅኝት እንዳላት ይታወቃል፡፡ ከእነርሱ ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የአምባሰልና የአንቺሆዬ ለኔ ቅኝቶችን እናያለን፡፡

#### 2.1.2.1. የአምባሰል ቅኝት

የአምባሰል ቅኝት ባለፈዉ ትምህርት ለማየት እንደሞከርነዉ ባሉት ሰባት ድምጾች ከመጀመሪያ ጀምረን ሶስተኛና ሰባተኛ ድምጽን በማዉጣት ሁለተኛና ስድስተኛ ድምጽን በግማሽ ድምጽ በመቀነስ የሚንጫወተዉ ነው፡፡


C-$D^b$-F-G-$A^b$-C

##### 1. C አምባሰል


C D <u>E</u> F G A B C (CM)

C $D^b$ F G $A^b$ C (C አምባሰል)

C አምባሰልን በአንድ እጅ በሚንጫወትበት ጊዜ ከዚህ በታች ባለዉ የሙዚቃ እስታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡



C አምባሰልን ከዚህ በታች ባለዉ ትልቁ እሰታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡




## 2. D አምባሰል


D, E,F$^{\#}$, G ,A, B ,C$^{\#}$D,(DM)


D E$^{b}$ G A B$^{b}$ D (D አምባሰል)

D አምባሰልን ከዚህ በታች ባለዉ የሙዚቃ እስታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡



D. አምባሰልን ከዚህ በታች ባለዉ ትልቁ እስታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡





### 3. ምሳሌ $A^b$አምባሰል

$A^b$ $B^b$ <u>C</u> $D^b$ $E^b$ F <u>G</u> $A^b$ ($A^b$M)


$A^b$ $B^{bb}D^bE^bF^b$ $A^b$ ($A^b$አምባሰል )

$A^b$ አምባሰልን ከዚህ በታች ባለዉ ትልቁ እስታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡



## ተግባር 2

1. ከዚህ በታች ያሉ ድምጾችን መነሻ በማድረግ የአምባሰልን ቅኝት በትሬብልና በቤዝ ክሌፍ ላይ አሳዩ፡፡



2. ከዚህ በታች ያሉትን በመጠቀም በክሌፎች ላይ የአምባሰልን ቅኝት መስርቱ፡፡

ሀ. G አምባሰል


ለ. $E^b$አምባሰል

## 2.1.2.2. የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት


ከዚህ በፊት እንደተማራችሁ ይህ ቅኝት በአብዛኛዉ በሰርግና ክብረ በዓላት ላይ ይዜማል/ይዘፈናል፡፡ የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት እንደ አምባሰል ቅኝት ሶስተኛና ሰባተኛ ድምጽን በማዉጣት ሁለተኛና አምሰተኛ ድምጽን በግማሽ በመቀነስ የሚንጫወት ነው፡፡

ለምሳሌ የ C አንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት

1. C D <u>E</u> F G A <u>B</u> C
2. C $D^b$ F $G^b$ A C (C አንቺ ሆዬ ለኔ)




C አንቺሆዬ ለኔ ቅኝትን ከዚህ በታች ባለዉ ትልቁ እስታፍ ለይ ተከታተሉ፡፡




F አንቺ ሆዬ ለኔ F, $G^b$, B, $C^b$, D, F

F አንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝትን ከዚህ በታች ባለዉ የሙዚቃ እስታፍ ላይ ተከታተሉ፡፡




A አንቺ ሆዬ ለኔ, A, $B^b$, D, $E^b$, F, A,



## ተግባር 3

1. ከዚህ በታች ያሉድምጾችን መነሻ በማድረግ አንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝት በትረብልና ቤዝ ክሌፍ ላይ አሳዩ፡፡




2. ከዚህ በታች ያሉትን እንደ መነሻበመጠቀም በክሌፎች ላይ የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝትን መስርቱ፡፡

ሀ. B♭አንቺ ሆዬ ለኔ


ለ. D አንቺ ሆዬ ለኔ

3. ከዚህ በታች ያለዉን የአምባሰልና አንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝቶችን ዘምሩ፡፡

ሀ. የአንቺ ሆዬ ለኔ ቅኝትን መዘመር



ለ.የአምባሰልን ቅኝት መዘመር



## 2.2. ባህላዊ ውዝዋዜ

ባህላዊ ውዝዋዜ  እንደ ሌሎች ባህላዊ እሴቶችየአንድን ማህበረሰብ ማንነት ማሳያ ከሆኑ እሴቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የምግብ፣የአልባሳት፣የመረዳዳት፣የእምነትና የመሳሰሉት ባህሎች አንዱን ብሔር  ከሌላዉ እንደሚለዩ ሁሉ የባህል ውዝዋዜ ሁኔታም ከቦታ ቦታ ልዩነት አለዉ፡፡ በውዝዋዜ የሚሳተፉ ሰዎች እድሜ፣እንቅስቃሴ፣ ጊዜ እና ስነ ስርዓት ከቦታ ቦታ ተመሳሳይነትና ልዩነት አለዉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በተወሰኑ የሃገራችን ክፍሎች የሚታወቁ የውዝዋዜ አይነቶችን እንመልከት፡፡

አንድ ማህበረሰብ ባህሉን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ በተለያየ መልክ በማስተላለፍ፤ እርስ በረሱን እያዝናና እና እያበረታታ ይኖራል፡፡ ከነዚህ አይነት ባህላዊ እሴቶች ውስጥ የዘፈንና ባህላዊ ውዝዋዜዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ውዝዋዜና ዘፈን በአብዛኛው አብረዉ የሚሄዱና የማይለያዩ ሆነዉ በየጊዜው ልሻሻሉና ልዘመኑ ይችላሉ፡፡

### ሀ. የመጫ ኦሮሞ/የወለጋ/ ባህላዊ ውዝዋዜ (ኤሞሌ)

ከወለጋ ዉዝዋዜ ታዋቂ ከሆኑት አንዱ ኤሞሌ ነዉ፡፡ ኤሞሌ ፍጥነት ያለዉ ዉዝዋዜ ሲሆን፣ ይህ በሆሮ ጉዱሩ ይታወቃል፡፡ የኤሞሌ አፈጻጸም በቡድን የሚከወን ሲሆን፤  እጅ፣ እግርና አንገትን ተቃራኒ በሆነ መልኩ ግራ እግር፣ ቀኝ እግርና አንገት በአንድ ጊዜ በአንድ አቅጣጫ ሲዞር በሚቀጥለዉ ዙር ደግሞ ቀኝ እግር፣ ግራ እጅና አንገት ተቃራኒ በሆነ (አቅጠጫ) ይዞራል ፡፡ በዚህ ሁኔታ ተወዛዋዦቹ አንገታቸዉን እርስ በራሳቸው ስር በማስገባት ይወዛወዛሉ፡፡



ስዕል 2.1. የኤሞሌ ውዝዋዜ

### ለ. የጉጂ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ሎሞላ/ ሳርብቻ

ይህ ባህላዊ ውዝዋዜ የሚታወቀው በጉጂ አከባቢ ወጣቶች ከሰዓት አከባቢ የሚጫወቱት ነው፡ ፡ አጨዋወቱም በቡድን በመሆን ሴቶችና ወንዶች ጥንድ በጥንድ በመሆን፤ አንገታቸዉን ወደ ግራ እና ቀኝ በማወዛወዝ፤ እንዲሁም ውዝዋዘውን ለማድመቅ ፊሽካ በመንፋት፣ብትር በመያዝ እናሶስት ጊዜ መሬት እየረገጡ ይጫወታሉ፡፡



ስዕል 2.2 ሎሞላ/ሳርብቻ ውዝዋዜ

### ሐ. የመጫ ኦሮሞ/ኢሉአባቦር/ ባህላዊ ውዝዋዜ (ትርትርሳ)

በኢሉ አባቦር የሚታወቅ ባህላዊ ውዝዋዜ ትርትርሳ ይባላል፡፡ ትርትርሳ ወንዶችና ሴቶች በቡድን በመሆን ይጫወታሉ፡፡ የትኩረቱ አፈጻጸም አንገትን በደምብ በማንቀሳቀስ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ሴቶች የባህል ልብሳቸዉን በመልበስ ትንሿን ድቤ ይዘዉ ይቀርባሉ፡፡ ወጣት ወንዶች ደግሞ፣ ቀጭን ሻሽ (ጨርቅ) ግንባራቸዉ ላይ በማሰር ጦራቸዉን መሬት ላይ አቁመዉ፣ ወደ ሴቶች አንገት ጠጋ በማለት አንገታቸዉን እያነቃነቁ ይጫወታሉ፡፡



ስዕል 2.3. የትርትርሳ ውዝዋዜ

### መ. የቱለማ ኦሮሞ/ሸዋ / ባህላዊ ውዝዋዜ እሸኬኬ

እሸኬኬ ታዋቂ የሸዋ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ ነዉ፡፡ እሸኬኬ ከረገዳ/ጭፈራ ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም፣ በአወዛወዝ ሁኔታ ልዩነት አላቸው፡፡ በአብዛኛዉ ጊዜ እየተቀባበሉ በሚዘፈኑ ዘፈኖች ላይ ለግጥሙ መሸጋገሪያ ይጠቀሙበታል፡፡ ከረገዳ/ጭፈራ የሚለየዉ እሸኬኬ በአንገት ወደ ላይ ቀና በማለት ጉልበትን በማጠፍና በመዘርጋት፣ እጃቸዉን በአንገታቸዉ ተቃራኒ ወደ ቀኝና ወደ ግራ በማነቃነቅ የሚወዛወዝ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ባህላዊ ውዝዋዜዎች ሲተገበር መልእክታቸው ተመሳሳይነት አለዉ፡፡ በተጨማሪም በሁለቱም "እሸኬኬ" የሚለዉን ቃል እንደ መነሻ ይጠቀሙበታል፡፡



ስዕል 2.4 የእሸከኬ ውዝዋዜ

### ሠ. የራያ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ (ጉቤ ሎሌ)

የራያ ኦሮሞ የሚያምርና የሚኮራበት የራሱ የሆነ የውዝዋዜ ባህል አለዉ፡፡ ይህም ውዝዋዜ "ጉቤ ሎሌ" ይባላል፡፡ ጉቤ ሎሌ በከፍተኛ ሞራል የሚወዛወዙበት የዉዝዋዜ አይነት ነዉ፡፡ የውዝዋዜዉ ሁኔታም ወጣቶች ዱላ በማንሳት በሁለት እግራቸዉ በትንሹ በመዝለል ሲወዛወዙ፣ ሴቶች ደግሞ ወንዶች ከሚዘሉት ሁኔታ በትንሹ በመዝለል አንገታቸዉን ወደ ግራና ወደ ቀኝ

በማነቃነቅ በቡድን ይጫወታሉ፡፡ የጉቤ ሎሌ ውዝዋዜ በጣም ፈጣንና ሰዉን ማነሳሳት የሚችል ነዉ፡፡



ስዕል 2.5. የጉቤ ሎሌ ውዝዋዜ

ረ. የከረዩ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ (ኤኢ.ያ)

የከረዩ ኦሮሞ ባህላቸዉን በውዝዋዜ ልዩ በሆነ ሁኔታ ይገልጻሉ፡፡ በከረዩ ኦሮሞ ዘንድ የሚታወቀዉ ባህላዊ ውዝዋዜ ኤኢ.ያ ይባላል፡፡ ኤኢ.ያ ወንዶችና ሴቶች ክብ በመስራት የሚጫወቱት ውዝዋዜ ነው፡፡ የኤኢ.ያ ውዝዋዜ ተሳታፊዎች ወንዶች ፀጉራቸዉን በማበጠር የባህል ልብሳቸዉን ለብሰዉ ይወጣሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ፀጉራቸዉን በማበጠር ይወጣሉ፡፡ በኤኢ.ያ ውዝዋዜ ቦታ ሴቶችና ወንዶች ክብ በመስራት ይቆማሉ፡፡ ሴቶች አንገታቸዉን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ማንቀሳቀስ ይጀምራሉ፡፡ የተወሰኑ ወንዶች ደግሞ በክቡ ውስጥ በመግባት ወደ ላይ በመዝለል ቁጥጥ እያሉ በክቡ መሃል ኤኢ.ያ በማለት ይወዛወዛሉ፡፡ ኤኢ.ያ በሰርግ ቦታና በተለያዩ በዓላት ላይ ይጫወታሉ፡፡



ስዕል 2.6 የኤኢያ ውዝዋዜ

ተግባር 4

1. በአከባቢያችሁ ያለዉን አንድ ባህላዊ ውዝዋዜ በመምረጥ በክፍል ውስጥ በተግባር አሳዩ፡፡
2. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን በሌሎች አከባቢ ካሉት ባህላዊ ዉዝዋዜዎች አንዱን በመምረጥ፣ በቡድን ከተመለማመዳችሁ በኋላ፣ በክፍል ውስጥ በተግባር አሳዩ፡፡
3. ከዚህ በላይ ያልተጠቀሰዉንና በሌሎች አካባቢዎች የሚታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በመዘርዘር፣ መቼ መቼ እንደሚተገበሩ ገለፁ፡፡

## ሰ. የአርሲ ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ (ቲሪ)

ቲሪ በአርሲ ኦሮሞ ከሚታወቁት ባህላዊ ዘፈኖች ውስጥ አንዱ ሲሆን በአርሲ እና በባሌ ዞኖች ይዘፈነል፡፡ ቲሪ ከሰርግ ዘፈን ዉስጥ አንዱ ሲሆን፣ በተለያዩ ጊዜያት የሚዘፈን ነዉ፡፡ ይህም በሰርግ ጊዜ ፣በሰርግ ዋዜማ ፣በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ እና በመኖሪያ ስፍራ/ቦታ ወጣቶች መዝፈን ይችላሉ፡፡



ስዕል 2.7. የቲሪ ውዝዋዜ

## ሸ. የቦረና ኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ (ዌዱ እና ቦሬ)

በቦረና ኦሮሞ አከባቢ ከሚታወቁ ውዝዋዜዎች ዌዱ እና ቦሬ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ዌዴ የሚ`ንለው ወንዶች ታዋቂ ሰው፣ከብቶቹን እና የሚያደንቀው ነገር ለማሞገስ የሚያዜሙ ሲሆን፤ ቦሬ ደግሞ ሴቶች በሰርግ እለት ለሙሽሪቷ ያላቸውን ክብር እና ፍቅር ለመግለፅ የሚያዘሙት እንዲሁም ተሰብስበዉ በመቀመጥ የሚጫወቱት የውዝዋዜ አይነት ነው፡፡



ስዕል 2.8. የዌዱ እና ቦሬ ውዝዋዜ

## 2.3 የትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን (ፈጠራ፣አጭር ታሪክ መፃፍና መመዘን)

**ተማሪዎች ብያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት፡**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣

- የትያትርና ፊልም ጥበብ ፕሮደክሽን ሂደት ትግልፃላችሁ፡፡
- አጭር የፈጠራታሪክ ለትያትርና ፊልም ጥበብ ትፅፋላችሁ፡፡
- የስነ-ጥበብ መተችያ መንገዶችን ትለያላችሁ፡፡

**መግቢያ**

በምዕራፍ አንድ ስለ ትያትርና ፊልም አላባውያን ተምራቸዋል፡፡ እንዲሁም በትወና ዉስጥ የምከናወኑ የተለያዩ ድርጊቶችን ተገንዝባቸዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የትምህርት ደግሞ ለትያትርና ፊልም ፕሮደክሽን ምን እንደሚያስፈልግና የዝግጅቱን ስልት የምትማሩ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለትያትርና ፍልም ጥበብ የአጭር ታሪክ ፈጠራ ስልትና ይዘቱን፣ የስነ-ጥበብ መተንተኛ መንገዶችን የሚትጎናፀፉ ይሆናል፡፡

**ተግባር 5**

1. ፈጠራ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የፈጠራ አይነቶች የሚባሉትን አስተውላችሁ ታዉቃላችሁ? አስተውላችሁ ከሆነ ስለ ፈጠራ አይነቶች በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች ግለፁ፡

### 2.3.1 ፈጠራ

ፈጠራ፣ የጥበብ ሥራ፤ትያትር፣ፊልም ጥበብ እና፣ሙዚቃ ብቻ የሚወስን ሳይሆን፤ በኢኮኖሚ፣ በምርት፣ በቴክኖሎጂ፣ በአስተዳደር፣ እና የመሳሰሉት ውስጥም ይገኛል፡፡

ተጨባጭ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎች፤ የስነ ጥበባት ሥራዎች፤ መፅሐፍት፣ ሙዚቃ፣ የክነ-ህንፃ ስራዎች፣ ማሽኖች ሲሆኑ፤ተጨባጭ ያልሆኑ የፈጠራ ስራዎች ደግሞ ሃሳብ፣ አገልግሎት፣ ዘዴ፣ ተረፈ ምርት እና ማከፋፈያን ያጠቃልላሉ፡፡

ስለዚህ ከላይ የተገለፁትን የፈጠራ ስራዎችን በማጠናከር፤ ለታለመ ግብ ማድረስ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም መሰረታዊ የሆኑ ነገሮች የጥበብ ባለሙያዎች ተነሳሽነት እና ለጥበብ ያላቸዉ ክብር ናቸው፡፡ በተጨማሪም በተለምዶ ያሉትን ነገሮችን ማዘመን እና ተጨባጭነ ጥበባዊ በሆነ መንገድ ነገሮችን መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ጥበባዊ ስራዎች የሚያምሩ የክነ ህንፃ ዲዛይኖች፣ የልብ ወለድ መፅሐፍቶች፤ ማሽኖች አስተዳደራዊ ስርዓት እና በሃገር ሰላም ጥበቃ ዘርፍ ግንዛቤዎችን ለማሳደግ ሊሆን ይችላል፡፡

የዘመናዊ ፈጠራ ታሪክ የተጀመረው በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን (1950 እ.አ.አ) ነበር፡፡ ምሁራን የፈጠራ ስራ በግለሰብ እድገት እና አኗኗር ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለዉ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ የፈጠራ ስራ በተማሪዎች ዘንድ ወደ ተጨባጭ የፈጠራ ስራ ክንውኖች በመለወጥ የፈጠራ ስራ ምዘና እና እድገት ክፍል ውስጥ የዉይይት ነጥብ መሆን አለበት፡፡ ይህም የፈጠራ ስራ አስፈላጊነትን በማነቃቃት፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰዉ ልጅ እድገት እና ስልጣኔ አካሄድን

ማስተዋወቅ ይቻላል፡፡ እነዚህም፡

1ኛ. አካሄድ/ የፈጠራ ሃሰብ

2ኛ. የሰዉዬዉ የፈጠራ ችሎታ

3ኛ. ከፈጠራዉ የተገኘ ውጤት

ስለዚህ ፈጠራ እንደ ምክንያትና ውጤት የሚወሰደዉ፤ በሰዎች ፈጠራ ችሎታ እና አካሄዳቸዉ ላይ በመመስረት ነዉ፡፡ በዚህ በሂደት የሚመጣዉ ችሎታ ደግሞ ውጤት ነው፡፡

ዘመናዊዉ የፈጠራ ታሪክ የተጀመረዉ በመካከለኛ 20ኛ ክፍለ ዘመን በ1950 ዓ.ም. ነዉ፡፡ የፈጠራ ችሎታን ወደ ንድፍ ሃሰብ ያመጡ ምሁራን ስለ ሰዉ ልጅ የሚፅፉ ፀሓፊዎችን ነበሩ፡ ፡ እነዚህ ምሁራን የፈጠራን አስፈለጊነትና በሰዉ ላይ በሚመጣው ለውጥና እንዲሁም በሰላም ውስጥ ተፅኖ እንዳለዉ የምናሉ፡፡ በዚሁ መሰረት በተማሪዎች ዘንድ ፈጣራ ወደ ተጨባጭ ለውጥ ተቀይሮ፣ የትምህርት አካል ለማድረግ የተነሳው ሃሳብ ተቀባይነት በማግኘት የውይይት አጀንዳ ሆነ፡፡ እንዲሁም የፈጠራ ሥራ አስፈላጊነቱ የማነቃቃት እና ግላዊ የእድገት ለዉጥ ለማስተዋወቅ መሆኑ ተቀባይነት አገኘ፡፡

ስለ ፈጠራ ስራ የመስኩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን የሚሰጡ ቢሆንም፤ በአጠቃላይ የፈጠራ ስራ ትርጉም ከሚከተሉት ሃሳቦች ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

- ፈጠራ ማለት ልዩ እና አዳዲስ ሃሳቦችን ወደ አዕምሯችን የሚያመጣ ነው፡፡
- ፈጠራ እንድ ሰዉ መሆን የሚፈልገዉን ነገር ሆኖ የሚገኝበት ነው፡፡ ይህም ሰዎች እራሳቸዉን የሚገልፁበት መንገድ ነው፡፡
- ፈጠራ ሰዎች ችሎታቸዉን የሚያሳዩበት ስራ ነው፡፡
- በሰዎች ዘንድ ሊታዩ የሚችሉ የችሎታ ደረጃዎች ልዩነት ስላላቸዉ በእዉቀት በመደገፍ ተጨባጭ የሆነዉን ነገር መፍጠር ነው፡፡
- ፈጠራ ሌሎች ሰዎችን የሚያነቃቃ እና ማስተማር የሚችልን ነገር ዉብ በሆነ ሁኔታ መስራት ነው፡፡
- ፈጣራ የተለመደዉን ነገር መሠረት በማድረግ አዳዲስ ነገርችን መፍጠር ነዉ፡፡ ይህም በጥበብ ስራዎች፤ ትያትር፣ ፊልም፣ስነ-ጥበብ፣ ግጥም፣ ቅርፃ ቅርፅ እና በፋሽን ዲዛይን መንፀባረቅ ይቻላል፡፡
- ፈጠራ ከተለመደ ውጪ በማሰብ እና ሃሳቦችን ተጨባጭ በማድረግ፤ እንዲታይ ወይም እንዲሰማ ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 2.3.2. አጭር ታሪክ ለትያትር ና ፊልም ጥበብ መፍጠር

በፊልምና ትያትር ጥበብ ዉስጥ የፈጠራ ችሎታዉ የሚጀመረዉ ሃሳብ መቀነበር መቻልና ከመፃፍ ነው፡፡ ማፃፍ ሲባል ትያትር ወይም ፊልም የሚሆን ፈጠራ ታሪክ ምፍፃበት መንገድ የስነ-ፅሑፍ ይዘት መኖሩ ነዉ፡፡ አንድ የፈጠራ ስነ-ፅሑፍ ሥራ ከይዘቱ የተነሳ ፈጠራ ሊባል ይችላል፡፡ የፊልም ጥበብ ሆነ የትያትር ጥበብ ዋናዉ መሰረቱ፤ ፃፊዉ አስቀድሞ በራሱ የፈጠረዉ ሃሳብ ሆኖ የተፈጠረው ሃሳብ ወደ

ፅሑፍ ይቀይራል፡፡ይህም የተፈለገው ሃሳብ በፅሑፍ መልክ የተፈለገዉን መልዕክት ማስተላለፍ እንድችል ማድረግ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ለጥበብ ስራ (ለትያትር ወይም ለፊልም) የሚፃፍ ፅሑፍ የተፈለገውን መልዕክት ለማስተላለፍ አስፈላጊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት፡፡

በዚሁ መሠረት አንድ ፅሁፍ ሦስት ዋናዋና ነጥቦችን በውስጡ መያዝ ይችላል፡፡

1ኛ፣ ለምን ጉዳይ እንደምፃፍ፣

2ኛ፣ የሚፃፍበት ዓላማ፣

3ኛ፣ ለማን እንደሚፃፍ፣ በተለይ እዚህ ዉስጥ ለሚፃፈዉ ተመልካችና ለተሰበበት የፅሑፉ አንባቢ አካል መሆኑ ነው፡፡ በአጠቃላይ አንድ ፅሑፍ ጉደይ፣ ዓላማ፣ አንባቢ፣ ተመልካች ይኖሯል ማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተገለፀው አንድ ለጥበብ ስራ የሚፃፍ ፅሑፍ የግድ በዚህ ረገድ በቂ ችሎታ የላው ፀሓፊ ይኖሯል፡፡በስነ ፅሑፍ የፈጠራ ስራ ውስጥ አንድ ፃሃፊ ችሎታዉን ለማሳደግ ከዚህ በታች የተገለፁትን ማወቅ አለበት፡፡

- ከፊልምና ትያትር በለሙያ ሃሳብ ለሙያዉ ቅርበት ካላቸዉ ሰዎች መቀበል፡፡
- የተለያዩ የትወና መፅሓፍቶችን ማንበብ፡፡
- ተስፋ ሳይቆርጡ በተደጋጋሚ መፃፍ- በዚሁ ነጥብ ሥር መረሳት የሌለበት ጉዳይ በፈጠራ ችሎታ ዉስጥ ጥንካሬና እምነት መኖር አለበት፡፡
- የምኖርበትን ማህበረሰብ በጥልቀት ማወቅ፡፡
- የተለያዩ ትያትርና ፊልምን ማየት እና ተዉኔቶችን ማንበብ ፡፡
- የራሱን ሥራ /ፈጠራ ከሌሎች ሰዎች ሥራ ጋር በማነፃፃር ማየት
- የማህበረሰብን ተጨባጭ የሆነ እውነታ ማወቅን በእውነታዉ ላይ ተንተርሶ መፃፍ አለበት፡ ፡
- ምናቦችን በማሳደግ መፃፍ፡፡
- የተሳሉትን ገፀ-ባህርያት በጥልቀት ማወቅ፣ ማጥናት- ይህ ማለት እየተፃፈ ያለው ጉዳይ ከማህበረሰብ፣ ባህል፣ አሴትና ከሃይማኖት ጉደይ ጋር ተያኸነት መኖሩን ማወቅ ነው፡፡
- ከግላዊ ስሜት ራሱን መቆጠብ አለበት፡፡
- ፀሃፊዉ በመስታወሻዉ ላይ የፃፈው እና ያገኘዉን መፃፍ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3.3 የአጭር ታሪክ ፈጠራ

ታሪክ የተዉኔት መሠረት ነው፡፡ አንድ ተዉኔት ታሪክ በመመስረት ይፃፋል፡፡አንድ ፀሃፊ ከመፃፍ በፊት ስለ ምን ታሪክ እንደሚፅፍ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ታሪኩ ምን እንደ ሆነ ከየት ተነስቶ የት እንደምቋጨ፣ ለወደፊት የት እንደምደርስ እንዲሁም ምን መሆን እንደ አለበት

ካወቀ በኋላ መፃፍ አለበት፡፡ የምፅፈዉ ይዘት ከጅምሩ እስከ ፍጻሜ ድረስ የምፈለገዉን የፈጠራ ስራ አላባውያን ለምሳሌ፡ መቼት፣ ሴራ፣ ወይም ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ፣ በገፀ-ባህርያት የሚፈፀመዉ ግጭት /ድርጊት በቅደም ተከተል/ ተመልምለዉ የሚፃፉ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ፡ከዚህ በታች የተሰጠዉን ታሪክ እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡

## የአናኔ ታሪክ

አናኔ ከአባቷ አቶ ገላና እና ከእናቷ ወይዘሮ ተሊሌ ምዕረብ ሸዋ ዞን አምቦ አከባቢ ተወለደች፡፡ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ በእንጅነሪንግ ትምህርት ዘርፍ የዘንድሮዉ ተመራቂ ናት፡፡ ቤተሰቦቿ በጣም በዝቅተኛ ኑሮ ስለምኖሩ ብዙ ጊዜ ልጃቸውን ከሰዎች ተበድረዉ ወደ ዩኒቨርሲቲ ይሸኛሉ፡፡ ልጃችን ትምርቷን ጨሪሳ ነገ ኑሯችን ትለውጣለች በማለት በጉጉትና በተስፋ ይጠብቁታል፡፡ በትምህርቷም ጎበዝ ተማሪ ስለሆነች ከቤተሰብ አልፋ ለሀገር ትበጃለች በምል ስሜት ተስፋ ተጥሎባታል፡፡

ትምህርቷን በጥሩ ሁኔታ እየተከታተለች ሳለ፣ ከሆነ ወንድ ልጅ ጋር ፍቅር ጀመረች፡፡ ትኩረቷ ከትምህርት ወደ ፍቀረኛ ላይ መጣል ጀመረች፡፡ በዚህ ሳለች በብዙ ኮርሶች ነጥቧ ስለ ወርዳ ለምረቃት ስነ-ሥረዓት ሳትበቃ ቀረች፡፡ ከዩኒቨርሲቲም ተባራረች፡፡ በቤተሰቧ በተስፋ ስለምጠባበቋት ወደ ቤተሰብ ለመመለስ በማፈር፣ በዩኒቨርሲቲው አከባቢ በቀን ሰራተኝነት የጉልበት ስራ ለመስራት ስትፈልግ፣ ለመስራት ነው ወይስ ትቀልዳለች ብለው አባረሯት፡፡ የቤት ሠራተኛ ሆና ተቀጥራ ለመስራትም ስት ፈልግ እንደ እሷ ያለ ሰው ለቤት ሰራተኝነት አትሆንመም፣ ለሌብነት መጥታ ይሆናል እንጂ ወይስ ሌላ ተልዕኮ አላት ብለዉ ሰድቧት አባረሯት ፡፡ በዚሁ መሠረት በመሸባት ቦታ አድራ በመካራና በራሃብ ከተፈታተነች ቦኋላ፣ ሆቴል ገብታ መስራ እንዳለባት በመወሰነች ሆትል ገባች፡፡ ነገር ግን የሆቴል ሥራ ስለማታቀው በየቀን ኪሳራ በራሷ ላይ እያስመዘገበች እንዲሁም እየተቆጧት ትሰራ ነበረ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሳለች የሆነው ልጅ የራራለት በማስመሰል በመቀራረብ ፍቅር ዉስጥ እዲትገባ አደርጋት፡፡ ከዛ በኋላ ይዟት ወደ ቤቱ መሄድ ጀመረ፡፡ ላንቺ እዚህ ቦታ አይመችሽም እኔ ብዙ ሀብት አለኝ ስለዚህ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከዚህ ትወጫለሽ ብለው በማባበል፣ ማታ ማታ ተከረይተዉ ወደሚኖሩበት ትንሿ ቤት ተያይዞዉ መግባት ጀመሩ፡፡ ይህ የኪራይ ቤት ነዉ፣ ሌላ እየሰረሁ ነው፣ እየሰራሁት ያለሁትን ቤት በእረፍትሽ ቀናት አሳይሻለዉ በማለት አባበላት፡፡ የሌላ ሰው ቤት የኔ ነዉ በማለት እየሳያት ሳለ በለቤቱ መጥቶባቸው ልጆች! ዱሪዬዉ ከዚህ ምን ይሰራል? ምን ልትሰሩ እዚህ መጣችሁ? በማለት ተናዶባቸው አበረራቸው፡፡ እሷም በጣም ተናዳ በማልቀስ ልጁን እዘዉ ጥላ ብቻዋን ሄደች፡፡ ከተወሰኑ ቀናት ቦኋለ በስልክ ጠርታ እንደፀነሰች ነገረችዉ፡፡ ከዚያ ቦኋለ የት አዉቅሻለዉ በማለት አበረራት፡፡ ሃኪም ቤት ሄዳ ፅንሷን ለማቋረጥ ስትጠይቃቿው ለመጫናገፍ እንደማትችል ተነገራት፡፡ ከዚያ ወደ ነበርችበት ሆቴል ተመልሳ ስትጠይቃቸው፣ ስትወጪ ምን አግኝተሽ ነው የወጣሽዉ ብለው ከለከሏት፡፡ ከዚያ በኋላ መፍትሄ ስታጣ በፀነሰች ሁኔታ መርዝ ገዝታ ወደ ቤተሰቧ ሄዳ ሰላም ከለቻቸው ቦኋለ አብራቸው ስትጨወት ቆይታ በእኩለ ሌሊት አከባቢ መርዝ ጠጣች፡፡

ይህ የፈጠራ ታሪክ ወደ ተዉኔት ትያትር ሲቀየር እንደሚከተለዉ ይሆናል፡፡

### ትዕይንት አንድ

(ቦታዉ ምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ 01 ቀበሌ በአቶ ገላና ቤት ዉስጥ ነው፡፡ የወፎች ድምፅ

የንጋት ምልክት ከመድረክ ይሰማል፡፡ ወይዘሮ ተሊሌ በጧት ተነስተው በር ከፍተዉ አቶ ገላናን ይቀስቅሳሉ፡፡ የሚከፈት የበር ድምፅ ይሰሟል፡፡)

ወ/ሮ ተሊሌ : ወይ አቶ ገላና ! እንደነጋ አላወቁም ወይስ እስከ ስንት ሳዓት ይተኛሉ? አይሰማም?

የአናኔ አባት: እም….(ከእንቅልፍ ባልነቃ ስሜት )

ወ/ሮ ተሊሌ: እባከዎ ተነሱ! ያችህ ልጅም እየጠበቀችን ነው! ተነሱና ሂዱ! እሷም ከኛ ውጭ ማን አላት?

የአናኔ አባት፡(በማዛጋት) እ…ከመቼው ነው የነጋው? እኔ የምለዉ ይህ ቀን ይሮጣል? ይህ ቀን ይሮጣል…ምንም አናይም…የት ልወስደን ነው? እስኪ ጋቢውን ስጭኝ.. አምላኳ ይርዳኝ እንጂ! ሁሉም ሰው አወቀኝ …የሰው ፊት ማየትም ከበደኝ (ረጅም ትንፋሽ ተነፈሱ)

ወ/ሮ ተሊሌ: የገላኔ አባት! ታገስ! የዘንድሮ ዓመት ብቻ ቀረን! ዘመን የምሮጥበትም ለጥሩ ነገር ልያሳጣን ነው…ልንወጣም ነው .. እሷ በሳላም አጠናቃ ትምጣ እንጂ ከዚያ በኋላ የሰው ቤት ላይ መዞርህ ይቆማል! እያዘንክ አትሂድ! ይሳካልሃል! የአናኔ አባት!

የአናኔ አባት: (የከብቶች ድምፅ ይሰማል) እንደ ቃልሽ ይሁን! እኔ እስከምመጣ ድረስ ይህችን ከብት አውጪና ሣር አስቀምጭላት..በጧት መጮይ ጀመረች! ጨለማና ብርሃን ሳይለይ መጮይ ጀመረች!(ወጥተው ሄዷል)

ወ/ሮ ተሊሌ: (ከበቶችን ከእስር ፈቱ) ተዉ..ተዉ….ይህ ከብት ደግሞ ! ሁለት ቢሆኑ እንዴት ይሆኑ ነበር ? ከዞረብህማ ከበትና ሰው አይለይም! ብላ… (የሳር ድምፅ ይሰማል)…ለነገሩ ይህቺ ላም ከእንግዲህ ወደ ሁለት፣ ከሁለት ወደ ሦስት፣ ከሶስት ወደ አራት እንዲሁም ወይፈን ተጨማምሮበት ማደሪያቸዉን ስሞሉ ኑሮው ይመጣል፡፡ "እንደዱሮ እና በቆሸሸ እጅ አይቀሩም እንደሚባል" አባባል!

## ትዕይንት ሁለት

(ከመድረክ የሰው እግር ድምፅ ይሰማል፡፡ አቶ ገላና እንደተናገሩት የውሻ ድምፅ መስማት ጀመረ፡፡)

አቶ ገላና: ቤቶች! ቤቶች ! (ውሻ ትጮይባቿለች)

አቶ ዋቅጋሪ : አቤት…ማን ልበል? ይህች ውሻ ደግሞ ምን ትጮሃለች! ተዉ! ሂድ አት ሄድም? ይግቡ (አቶ ዋቅጋሪ በመቀበል)

አቶ ገላና: በእግዜር! ሰላም ናችው ? (አክሊላቸዉን አንስተው)

አቶ ዋቅጋሪ: እንዴ ! አቶ ገላና አንተ ነህ ለካ ! እንዴት ነው ? ይግቡ …ግቡ!(በለሰለሳ ድምፅ)

አቶ ገላና: እኔ አቶ ዋቅጋሪ ነኝ ! ታዲያ እንዴት ነው? ቤተሰብ ሁሉ ሰለም ናቸው?

አቶ ዋቅጋሪ: እግዝአብሄር ይመስገን ክብሩ ይስፋ! ሰላም ነን! ልጆቻቹስ እንዴት ናቸዉ?

አቶ ገላና: ሰላም ነዉ ! ሰላም ነው! ዛሬ ደርሰናል! አንድ ሁለት እያለን ነው!

አቶ ዋቅጋሪ: እባከዎትን ይግቡ ዉጭ ቆሙ?

አቶ ገላና:: ችግር የለም ጧትም............

## 2.3.4 ሂስ

ሂስ ማለት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዋና አጀንዳ በጥልቀት የሚካሄድ ፍቺ የሚሰጥ፣ የሚገመግም፣ማብራሪያ የሚሰጥ ፣ውሳኔ፣የሙስና ሀሳብ እንዲንጣራ የሚያግዘን በስልት የተሟላ የጥበብ ዘርፍ ሆኖ ስለ መቼት ትርጉም ሰፊና መልካም እድል ለህያሲያን ይሰጣል፡፡ የስነ-ፅሑፍ ሂስ ስራ የአንድ ሰው የስነ-ፅሁፍ ምርምር ስሆን፤ የመልካም አመለካከትና ከፉኛ አመለካከት ይዘት ያለው ጥበብ ነው፡፡

ሂስ ማላት የጥበብ ስራ የምንገልፅበትና የሚገመገምበት የስልት ዓይነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ሂስ ሳይንሳዊ የሆነ ምርምር በስነ-ፅሁፍና ስነ-ጥበብ ላይ የሚከናወንበት ስልት ነው፡፡

ሂስ የስነ-ጥበብ ስራዎች ላይ የውይይት አጀንዳን የምቀርፅ እንዲሁም የስራው መልካምነት ላይ ዉሳኔ መስጠት እና የስራው ደከማ ጎን የምገልፅበት መንገድ ነው፡፡

ለማኛውም ሂስ የሚከተለውን የራሱ ዘዴ አለው፡፡

እውቀት + መረዳት/ማስተዋል = ትርጉም ያለው ውሳኔ/ሂስ

እዚህ ውስጥ መታወቅ የሚገባ ነገር ቢኖር ሂስ ትርጉም ያለው ውሳኔ መሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም ሂስ በእዉቀትና መረዳት/ማስተዋል ላይ ተንተርሰዉ የምከነወን ከሆነ ትርጉም ያለው ይሆናል፡፡

ስለዚህ ሂስ እንደ ሌሎች ጥበብ  እውቀትና ሙያ ባለው በባለሙያዉ መከናወን አለበት፡፡ የመተቻት ችሎታ ያለቸው ሰዎች እውቀታቸውና ግንዛቤያቸው ተያዥነት አሏቸው፡፡

## የስነ-ጥበብ ሂስ ይዘቶች

በዚህ ርዕስ ትምህርት ሥር የሚንመለከተው የስነ-ጥበብ ሥራ መመዘኛ መንገዶች/ሂስ መስጫ ስልቶችን ነው፡፡ የማንኛዉም የጥበብ ሥራ ተሰርቶ ከማህበረሰብ ዘንድ ከደረሰ ቦኋለ  የምታየዉ ታይቶ የምነበብ ተነቦ፤ ከተማረበትና ከተዝናነበት ቦኋለ በስራው ጥንካሬና  ደካማ ጎን ላይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ በግለሰብ ደረጃና በቡድን ደረጃ መስጠት ይቻላል፡፡ ሰዎች ሂስ ስሰጡ በተረዱና በተገነዘቡበት መንገድ ብሰጡም ነገርግን የጥብበ ስራ ለመተቻት የራሱ ይዘትና ስልት አለው፡፡ ሂስ ማለት የጥበብ ሥራ ደካማ ጎኑ ብቻ መተቻት ሳይሆን፤ ጥንካሬውንም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ የስነ-ጥበብ  ሥራ ሂስ  የራሱ ሂደት አለው፡፡

### ሀ. ማብራሪያ

በሂስ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ መታወቅ ያለባቸው መሠረታዊ ነገሮች አሉ፡፡

እነዚህም፣

- የስራው ርዕስ

- የፀሃፊው ስም
- የተፃፈበት ቀን
- የዕትም ቦታ ...ይህንን ስንፈፅም በትክክለኛ መረጃና ተዓማንነት መሆን አለበት፡፡

## ለ. ትንታኔ

ትንታኔ ውስጥ መታየት ያለበት የጥበብ ሥራው በተቀነጀበት መንገድ ነዉ፡፡ የሥራው አወቃቀር ስልት እንዲሁም መጠቀም ያለበት አላባዊያንና መከተል የለበት ደንቦች ተጠቅሟል ወይ የሚል ያካትታል፡፡ የጥበብ ሥራ ሁሉ የራሱ ዘርፍ አለው፡፡

ለምሳሌ፡ ፊልም ጥበብ፣ ድራማ፣ ትያትርና ሌሎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

## ሐ. ትርጉም/ፍቺ መስጠት

ከአንደኛና ከሁለተኛ ያገኘነዉን መረጃ ላይ በመመስረት ፃሃፊው ማስተላላፍ የፈለገውን ነገር መረዳት የኛ ግኝት የሚነገረዉን በማስተዋል መግለፅ መቻል ነው፡፡

## መ. ውሳኔ

ይህ ቦታ የጥበብ ስራ ጥንካሬን የምንገመግመበት፣ ደካማ ጎኑን የምንፈትሽ፣ የስራው ውበት ላይ የራሳችንን ሃሰብ የምንሰጥበት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የአንድን ሰው ሥራ መውደድ ወይም መጥላት ሳይሆን፤ እውነትና የሂስ ሳይንስ መጠቀም ነው፡፡

## 2.4 የህትመት እና ቅርፃ ቅርፅ ስራ (የሸክላ አፈር፣ፔፐር ማሼ)

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች፡

- የግራፊክስ ትምህርት ምንነት ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የፔፐር ማሼ ስራ ሂደት ትለያላችሁ፡፡
- የሸክላ ስራ ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡

### 2.4.1 ህትመት

በአሁኑ ጊዜ የህትመት ስራ በሰው ልጅ አኗኗር ጋር ተያይዘዉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ፤ የሰው ልጅ የእለት እለት ፍላጎት እና ምኞት እያሟላ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ ከጥንት ጊዜ ጀምረዉ እስከ ዛሬ ያለዉ የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታ የአሰራር ዘዴዉ ልዩነት ቢኖረዉም፤ ሲሰራ እና እየተሰራ ከለዉ ውስጥ የልብስ ዲዛይን፣ወረቀት በመቆራረጥ የሚሰሩ ህትመት፣ ስክራች እና የመሳሰሉት በዚህ ትምህርት ክፍል የምትማሩ ይሆናል፡፡ እናዲሁም ለዚህ ህትመት አይነት የሚያገለግል መሳሪያ እና የአሰራር ዘዴዎችን በዚህ ርዕስ ግንዛቤ የሚታገኙ ይሆናል፡፡

#### 2.4.1.1. የልብስ ዲዛይን



ስዕል 2.9. የልብስ ዲዛይን

የልብስ ዲዛይን ማለት በሚንሰራ ልብስ ላይ የተፈጥሮ ፎርም/ቅርፅ ወይም ሰው ሰራሽ ሆኑትን በማቀናጀት እና በማሳመር መስራት፤ ልብስ ሳይመረት በፊት እንድያምር እና ሰው እንድስብ በልብስ ላይ የሚሰራ ዲዛይን ማለት ነው፡፡ የልብስ ዲዛይን የሚሰራ ሰው ባለዉ ችሎታ በመጠቀም፤ ለባህላዊ ወይም በዘመናዊ መልክ መስራት ይችላል፡፡ የልብስ ዲዛይን ሲሰራ፤ ቀላል ወይም ዉስብስብ በሆነ ጥልፍ (ፓተርን) ልሰራ ይችላል፡፡ የተለያዩ በሚያምሩ ቅርፅ ወይም ፎርም ይሰራል፡፡

ይህ የልብስ ዲዛይን በጣም ተፈላጊ እና ጥበባዊ ጌጥ ያለዉ ነው፡፡ በጥንት ጊዜ የሰው ልጅ የተለያዩ ጥልፍ በመስራት ሲገለገልበት እንደነበር ጣሪክ ያስረዳል፡፡ጥልፍ ያለዉ ልብስ በእጅ መሰራት የጀመረዉ ከጥጥ ነው፡፡



ሥዕል 2.10 በተለያዩ አይነት የተሰራ የልብስ ዲዛይን

የልብስ ዲዛይን በተለያየ ዘዴዎች ሊሰራ ይችላል፡፡ እነርሱም፡-

1. ልብስ በመንከር እና
2. ልብስ በመጥለፍ

## 1. ቀለም ውስጥ በመንከር የሚሰራ የህትመት ዘዴ

አንዳንድ የታሪክ መፅሓፍት እንደሚገልፁት ልብስ ቀለም ውስጥ የመንከር ጥበብ በግብፅ፣ፔሩ እና በሰሜን ህንድ እንደተጀመታሪክ ይናገራል፡፡ ይህ ጥበብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ አከባቢ በመስፋፋት፤ በአሁን ጊዜ በአለም ከፍተኛ እድገት እያሳየ ያለ ጥበብ ነው፡፡ በተለይ በምጣኔ ሃብት ያደጉት ሃገራት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየሰሩ መሆናቸው እና ብዙ ገቢ እያገኙበት ያለዉ የጥበብ ስራ ነው፡፡ ቀለም ውስጥ የመንከር አሰራር የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. አስረዉ ወይም ጠቅልለዉ መንከር  እና

ለ. በሰፊፍ መንከር (የባቲክ ዘዴ) ናቸው፡፡

## ሀ. አስረዉ ወይም ጠቅልለዉ የመንከር ዘዴ

### ተግባር.6

በአከባቢያችሁ ስንደዶ/ሰርዶ አስረዉ በቀለም ስነክሩ አይታችሁ ታዉቃላችሁ? አይታችሁ የሚታዉቁ ከሆነ እንዴት እንደሚነከር በቡድን በመወያየት ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡.

ይህ ጥበብ በቀላል ዘዴ የተለያየ ዲዛይንእንዲሰራ አጣጥፈዉ በማሰር የሚሰራ ነው፡፡

የሚከተለዉን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡



ሥዕል 2.11. አስረዉ ወይም ጠቅልለዉ የመንከር ዘዴ

## ሀ. ለስራዉ የሚያስፈልጉ ነገሮች



Halluuwwan adda addaa



Meesha bal'aa huccuun keessatti cuuphamu



Waan ittin hidhamu kan akka funyoo



Uffata adda addaa



Saamunaa



Soogidda



Soodiyeem baayikaarboneetii

### ለ. አስረዉ ወይም ጠቅልለዉ የመንከር ዘዴ



- ሳይነከሩ በፊት የሚነከር ልብስ በዉኃ እና በሳሙና ማጠብ፡፡
- የታጠበዉን ልብስ ሳይደርቅ ልንሰራዉ በፈለግነው ዲዛይን በማጠፍ ማሰር፡፡
- በፈላ ዉኃ ቀለም መበጥበጥ፡፡
- ታስረዉ የተዘጋጀዉን ልብስ በተበጠበጠ ቀለም ውስጥ ማንከር፡፡
- ልብሱ ከተነከረ በኋላ በፈላ ዉኃ እንፋሎት መቀቀል፡፡
- ጨዉ እና ሶዲዬም ባይካርቦኔት በቀዝቃዛ ዉኃ መበጥበጥ፡፡ ይህም በአምስት ሊትር (5ሊ) ዉኃ አምስት መቶ ግራም (500ግ) ጨዉ እና አንድ መቶ ሃምሳ ግራም (150ግ) ሶዲዬም ባይካርቦኔት ማዘጋጀት፡፡
- ይህ ታስረዉ የተነከሬ ልብስ ዉኃ፣ ጨዉ እና ሶዲዬም ባይካርቦኔት ለአራት ሰዓት በመንከር ማቆየት፡፡
- ልብሱ ተነክረዉ ከወጣ በኋላ በዉኃ እና ሳሙና በማጠብ ጥላ በለበት ቦታ ማሳጣት፡፡
- ልብሱ በደንብ ሳይደርቅ በሞቀ ካዉያ መቶከስ፡፡.
- በመጨረሻም የተነከረዉን ልብስ ለተለያየ አገልግሎት ማዋለው፡፡

በተለያዩ ቀለማት መንከር አስፈላጊ ሆነው ከተገኘ፣ በፊት የተነከረዉን ልብስ በእንፋሎት ሳይቀቀል፣ ከበፊቱ በተለየ ቀለም አስረዉ ንጣት ካላቸዉ ቀለም ወደ ደብዛዛ ቀለም መንከር ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ፡-አንድን ልብስ በቢጫ እና ቀይ ቀለም ውስጥ መንከር ከፈለግን፣ በመጀመሪያ በቢጫ ቀለም ውስጥ መንከር ይኖርብናል፡፡ በመቀጠል ደግሞ በቀይ ቀለም ውስጥ እንነክራለን፡፡

እንድን ልብስ ከመንከራችን በፊት በደንብ መታሰሩን ማረጋገጥ አለብን፡፡

## ለ. ሰም በማቅለጥ (የባቲክ ዘዴ)



ሥዕል 2.12 ሰም በማቅለጥ (የባቲክ ዘዴን)የምያሰይ ሥዕል

የባቲክ ጥበብ ሙያ የተጀመረዉ በግብጽ ሀገር ቢሆንም፤ ወደ ቦኋላ ላይ በፔሪሺያ እና በህንድ ተስፋፍቷል፡፡ በአሁን ጊዜ በተለያዩ በአለም ሃገራት መስፋፋቱን ፅሁፎች ያስረዳሉ፡፡ የዚህ ስራ ዘዴ የቀለጠ ሻማ እና ሰፈፍ ልብስ ላይ በማፍሰስ፤ የተለያዩ ዲዛይኖች ይሰራበታል፡፡ ይህም የተንጠባጠበበት ቦታ ቀለም እንዳይነካ ያገለግላል፡፡

### 1. ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

- ልብስ
- ሰፈፍ ወይም ሻማ
- ሰፈፍ ወይም ሻማ የሚቀልጥበት እቃ፡፡
- የተለያዩ ብሩሾች (ትልቅ እና ትንሽ)
- ቀለም
- ትልቅ ሳሃን ወይም ባልዲ
- ጋዜጣ
- ካዉያ
- ጠረጴዛ
- ልብስ የሚሳጣበት ሽቦ እና ልብስ ማስያዣ፡፡

### 2. የባቲክ ስራ አሰራር

- በመጀመርያ ለዚህ ስራ የሚሆን ልብስ ማዘጋጀት፡፡,
- ለመንከር የሚመች ልብስ በሳሙና በደንብ ማጠብ፡፡
- የታጠበዉን ልብስ በፀሀይ እንዲደርቅ ማድረግ፡፡ ከደረቀ በኋላ በካዉያ መቶከስ፡፡
- የተዘጋጀዉን ልብስ በጠረጴዛ ወይም ዝርግ በሆነ ነገር ላይ መዘርጋት፡፡
- የሚያስፈልገዉን ዲዛይን በእርሳስ መንደፍ፤ የተነደፈዉን ንድፍ ካርቦን በመጠቀም በልብስ ላይ መገልበጥ፡፡ ለምሳሌ፡-አበባ፣ወፍ፣የዛፍ ፍሬ፣ቢራብሮ፣አሣ፣ የተለያዩ ቅጠሎች እና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት በልብስ ላይ መንደፍ፡፡ ,
- የተፈለገዉ ዲዛይን ከተሰራ በኋላ፤ የቀለጤ ሻማ ወይም ሰፈፍ የተሰራዉን ንድፍ

በመከተል መቀባት/ማፍሰስ፡፡

- ያፈሰስነው ሻማ/ሰፈፍ ከደረቀ በኋላ፣ የልብሱን መልክ የማይመስል ቀለም መቀባት ወይም መንከር፡፡
- የተቀባ ቀለም እንዲደርቅ ማድረግ፡፡,
- በልብስ ላይ ቀለም ከደረቀ በኋላ ሻማ የተቀባዉን ቦታ ሙቅ በሆነ ነገር ቀልጠዉ እንዲለቅ በማድረግ፣ ውይም ስለት በለዉ ነገር ማስለቀቅ፡፡,
- ይህ ልብስ የሚለብሱት ከሆነ፣ ለረጅም ጊዜ ቀለም ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ፡፡
- በቀለም የተነከረዉ ልብስ ከቀለም ውስጥ ካወጣን በኋላ፣ በዉኃ የተበጠበጠ ጨዉ እና በሶዲዬም ባይካርቦኔት ለአራት ሰዓት ማቆየት፡፡,
- በጠረጴዛ ላይ መዘርጋት፡፡,
- የተነጠፈ ልብስ ለይ የተነከረዉ ልብስ በመዘርጋት ማሳጣት፡፡
- የተሳጣ ልብስ ላይ ሌላ ጨርቅ በማንጠፍ በካዉያ መቶከስ፡፡

በአጠቃላይ የልብስ ዲዛይን ሲሰራ፣ ማወቅ ያለብን ነገር የሚንሰራ ነገር መለየት፡፡ ይህም ሲሰራ ባህላዊ እና ዘመናዊ መሆኑን መለየት፡፡ ይህ ካልሆነ የሚሰራ ነገር ዋጋቢስ ይሆናል፡፡

## 2. ልብስ መጥለፍ/ጥልፍ መስራት

**ተግባር. 7**

በአከባቢያችሁ በወተት ቅል/ጮጮ ላይ የሚሰራ ዲዛይን አይተህ ታዉቃለህ/ሽ? አይታችሁ የሚታዉቁ ከሆነ በክፍል ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡



ሥዕል 2.13 ልብስ ለይ መጥለፍ/ጥልፍን የምያሰይ ሥዕል

መጥለፍ/ጥልፍ መስራት ማለት የእጅ ሙያ ሆኖ፣ የስፌት መርፌ እና የተለያዩ ቀለማት ያለዉ ክር በመጠቀም ልብስ፣ምንጣፍ፣ስፌት እና የመሳሰሉት ላይ ዲዛይን በመጥለፍ የሚሰራ ነው፡፡ ይህ ሙያ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በእንጨት፣በሣር እና የመሳሰሉት ነገሮችን በመጠቀም ስርዓተ ጥለት ሲሰሩ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ይህ ሙያ ትልቅ ቦታ ደርሰው በሲንጀር/ልብስ የሚሰፋ መኪና

በመጠቀም ሰውን የሚማርክ እና ዉብ የሆነ ዲዛይን በተለያዩ ክር በመጠቀም እየተሰራ ነው፡ ፡እንደ ምሳሌ በዚህ ሙያ የሚሰሩ ነገሮች የተለያዩ መጋረጃዎች፣አልጋ ልብስ፣ምንጣፍ፣የሶፋ ጨርቅ እና የመሳሰሉት እያስዋቡ ይገኛሉ፡፡.

## 2.4.1. 2 ወረቀት በመቆራረጥ የሚሰሩ የህትመት ስራዎች /paper cut print/

ወረቀት ቆርጠዉ በማዉጣት የሚሰራ የህትመት ስራ ማለት በወረቀት ላይ አስፈላጊ ዲዛይን ከተነደፈ በኋላ ጥቁር እንክ/ቀለም በመቀባት፣የቀረዉን ቦታ ደግሞ ቆርጠዉ በማዉጣት የሚሰራ ስራ ነው፡፡ ይህ ዘዴ እንጨት ላይ ለሚሰሩ ለህትመት ስራ እንደመነሻ ያገለግላል፡፡

ወረቀት ከእንጨት ይልቅ ቀላል ስስ ስለሆነ በቀላሉ እንደፈለግነው መቁረጥ መስራት እንችላለን፡ ፡ ይህ ማለት እንድ ሰው ወረቀት የመቆራረጥ ሙያ ካለዉ እንጨት በማጎድጎድ እን በመላግ ዲዛይኖችን መስራት ይችላ ማለት ነው፡፡.

ማንኛዉም ትምህርት ከቀላል ወደ ወስብስብ እንደሚሄድ የታወቀ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ስራ ከሌሎች ልዩ የሚያደርገዉ፣ ዲዛይን ከተሰራ በኋላ ብርሃን እና ጥላ በመስራት ጥላ ባለበት ሁሉም ቦታ ዲዛይኑ በተሰራበት ላይ በመተዉ፣ ብርሃን ያርፍበታል ብለን ያሰብነውን ደግሞ ተቆርጠዉ ከወጣ በኋላ ጥቁር ቀለም በመቀባት፣ በሙጫ/ማጣበቂያ ጥቁር ነገር ላይ በማጣበቅ የሚሰራ ስራ ነው፡፡

ይህ የህትመት አሰራር ወረቀት በመቆራረጥ /paper cut print የሚሰራ ስራ ይባላል፡፡/





ሥዕል 2.14ሀ ወረቀት በመቆራረጥ የተሰራ የህትመት ስራ

1. ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች
   - ዲዛይን የሚሰራበት ወረቀት
   - የሚለጠፍበት ወፍራም ወረቀት
   - እርሳስ
   - መቅረጫ

- ላጵስ
- መቁረጫ
- ኮላ ወይም ማጣበቂያ
- ጥቁር ቀለም /Ink/
- ብሩሽ/መቀቢያ

## 2. የስራዉ ሂደት

- በወረቀት ላይ ንድፍ ወይም ስዕል መሳል፡፡
- የተሳለዉን ስዕል በስርዓት ብርሃን እና ጥላ መስራት፡፡
- ሥዕሉን ለመለጠፍ የተዘጋጀዉን ወፍራም ወረቀት ጥቁር ቀለም በመቀባት ማድረቅ፡፡ ወይም በተዘጋጀዉ ዲዛይን ላይ ጥላ ያለበት ቦታ ቀለም በመቀባት ቆርጠዉ በማዉጣት መለጠፍ፡፡
- የብርሃን እና ጥላ ቦታ በመለየት ብርሃን ያለበት ቦታ ቆርጠዉ ማዉጣት፡፡
- ከቆረጥን በኋላ ወረቀት ስስ ስለሆነ እንዳይጨማደድ በጥንቃቄ ኮላ/ማጣበቂያ መቀባት፡፡
- የተቀባዉ ማጣበቂያ ሳይደርቅ ቶሎ ብለን መለጠፍ ነው፡፡

የሚከተለዉን ምሳሌ ተመልከቱ፡-.



ሥዕል 2.14ለ ወረቀት በመቆራረጥ የተሰራ የህትመት ስራ

### ልምምድ 1

ከላይ የተገለፁት ወረቀት በመቁረጥ የሚሰራ የህትመት ዘዴ አሰራር ላይ በመመስረት ከታች ያለዉን ህትመት አስመስላችሁ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡



ሥዕል 2.14ሐ ወረቀት በመቆራረጥ የተሰራ የህትመት ስራ

### 2.4.1.3 ስክራች / Scratch/

ስክራች የህትመት ዘዴ አይደለም፡፡ ግን ከግራፍክስ ስራዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነ፤ በዚህ ዘዴ በመጠቀም የግራፍክስ ትምህርት ማስተማር ይቻላል፡፡የስክራች ስራ ጥቁር ቀለም /ink/ብቻ ስለሚንጨምር ነው እንጂ በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮች ሻማ፣የልብስ ሳሙና፣ጥቁር ቀለም እና መርፌ/ ስለት ያለዉ ነገር/ በመጠቀም መስራት ይቻላል፡፡ይህ ዘዴ ከግራፍክስ ስራዎች ውስጥ ቀላል የሆነ እና ብርሃን እና ጥላ በመጠቀም የሚሰራ ስራ ነው፡፡

ይህ የስክራች ሙያ ቀላል የሆነ ስራ እና ማንኛዉም ሰው የሚሰራ ሆኖ፤ አሰራሩ ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ስራ ነው፡፡ ምክንያቱም ከተሳሳትን ተመልሰን ለመስራት ወይም ለማስተካከል እስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ስራ ቀላል ስለሆነ እንጨት ተፍቀዉ ከሚሰሩት ስራዎች ቀድመዉ ይታያል፡፡ ይህም በነጭ እና ጥቁር ብቻ የተለያዩ ቶኖች ቫሊዩ መሰራት መቻሉ ነው፡፡

#### 1. ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮች:

- ወፍራም እና ጠንካራ ወረቀት፡፡
- ሳሙና
- ዉኃ
- ሻማ
- የቀለም ብሩሽ
- ጥቁር ቀለም / Ink/
- ስለት ያለዉ ነገር መርፌ እና የመሳሰሉት መጠቀም እንችላለን፡፡

## 1. የአሰራር ሂደት

- የተዘጋጀዉ ወፍራም እና ጠንካራ ወረቀት ዝርግ በሆነ ነገር ላይ በማስቀመጥ እንዳይጎብጥ ማድረግ፡፡
- የተዘረጋ ወፍራም ወረቀት ላይ ሻማ በማሸት መቀባት፡፡
- የተቀባ ሻማ ላይ በብሩሽ ፈሳሽ ሳሙና መቀባት፡፡
- እስክደርቅ በትዕግስት መጠበቅ፡፡
- በደንብ ከደረቀ በኋላ ጥቁር ቀለም በብሩሽ መቀባት፡፡
- የተቀባ ቀለምበደንብ ከደረቀ በኋላ፣ በመርፌ ቀስ ብለን የፈለግነውን ንድፍ መንደፍ፡፡,
- የብርሃን እና ጥላ አቅጣጫ በመለየት፣ ብርሃን መስለዉ የሚታየዉን አቅጣጫ በደንብ መፋቅ፡፡
- ጥላ ያለበት አቅጣጫ አስፈላጊ ከሆነ በስተ ጀርባዉን በማላቀቅ ወይም በቶሪ መስመር መስራት ነው፡፡

ይህንኑ ከሚከተለዉ ስዕል መረዳት ስለሚትችሉ ተመልከቱ፡፡






ሥዕል 2.15ሀ በስክራች የተሰራ ስራን የምያሰይ ሥዕል

**መልመጃ 2**

ከላይ በተገለፀዉ የስክራች አሰራር ላይ በመመስረት፣ የሚከተለዉን ሥዕል በማስመሰል ስሩና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ



ለ



ሥዕል 2.15ለ በስክራች የተሰራ ስራን የምያሰይ ሥዕል

## 2.4.2. የቅርፃ ቅርፅ ትርጉም

ቅርፃ ቅርጽ ከስነ-ጥበብ ስራዎች አንዱ ሆኖ ቁመት፣ወርድ እና ርዝመት ያለዉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የቀለም ቅብ እና ንድፍ ከሚሰሩ የስነ-ጥበብ ስራዎች አሰራር ለመለየት ያገለግላል፡፡

### 2.4.2.1 የሸክላ ጥበብ ስራ

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሰው ልጅ የተለያዩ ነገሮችን በመስራት ሲገለገልበት ነበር፡፡ ለጊዜዊ ጥቅም ብቻ ነበር፡፡ በተለይ ለአደን የሚጠቀሙበት እና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር የሚያስቸግር መሳሪያዎች አብዛኛዉ ጊዜ አይጠቀሙበትም ነበር፡፡ እንስሳትን በማላመድ ኑሯአቸዉን ወደ እርባታ ለመቀየር ባሰቡበት ጊዜም፣ ዉኃ እና ሣር እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ምክንያት ሲያጋጥማቸዉ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚዘዋወሩ በአደን ጊዜ ህይወታቸዉን እንደሚመሩ ሁሉ ቀለል ባሉ ቁሳቁሶችን ይጠቀሙ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ የሰው ልጅ ተረጋግቶ አንድ ቦታ መኖር ከጀመረ ወዲህ የሸክላ ስራ ሙያ እንደተጀመረ ታሪክ ያስረዳል፡፡.

የሸክላ ጥበብ ስራ የቆየ ሲሆን የሰው ልጅ በተለያየ ቦታዎች ሲጠቀሙበት ከነበሩት አንዱ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከሸክላ ስራ እንስራ፣ዶሎ እና የተለያዩት በመስራት ዉኃ ስቀዳበት ነበር፡፡ከወንዝ የሚቀዱ ዉኃ የሸክላ አፈር ስላለበት ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚቀዳበት እንስራ ከስር እየተጠለለ የእንስራ ፎርም ይይዛል፡፡ በሂደት ዉስጥስደርቅ የሰው ልጅ የሸክላ አፈር እንደ እንስራ ዉኃ መያዝ እንደሚችል ተረዱ፡፡

ከዚህ ሃሳብ በመነሳት፣የሸክላ አፈር ወንዝ አከባቢ በመፈለግ በመሰብሰብ መቅረፅ፣ በፀሀይ እና እሳት ጪስ ማስዋብ ጀመሩ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ቀለል በሉ ነገሮች በመጠቀም የሚያምር ስራ መስራት ጀመሩ፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ሙያ ተጀመረ፡፡.

የሸክላ ሙያ ስራ ምግብ የሚሰራበት እቃ፣ ዉኃ ለመቅዳት እና የተለያዩ ነገሮችን ለማስቀመጥ በእሳት ተቃጥለዉ ይሰራል፡፡ይህ ሙያ ለረጅም ጊዜ ሲሰራ የነበረ ሙያ መሆኑን አንዳንድ ጥናቶች እና የታሪክ መዛግብት ያስረዳል፡፡. ይህ ደግሞ የሰው ልጅ የስልጣኔ ማሳያ ነው፡፡

ከሸክላ አፈር የተሰራ ነገሮች ይሰበራሉ ነገር ግን ስብርባሪዉ ለረጅም አመታት ሳይጠፋ አፈር ውስጥ ይቆያል፡፡እንደ ዋሻ ጥበብ ሁሉ ወይም በፊት ሲሰሩ የነበሩ ሌሎች የጥበብ ስራዎች፤ የፈጠራ ስራ እና የሸክ ስራ ማህበረሰባዊ፣ከምጣኔ ሃብት እና የአከባቢ አየር ሁኔታ ጋር ተያያዥነት እንዳለዉ ያሳያል፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ የሸክላ ስራ የሚሰሩ ሰዎች የሚሰሩትን ሸክላዎች በተለያየ መንገድ ሲያስውቡ ነበር፡፡ በተለያየ አከባቢ የህብረተሰብ ባህል፣እሴት እና ታሪክ ልዩነት እንዳለዉ፤ ሁሉ የማስዋብ እና አሰራር ሂደትም ይለያያል፡፡

የሸክላ ስራ ምርቶች የተለያዩ ጥቅሞች አላቸዉ፡፡ በተለይ እንደ አሁኑ ጊዜ፤ የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸዉ መሳሪያዎች በተለያዩ ነገሮች ከመተካታቸው በፊት፤ ሰዎች የሸክለ ስራ ውጤትን ዉኃ ለመቅዳት፣ ምግብ ለማብሰል፣እህል ለማጠራቀም እና ለመሳሰሉት ጉዳይ ሲገለገሉበት ነበር፡፡

የሸክላ ስራ ለመስራት ተመራጭ የሆነ የሸክላ አፈር ነው፡፡ የተለያዩ እቃዎች ከሸክላ አፈር ከሰራን በኋላ፤ በእሳት ማቃጠል አለብን፡፡ ጥቅሙ ከዉኃ ተፅዕኖ ይታደጋል፡፡ ከሸክ የተሰራዉን በፀሃይ ብቻ አድርቀን ዉኃ ብንጨምርበት፤ ያፈሳል፡፡ ነገርግ ሳንጠቀም በፊት ከአምስት መቶ ድግሪ ሴሊሼስ /500$^{o}$c/ በላይ ቢናቃጥል አያፈስም፡፡ምክንያቱም የሸክላ አፈር በመቃጠሉ የጠነሳ በኬሚካላ ለዉጥ የፕላስትክነት ባህሪይ ስለሚኖረዉ ወኃ በውስጡ እንዲቆይ እና እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡

### ሀ. የሸክላ አፈር አይነት

ከሸክላ አፈር የሚሰሩ መሳሪያዎች በአፈር አይነት እና በሚቃጠልበት ሙቀት ቴምፕሬቸር ላይ በመመስረት ለሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡-

1. ጠንካራ የሸክላ አፈር
2. አሸዋማ አፈር
3. ነጭ የሸክላ አፈር ናቸው፡፡

### 1. ጠንካራ የሸክላ አፈር

ጠንካራ የሸክላ አፈርከአፈር አይነት ሊቆይ የሚችል እና ቀላል የሆነ ነው፡፡ እንዲሁም ለስለስ ያለና በአነስተኛ ቴምፕሬቸር የሚቃጠል/የሚሚሽ ነው፡፡ በአማካይ ቴምፕሬቸር ከአንድ ሺህ እስከ ሺህ ሁለት መቶ ድግሪ ሴሊሼስ /1000$^{o}$c-1200$^{o}$c/ ይቃጠላል፡፡

### 2. አሸዋማ አፈር

ጥቅጥቅ ያለ አፈር እና በአማካይ ቴምፕሬቸር ከአንድ ሺህ አንድ መቶ እስከ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ድግሪ ሴሊሼስ /1100$^{o}$c-1300$^{o}$c/ ይቃጠላል፡፡ በተጨማሪ አሸዋማ አፈር በመስተዋት

ስብርባሪ/ ዱቄት የሚለበስ እና በከፍተኛ ቴምፐሬቸር የሚቃጠል/የሚሟሽ ነው፡፡ የመስተዋት ዱቄት ጥቅም ሲያቃጥሉ ቀልጠዉ በመያያዝ እያንጠባረቀ እንዲያምር እና ዉኃ በውስጡ እንዳያሳልፍ ይረዳል፡፡ ከአሸዋማ አፈር የሚሰራ ስራዎች የተለያ መልክ አላቸዉ፡፡ ለምሳሌ፡ - ከቢጫ ደብዛዛ እስከ ቀይ ደብዛዛ፣ ከግራጫ እስከ ቢጫ ደብዛዛ ወይም አሪንጓዴ መልክ አላቸዉ፡፡.

## 3. ነጭ የሸክላ አፈር

ነጭ የሚያንፀባርቅ እቃዎች ከነጭ የሸክላ አፈር ይሰራል፡፡ በቀላሉ የሚሰበሩ እቃዎች ኩባያ፣ሲኒ፣ሳሕን፣ጨሌ፣ዶቃ እና የመሳሰሉት ከዚህ አፈር ይሰራሉ፡፡ ይህ ምርት ከሌሎች ከፍ ያለ ዋጋ ያለዉ እና የሚያምር ነው፡፡

### ለ. የሸክላ አፈር ውጤቶች ማስዋቢያ ሂደት

ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ምርቶችን በተለያዩ መልክ ማስዋብ ይቻላል፡፡ እነርሱም፡-

- እንዲያንፀባረቅ ማድረግ፡፡
- መቀባት
- መቦርቦር
- ወደ ላይ ማዉጣት፡፡
- ስርዓተ ጥለት/ ፓቴርን መስራት፡፡

### ሐ. የሸክላ ስራ ባህሪይ

- ከፍተኛ የመቅለጫ የሙቀት ነጥብ አለዉ/ ስለዚህ እሳት እንዳይጎዳ ይረዳል፡፡
- ጥንካሬ አለዉ፡፡
- ረጅም እድሜ አለዉ፡፡
- የኤለትርክ ኃይል የማስተላለፍ አቅሙ አነስተኛ ነው፡፡
- ከሌሎች ኬሚካሎች ጋር አፀግብሮት/ብልልት (reaction) አያካሂድም፡፡
- አብዛኛዎቹ ማግኔት አይስቡም፡፡
- አነስተኛ አፍጋት(density) ስላላቸዉ፣ ክብደት የለላቸዉ ነገሮች ይይዛሉ፡፡

### መ. የሸክላ አፈር ደካማ ጎን

- በተፈጥሮ ቶሎ የመሰበር ባህሪይ የላቸዉም፡፡
- መተጣጠፍ ላይ አስቸጋሪ ናቸው፡፡
- በጣም ስስ ከሆኑ ጥንካሬ የላቸዉም፡፡
- የተለያየ ጥንካሬ አላቸዉ፡፡

- ቅርፅ ለማዉጣት አስቸጋሪ ናቸው፡፡

### ሠ. የሸክላ ስራ ጥቅሞች

- ለጌጥ ይዉላል፡፡
- ቤት ውስጥ ለመገልገል ይረዳል፡፡
- ገቢ ያስገኛል፡፡
- የኤሌትርክ ኃይል ለመቀነስ ያገለግላል፡፡
- ሙቀት እና ብርሃን እንዳያሰስተላልፉ ይረዳል፡፡
- የኤለትርክ ሙቀት ለመቀነስ ያገለግላል፡፡

## 2.4.2.2. የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ስራ ጥበብ

### ሀ. የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ስራ ምንነት

የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ የተለያዩ የሚያምሩ እና የማያምሩ ነገሮች የሚሰሩበት ዘዴ እና ቀላል የሆነ እና በቀላል መልክ የሚሰራ ነው፡፡ በተለያየ መንገድ በመጠቀም የአንድን ነገር ሞዴል መስራት ይቻላል፡፡ ጠንከር ያለ ወረቀት በፈለግነው መጠን በመቆራረጥ በኮላ፣ማጣበቂያ፣ቅጠል፣ኡሁ እና በተለያዩ አበባዎች በመጠቀም በተለያዩ ነገር በማጣበቅ እብደሚሰራ ታሪክ እና ጥናቶች ያስረዳል፡፡

### ለ. የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ስራ ታሪክ

የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ስራ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ሃገራት እየተሰራ እንደነበር በተለያየ ጊዜ የተጻፉ ጽሁፎች ያስረዳሉ፡፡ የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ስራ እንዲያድግ እና እንዲታወቅ በይበልጥ የሚጠቀሙበትእና ከፍተኛ ሚና የተጫወቱሃገራት የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ግብፅ
2. ፈረንሳይ
3. መካከለኛ ምስራቅ ሃገራት
4. ሩቅ ምስራቅ ሃገራት
5. የአዉሮፓ ሃገራት

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ሃገራት የጥበብ አመጣጥ እንመልከት፡፡

#### 1. ግብፅ

ከተለያየ የታሪክ ምንጭ መረዳት እንደሚቻለው በጥንት ዘመን ግብፅ የጥበብ ሙያ በመስራት እና በመጀመር የአለም ሃገራትን ትቀድማለች፡፡ ይህች ሃገር ከክርስቶስ ልደት በፊት የጥበብ ስራ በመጀምሯ ከፍተኛ ቦታ ያላት ሃገር ነች፡፡

በጥንት ዘመን በግብፅ ሲሰራ የነበረዉ የጥበብ ሙያ ውስጥ የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ አንዱ ነው፡ ፡ በይበልጥ ሲሰሩ የነበሩ የሬሳ ሳጥን እና የፊት ማስክ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡ እንዲሁም የፔፐር ማሼ /ወረቀት የማቡካት ስራ በመጠቀም አልጋ ልብስ እንደ ማስተሸ/ ለማያያዝ የሚያገለግሉ ነገሮችን በመጠቀም ሲሰሩ ነበር፡፡

## 2. መሀከለኛ እና ሩቅ ምስራቅ ሃገራት

ሩቅ ምስራቅ ሃገራት የሚባሉ ጃፓን፣ቻይና፣ኮሪያ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ መሀከለኛ ምስራቅ የሚባሉት ደግሞ እስራኤል ፍሊስጤም፣እራቅ፣እራን እና የመሳሰሉት መጥቀስ እንችላለን፡፡ በፔሪሽያ አእና ካሽሚር የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ስራ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሁለቱ ሃገራት የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሲሰራ የነበረ ሲሆን፤ የቤት እቃዎች ሳሃን፣ በተለያዩ ቀለማት የተዋቡ የልብስ ሳጥን እንደሚሰራ ታሪክ ያስረዳል፡፡ እንዲሁም በጃፓን እና በህንድ ጋሻ፣ጦር፣ ጎራዴ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ዉጪዉን በማስገጥ ሲሰሩ ነበር፡፡ ሲሰሩ ነበር፡፡

## 3. አዉሮፓ

የፐፔር ማሼ ጥበብ በአዉሮፓ የተጀመረ ሲሆን፤ የተለያዩ እንጨቶችን በመጥረብ የተሰራ ዲዛይን እንደሁለተኛ ምርጫ በቅናሽ ዋጋ እየቀረበ እንደሆነ ታሪክ ይናገራል፡፡ ለምሳሌ፡- በ1772 እ.አ.አ በእንግሊዝ ሃገር ንፁህ ወረቀት በኑግ /ተልባ ዘይት ማያያዝ እና በመለጠፍ ያስፈለገበት ማክንያት፤ ዉኃ እናዳያረጥበዉ የጥረዳል ብለዉ ያምናሉ፡፡ ቴዶሬ ጀኔንስ የሚባል ሰው የተለያዩ ወረቀት በመቀቀል፤ ቅርፃ ቅርፅ ሲሰራ ነበር፡፡ ለምሳሌ፡-ሳሃን፣ጠረጴዛ፣የተለያዩ ቅርፃ ቅርፆችን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ይህ ባለሙያ ዉኃ እና ወረቀት በመጠቀም እና ጠንካራ እናዲሆን የተሰራዉን ስራ በእንጨት እና ብረት ላይ በመለጠፍ እየሰራ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

በአዉሮፓ ሃገር ሲሰራ ከነበሩ ስራዎች የተወሰኑት፡-

- ጀልባ እና
- የፊት ማስክ ናቸው፡፡

ከወረቀት ቅርጻ ቅርጽ የፊት ማስክ መስራት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ሙያዉን ለሚወዱት ሰዎች ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነው፡፡

## ሐ. የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ አይነት

የወረቀት ቅርጻ ቅርጽ ጥበብ አሰራር እና በተለያየ መሳሪያዎች በመጠቀም መስራት እንችላለን፡ ፡ ይህ ስራም ከአጭር እስከ ረጅም ጊዜ በመዉሰድ የሚሰራ ሲሆን፤ ስለዝህ ከህፃናት እስከ አዋቂዎች መሳተፍ ይችላሉ፡፡ በሚንጠቀምበት መሳሪያዎች እና አሰራር ላይ በመመስረት ለሁለት እናካፍላለን፡፡ እነርሱም፡-:

- ወፍራም ወረቀት በመቆራረጥ የሚሰራ እና
- ወረቀት በማቡካት የሚሰራ

1. የተቦካ ወረቀት በመጠቀም ቅርፃ ቅርፅ (ሞዴል) የሚሰራበት ሂደት

ከሸክላ አፈር የተለያዩ ቅርፃ ቅርፅ እንደሚሰራ ሁሉ፤ ከተቦካ ወረቀትም የተለያዩ ፎርም ያላቸዉ/ ሞዴል

መስራት ይቻላል፡፡ ይህም ከተቦካ ወረቀት የሚሰራ ስራ ፐፔር ማሼ ይባላል፡፡ፐፔር ማሼ የሚባል ቃል ከፈረንሳይ የተወሰደ ሲሆን፤ ትርጉሙም የተቦካ ወረቀት ማለት ነው፡፡ ይህ ጥበብ በ11ኛ ክፍለ ዘመን እንደተጀመረ ታሪክ ያስረዳል፡፡.

በፐፔር ማሼ ሞዴል በሁለት መንገድ ይሰራል፡፡ እነርሱም ለዚህ ስራ የሚሆን ስስ ወረቀት በማስያዣ (የእህል ዱቄት በመበጥበጥ) ደጋግመዉ በማያያዝ የሚሰራ ሲሆን፤ ሌላዉ ደግሞ ወረቀት በማቆራረጥ፤ ዉኃ ከበሰበሰ በኋላ ከኮላ/ ሙጫ ጋር እንደ ሸክላ አፈር  በማደባለቅ የተለያዩ  ቅርፃ ቅርፅ ይሰራል፡፡ በዚህ አሰራር ከሚሰሩ ስራዎች ሳሃን፣ኩባያ፣ባልዲ፣ሲኒ እና የመሳሰሉትን መስራት ይቻላል፡፡

## ሀ. ለፔፐር ማሼ ስራ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች

ለፔፐር ማሼ ስራ ከሚያስፈላጉ መሳሪያዎች የተለያዩ ነገሮችን መስራት እንደሚቻል ከጥበብ ታሪክ መረዳት እንችላለን፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሳሪያዎች ማንኛዉም የወረቀት ቅርጻ ቅርፅ ስራ ለመስራት ያገለግላሉ፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች በአከባቢያችን የሚናገኛቸው ወይም በፋብሪካ የሚሰሩ ሊሆኑ ያችላሉ፡፡ እነርሱም፡-

- የተለያዩ ወረቀቶች
- የተለያዩ ቀለማት
- የብርጭቆ ወረቀት
- የተለያዩ መጠን ያላቸዉ ሽቦዎች
- የሚለጠፍበት ነገር (ሳንቃ/ሰሌዳ፣ኮምፖርሳቶ፣ብረት እና የመሳሰሉት)
- የተለያዩ መጠን ያላቸዉ ብሩሾች
- ሳሙና፣ ቫዝሊን እና ዘይት
- ጨዉ
- ጎድጎድ ያሉ እቃዎች ( ጎድጋዳ ሳህን፣ባልዲ እና የመሳሰሉት)
- ፒንሳ
- ቫርኒሽ
- መሮ
- ለማጣበቂያነት የሚያገለግሉ፤ ኮላ፣ ኡሁ፣ ሙጫ፣አዳሚ፣ጥድ እና የመሳሰሉት መዉሰድ እንችላለን፡፡ ከዱቄት ደግሞ ስንዴ፣ጤፍ፣ገብስ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ዉኃ
- እስኮች
- ማንኪያ
- የተለያዩ ፎጣዎች
- ቅርጽ ማዉጫ ነገር ምላጭ፣ መቀስ፣ካተር እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የፐፔር ማሼ ቅርፃ ቅርፅ ሰራ የሚያገለግሉት መሳሪያዎች ያላቸው ጥቅሞች ሚከተሉት ናቸው፡፡

- ወረቀት:ለዚህ ስራ ማኛዉም ወረቀት ብያገለግልም፤ በቀላሉ ወይም በአጭር ጊዜ የሚበሰብስ ቢሆን ይመረጣል፡፡
- ወረቀት እንዲያያዝ የሚያደርጉ ነገሮች፡የመያያዝ ባህሪይ ያላቸዉነገሮች እንደነ ኮላ፣ከእህል ዱቄት የተዘጋጀ ሊጥ፣ ተልባ እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በአከባቢያችን የሚገኙ ነገሮችዱቄት እና የተቦካ ወረቀት በደንብ የሚደባለቅ/የመሳሳብ ባህሪይ ያላቸዉ ከእነርሱም የስንዴ ዱቄት እና አጃ ሲሆን፤ ለመስራት የማይመቹ ደግሞ የማሽላ እና ቦቆሎ ዱቄት ለስለስ ስለሚል መጠቀም አስፈላጊ አይደለም፡፡
- ነጌቲቭ:ነጌቲቭ  በፐፔር ማሼ ስራ ለሚሰራ ነገር ፎርም የሚሰጥ ነው፡፡ ይህን ነጌቲቭ በሚንሰራ ነገር ሞዴል መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ፡-በዚህ ጥበብ የሲኒ ሞዴል የሚሰራ ከሆነ እንደ ነጌቲቭ የሚንጠቀመዉ ሲኒ ነው፡፡
- ሳሙና ፣ ዘይት፣ ቫዚሊን እና የመሳሰሉት:ይህ ደግሞ የሚሰራ ሞዴል ከነጌቲቭ አካ ጋር እንዳይያያዝ ያገለግላል፡፡ ይህም የሞዴል አካል ከነጌቲቭ ጋራ በሚሰራበት በኩል ሲሆን፤ በነጌቲቭ አካል በዉሥጥ በኩል የሚንሰራ ከሆነ፤ በውስጥ በኩል እንቀባለን፡፡ በዉጪ በኩል የሚንሰራ ከሆነ በዉጪዉ እንቀባለን፡፡በአከባቢያችን ከሚንገኘ ነገሮች መስራት እንችላለን፡፡
- ቀለም፡የሚሰራ ሞዴል ከተሰራ በኋላ በሰራ ሞዴል ላይ አስፈላጊ ዲዛይን  ለመስራት/ ለማስዋብ የሚያገለግል ነው፡፡
- የብርጭቆ ወረቀት፡በዚህ ስራ የብርጭቆ ወረቀት ጥቅም የተሰራዉን ሞዴል አካል ለማስተካከል/ለማሽት፡፡
- ጨዉ፡ የተቦካ ወረቀት እንድብላላ ያገለግላል፡፡

## ለ. የፐፔር ማሼ አሰራር

ከፐፔር ማሼ የተለያዩ ሞዴሎች የሚሰራበት ሁኔታ ከሚቀጥለዉ መረዳት እንችላለን፡፡

- ለዚህ ስራ የሚያገለግል ወረቀት በማቆራረጥ በንፅሁ ዉኃ ውስጥ እንድረጥብ ማቆየት፡፡
- በእህል ዱቄት የሚንጠቀም ከሆነ፤ የእህል ዱቄት እና በጨዉ የተበጠበጠ ዉኃ በመጨመር ሊጥ ማዘጋጀት፡፡ ይህም ሊጥ እሳት ላይ በመጣድ ከፈላ በኋላ እንዲቀዘቅዝ ማድረግ፡፡ ኮላ ማግኘት የሚንችል ከሆነ ደግሞ በዱቄት ሊጥ ፋንታ ኮላ መጠቀም እንችላለን፡፡
- በዉኃ ውስጥ የረጠበ ወረቀት በሊጥ ወይም ከኮላ ጋር ማዋሃድ፡፡.
- ሊጥ እና የተቦካ ወረቀት ሲናደባልቅ እኩል በሆነ መጠን መሆን አለበት፡፡.
- በደንብ እንድብላላ ለሃያ አራት (24 ሰዓት) ማቆየት፡፡
- ለሚሰራ ሞዴል እንደ ነጌቲቭ የሚያገለግል ነገር ማዘጋጀት
- ሞዴል በመሚሰራበት በኩል ነጌቲቭ አካል ሳሙና ወይም ዘይት መቀባት፡፡
- የተደባለቀ ወረቀት እና ሊጥ በደንብ ታሽተዉ፣መስራት በፈለግን ሁኔታ ዘይት ወይም ሳሙና በተቀባበት በኩል በነጌቲቭ አካል ላይ በመለጠፍ ሞዴሉን መስራት፡፡
- የሚሰራ ሞዴል ደርቀዉ የነጌቲቭ አካል እስክለቅ ድረስ እንዲቆይ ማድረግ፡፡ የሚሰራ ሞዴል ከደረቀ በኋላከነጌቲቭ አካል ማስለቀቅ፡፡

- ከተቦካ ወረቀት የተሰራ ሞዴል ደርቀዉ ከነጌቲቭ አካል ካስለቀቅን በኋላ እኩል ያልሆነ ቦታ በብርጭቆ ወረቀት በማሸት እኩል ማድረግ፡፡
- በመጨረሻም ቀለም በመጠቀም የተሰራዉን ሞዴል ላይ ዲዛይን በመስራት ማስዋብ፡፡

## ተግባር 9

1. ከዚህ በላይ የተዘረዘረዉን የተቦካ ወረቀት አሰራር በመከተል፤ የጎርጓዳ ሳሃን ሞዴል በመስራት ለክፍል አቅርቡ፡፡

ከተቦካ ወረቀት የተለያዩ ሞዴሎችና መስራት እናደሚቻል ተምረሃል፡፡ ስለዚህ ለፐፔር ማሼ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማዘጋጀት፤ ከላይ የተገለፀዉን የፐፔር ማሼ አሰራር በመከተል፤ ጎርጎድ ያለ ሳሃን በመስራት ለመምህራችሁአሳዩ፡፡ የዚህ ስራ ዉጣዉረድ እና ያጋጠመህን/ሽን ነገር እንዲሁም ምን እንደተማርክ/ሽ ለክፍል ተማሪዎች አስረዱ፡፡.


## ተግባር 10

የሳህን ሞዴል ከሰራችሁ በኋላ የሚከተለዉን አሰራር በመከተል፤ ከፐፔር ማሼ የአእዋፋት፣ የቤት እንስሳት እና የዱር እንስሳት የሚመቻቻሁን ስሩ እና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ በመጨረሻም አጠቃላይ የስራ ሂደት እና በዚህ ስራ ያጋጠመዉን ነገር እንዲሁም የተማራችሁበትን ነገር ለተማሪዎች አስረዱ፡፡

### የአሰራር ቅደም ተከተል

- የሚትፈልጉ ንድፍ በወረቀት ላይ በእርሳስ የአዋፋት፣የቤት እንስሳት እና የዱር አራዊት ንደፉ፡፡
- የተሰራዉን ንድፍ በማየት የእንስሳት ሞዴል መስራት ከፈለጋችዉ በሽቦ ሞዴሉን መስራት፡፡ሽቦ ለማግኘት የሚያስቸግር ከሆነ በክር እና ቀጫጭን እንጨት መጠቀም ይቻላል፡፡

.



ሥዕል 2.15 ከሽቦ፣ ከቀጭን እንጨት ና ወረቀት የተሰራ የቅርፀ ቅርፅ ስራ

- የተቦካ ወረቀት እና ከኮላ ጋር በማዋሃድ አዘጋጁ፡፡
- ፎርሙን በሸቦ ወይም ከእንጨት በተሰራ ላይ የተቦካዉን ወረቀት በትንሹ የሚሰራዉን ፎርም በማየት ማያያዝ፡፡
- ትንሽ ከቆያቸው በኋላ ከላይ መጨመር፡፡
- በመጨረሻም የሚሰራ ነገር እስከ መስል ድረስ ስሩ፡፡
- ከጨረስክ በኋላ እንዲደርቅ ፀሀይ ውስጥ አድርጉ፡፡
- እኩል ያልሆነ አካል ላይ የሚስተካክለል ነገር ካሌ በብርጨቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡
- በመጨረሻም አስፈላጊ የሆነ ዲዛይን በሞዴሉ ላይ በመስራት በቀለም አሳምሩ፡፡

## 2. ወረቀት በማያያዝ ሞዴል መስራት

የዚህ ዘዴ ወረቀት በዉኃ ውስጥ በመዘፍዘፍ የሚሰራ ሳይሆን፤ ወረቀት በማቆራረጥ በሙጫ/ኮላ ደጋግሞ በማያያዝ የተለያዩ ሞዴል የሚሰራበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ስራ በጥሩ መልክ ከተሰራ የተለያዩ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳል የቤት እቃ እና ጌጣ ጌጥ መስራት ይቻላል፡፡.

በዚህ ዘዴ የሚሰሩ እቃዎች ኩባያ፣ሳሃን፣ሰው፣የቤት እንስሳት እና የመሳሰሉትን መስራት ይቻላል፡፡ ለዚህ ስራ ዘዴ የሚያስፈልጉ ነገሮች እንደሚከተለዉ ቀርቧል ተመልከቱ፡፡

### ሀ. ለዚህ ስራ የሚያገለግሉ ነገሮች

- ለዚህ ስራ ምቹ የሆነ ወረቀት ጋዜጣ፣ የተለያዩ መፅሔት እና የመሳሰሉት፡፡.
- መቁረጫ/ከተር
- ሙጫ
- እንደ ሞዴል ያለዉ ነጌቲቭ ነገር
- የብርጭቆ ወረቀት
- እርሳስ
- ቀለም እና ብሩሽ
- ዘይት

### ለ. የስራዉ ሂደት

- የሚሰራዉን ሞዴል መወሰን፡፡
- ለዚህ ስራ የሚያገለግል ወረቀት ማዘጋጀት፡፡
- የተዘጋጀዉን ወረቀት በመቁረጫ በቀጭኑ መቁረጥ፡፡
- ሞዴል በሚሰራበት አቅጣጫ በነጌቲቭ አካል ላይ ዘይት መቀባት፡፡
- ወረቀት በዉኃ በመንከር፤ ሙጫ/ኮላ ሳይቀባ ለመጀመሪያ ዙር በነጌቲቭ አካል ላይ ማያያዝ እና መለጠፍ፡፡
- የተቆራረጠዉን ወረቀት ሙጫ/ኮላ በመቀባት ተራበተራ ከላያ ላይ ማያያዝ፡፡
- በዝሁ ሁኔታ ወረቀት እስክወፍር ድረስ ደጋግመሞ ማያያዝ፡፡

- የሚንሰራ ከመሰለልን እንዲደርቅ ፀሀይ ላይ ማስቀመጥ፡፡
- ከደረቀ ቦኋላ ዳር ላይ የሚቀሩ ወረቀት ስለት በሆነ ነገር ማስተካከል እና የማያስፈልግ ነገር መቁረጥ፡፡
- የተሰራ ሞዴል ከነጌቲቭ አካል ማለያየት፡፡

በዚህ ስራ መታወቅ ያለበት ነገር፤ ወረቀት በሙጫ/ኮላ በመቀባት በነጌቲቫ አካል ሳንያያዝ በፊት፤ በመጀመሪያ ዙር ወረቀት በዉኃ በመንከር፤ በነጌቲቭ አካል ላይ ማያያዝ የሚንሰራበት ወረቀት ነጌቲቭ አካል እንዳይነካ ያገለግላል፡፡

- የተሰራዉን ሞዴል በብርጭቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡
- በመጨረሻ ለማሳመር ኮላ አቅጥነን በብሩሽ መቀባት፡፡
- ከዚህ በኋላ እንዲደርቅ ማድረግ፡፡
- ይህ ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ ወይም ሞዴሉ ከደረቀ በኋላ ቀለም በመቀባት የተለያዩ ዲዛይን በማሳመር እንደጥቅሙ መጠቀም እንችላለን፡፡

## ተግባር. 11


ወረቀት በሙጫ/ኮላ በማያያዝ የተለያዩ ሞዴሎች እንደሚሰራ ተምራቸዋል፡፡ ለዚህ ስራ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በማሟላት፤ ወረቀት በማቆራረጥ የሉል ሞዴል እነደሚሰራ የሚከተለዉን ቀድም ተከተሉን በመከተል፤ የሉል ሞዴል በመስራት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡ በመጨረሻም ያለዉን ጠንካራ እና ደካማ ጎንህን/ሽን ከተማሪዎች እና ከመምህርህ ተቀበሉ፡፡

የአሰራርሂደት ቅደም ተከተል

- ለዚህ ስራ የሚመቸዉን ወረቀት በቀጫጭን መጠን በመቁረጥ አዘጋጅ/ጂ፡፡
- እንደ ነጌቲቭ የመሚያገለግል መሳሪያ አዘጋጅ፡፡ ለምሳሌ፡- ክብ ቅርጽ ያለዉ ድስት ወይም ለዚህ ስራ የሚሆን ጎድጓዳ ሳህን፡፡
- ነጌቲቭ አካል ዘይት ቀቡ፡፡
- በመጀመሪያ ዙር የነጌቲቭ አካል ወረቀት ወኃ ውስጥ በመንከር አያይዙ፡፡
- በሁለተኛ ዙር በወኃ ተነክሮ የተያያዘዉን ወረቀት ላይ ሙጫ/ኮላ በመቀባት ሌላ ወረቀት በማያያዝ መስራት የፈለግነውን ቅርፅ እስክመስል ድረስ ማያያዝ፡፡
- እንዲደርቅ ፀሀይ ላይ አድረግ/ጊ፡፡
- ከደረቀ በኋላዳር ላይ የሚቀሩ ወረቀት ስለት በሆነ ነገር ማስተካከል እና የማያስፈልግ ነገር መቁረጥ፡፡ ይህም ክብ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህ ዘዴዎቸች አንዱ የሚንሰራበት ሞዴል በመቀመጫ በኩል ግማሽ ክብ አካፍላችሁ በስፒል/በአከባቢያችሁ በሚገኝ ነገር አያይዙ፡፡
- መርፌ/በአያይዛችሁት ነገር ላይ ክር በማሰር፤በሌላኛዉ ክር ጫፍ እርሳስ በማሰር፤ ክብ መስመር ስሩ፡፡
- በእርሳስ የሚሰመር መስመር እኩል በሆነ ርቀት/ራዲየስ በጀመርንበት ቦታ መመለስ አለብን፡፡

በዚሁ መሰረት ሁለተኛዉን ሞዴል በመስራት ለሉል/ግሎብ/ ስራ የሚመቸዉን ወረቀት አዘጋጅ/ጂ፡፡

የዚህ ስራ አሰራር ግልፅ እንዲሆንላችሁ ከታች ያለዉን ስዕል ተመልከቱ፡፡





ስዕል 2.16 ወረቀትን በማያያዝ የተሰራ ሞዴል

በዚህ ስራ ሁለት የተዘጋጁ ሞዴሎች እናዳይበላለጡ በሁለቱም ላይ በእርሳስ የሚሰራዉን መስመር ማስመር ተገቢ ነው፡፡ይህ ካልሆነ ሁለቱ የሚሰራ ሞዴሎች ስለሚበላለጡ፤ ላይገጣጠሙ ይችላሉ፡፡ በዚሁ ሁኔታ ሌላ ዘዴ ካሌ መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህ ሁለቱ ቅርፆች እንያያዙ/ እንዲገጣጠም፤በተለያየ ዘዴ መጠቀም ይቻላል፡፡ይህምመካከለኛ ዉፍረት ያለዉ ወረቀት/ ወርዱ ስድስት ሴንት ሜትር (6ሴ.ሜ) እና ርዝመቱ ከተሰራ ሞዴል አፍ ጋር እኩል የሆነ ክላሰር አዘጋጅ/ጂ፡፡ ይህን ወፍራም ወረቀት ሶስት ሶስት ሴንትሜትር ሁለት ቦታ አካፍል/ዪ፡፡

- እስከ ሶስት ሴንትሜትር (3ሴ.ሜ) ሙጫ/ኮላ ቀባ/ቢ፡፡
- ሙጫ/ኮላ በተቀባዉ በኩል በአን ቅርፅ ውስጥ በማስገባት፤ የተሰመረዉን መስመር በመከተል በአፉ ቅርፅ ወረቀቱን በማዞር አያይዙ፡፡
- ሶስት ሴንትሜትር ያህል የቀረዉ ደግሞ ወደ ዉጪ ይቀራል፡፡
- ሶስት ሴንትሜትር ወረቀት/ክላሴር በኣንዱ ቅርፅ አፍ ወደላይ የቀረዉን በማዞር በዉጪዉ በኩል ሙጫ/ኮላ ቀባ/ቢ፡፡
- ሁለተኛዉን ስራ በማምጣት ሙጫ/ኮላ የጠቀባዉን ክላሰር በውስጥ በኩል በማድረግ ክደኑ፡፡
- በውስጥ በኩል ሙጫ/ኮላ የተቀባዉ ወረቀት ሁለቱን ቅርፅ ለማያያዝ ያገለግላል፡፡
- ይህ የተሰራ የሉል ሞዴል የአፉ ዳር ተስተካክለዉ እና ተያይዘዉ ከደረቀ በኋላ፤ የተሰራዉን ሞዴል በዉጪ በኩል የሚበላልጠዉን ቦታ በብርጭቆ ወረቀት በማሸት ማስተካከል፡፡
- ሙጫ/ኮላ በማቅጠን ሞዴሉን በዉጪ በኩል ቀባ/ቢ፡፡ ይህም የሚቀባ ቀለም ወረቀቱ እናዳይመጥ እና የቀረ ቀዳዳ ካሌ ለመድፈን ያገለግላል፡፡.

- ሁለቱ ቅርፅ ከተያያዘ በኋላ የስፍር ፎርም ወይም ሉል የሚመስል ቅርጻ ቅርጽ ማግኘት እንቸችላለን፡፡
- የአለም ካርታ/ የሉል ስዕል ከመፅሐፍ ወይም ከሌላ ነገር በማየት ወኃ ያለበት ቦት ነጭ-ሰማያዊ (ሰማያዊ ወኃማ) ቀለም ቀባ/ቢ፡፡ መሬት ያለዉ ቦታ ደግሞ የተመረጠዉን ቀለም ቀባ/ቢ፡፡
- በመጨረሻም የመሪዲያን እና ሎንግትዉድ እንዲሁም የመሬት ወገብ የሚያሣይ መስመር በመስራት እንደግሎብ መጠቀም እንችላለን፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፁት ዘዴዎች ብቻ ሳይሆን ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡
በዚህ ዘዴ የተሰራዉን ሉል/ግሎብ ተመልከቱ፡፡



ማሳሰቢያ፡-፡ ከዚህ በላይ ያለዉን ቅደምተከተል ስንመለከት፤ እንደ ነጌቲቭ የሚያገለግለዉ መሳሪያ በምሳሌ የተገለፀዉ ክብ ቅርፅ ያለዉ ድስት ወይም ጎድጓዳ ሳሃን ለዚህ ስራ ይጠቅመናል፡፡

በድስት እና ሳሃን ፋንታ የመረብ እና እግር ኳስ መጠቀም እንቸችላለን፡፡ ነገርግን በጥንቃቄ መሆን መስራት አለብን፡፡.

- በኳስ እንዴት መጠቀም እንችላለን ለሚለዉ ሃሳብ፤ በምንጠቀምበት ነጌቲቭ አካል ይቀየራል እናጂ የተገለፀዉ ቅደምተከተል እንደተጠበቀ ነው፡፡ ከኳስ የሉል/ግሎብ ሞዴል ለመስራት፡-
- ኳስ በደንብ መነፋት አለበት፡፡
- ዘይት/ቫዝሊን መቀባት፡፡
- ከዛ በኋላ በወኃ የተነከረዉን ወረቀት፤ በመጀመሪያ ዙር አዙረን በማያያዝ፤ ይህን ሲንሰራ ኳስ የሚነፋበት ቀዳዳዉን መድፈን የለብንም፡፡
- በመቀጠል ወረቀት በኮላ በመቀባት፤ እስከተፈለገ በማወፈር ኳስ የሚነፋበት ቀዳዳ እንዳይነካ በመጠንቀቅ ወረቀቱን ማያያዝ፡፡
- ከዚያ በኋላ እንድደርቅ ፀሀይ ላይ ማድረግ፡፡
- በደንብ ከደረቀ በኋላ ከላይ የተገለፀዉን ዘዴ በመጠቀም መሀሉን በእርሳስ እያዞርን

ማስመር፡፡

- ኳስ የሚነፋበት ቀዳዳዉን በመክፈት አየር ከውስጡ እንዲወጣ ማድረግ፡፡
- አየሩ ከውስጡ ወጥቶ ካለቀ በኋላ፤ በጥንቃቄ ኳስ ሳይቆረጥ በከተር ቅድም በእርሳስ ያሰመርነውን መስመር ተከትለን በመቁረጥ ኳስ እና ወረቀት ማለያየት፡፡
- ከላይ ያለዉን ቅደም ተከተሉን በመከተል፤ ሁለት ቦታ የተካፈለዉን ወረቀት በኮላ በማያያዝ የሚያስፈልገዉን ነገር በመስራት ስራዉን ማጠናቀቅ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ፊልምም ሆነ ትያትር ዋናዉ መሠረቱ በምናባችን ዉስጥ የፈጠረነውን ከመፃፍ ይጀምራል፡ ፡
- መጻፍ ማለት በነበረው ፍቺ በፅሁፍ የተፈለገዉን መልዕክት ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡
- አንድ ፅሁፍ ስፃፍ ለምፃፍ ጉደይ፣ለምፃፍ ዓላማ እንዲሁም ለማን እንደሚፃፍ ግምት ውስጥ በማስባት ነው፡፡
- በትያትር ጥበብ ፕሮደክሽን ዝግጅት ዉስጥ የገፀ-ባህርያት ሚና ስክረፕትን መለማመድ ነው፡፡
- የትያትር ልምምድ በተደጋጋሚ በማጫወት ድርሻቸውን በመወጣት ስራቸው ውበት እንደዲኖርና በጥበብ እንዲቀርብ ማድረግ ነው፡፡
- አንድ የትያትር ጥበብ ሥራ ውበት በምኖረው መልክ ተመልካችጋ እንዲደርስ የሚያደርገዉ ዳይሬክተር ነው፡፡
- የስነ-ጥበብ ሂስ ማለት አንድን የጥበብ ሥራ ጥንካሬዉና ደካማ ጎኑን መገምግ ነው፡፡
- የሸክላ ስራ ጥበብ ብዙ ዘመን ያስቆጠረ እና የሰው ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ስፍራዎች በመስራት ሲገለገልበት ነበር፡፡
- የሸክላ ስራ ጥበብ የስነ-ዉበት ጥበብ ሲሆን ከሸክላ አፈር በተለያዩ ቦታዎች ሲሰሩ ነበር፡፡.
- ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ነገሮች የሚሰበሩ ናቸው ነገርግን የተሰባበሩት ሸክላዎች በቀላሉ ሳይጠፉ ለረጅም ዘመን አፈር ውስጥ መቆየት ይችላል፡፡
- ከሸክላ የሚሰሩ እቃዎች እና አሰራር የአንድ ህብረተሰብ ከሌሎች ልዩነት አላቸዉ፡፡
- ሁሉም የሸክላ ስራዎች ምርት ለመስራት የሸክላ አፈር ተመራጭ ነው፡፡
- ከሸክላ አፈር የሚሰራ እቃዎች የአፈር አይነት እና የሚሟሸበት/በሚቃጠልበት ቴምፐራቸር ላይ በመመስረት ለሶስት ይካፈላሉ፡፡
- ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ምርቶች በተለያዩ ሁኔታ ማስዋብ እንችላለን፡፡
- ከሸክላ አፈር የሚሰሩ ነገሮች የኤሌትርክ ኃይል ለማስተላለፍ ዝቅተኛ አቅም አላቸዉ ወይም አያስተላልፍም፡፡
- የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ የተለያዩ የሚያምሩ እና የማያምሩ ስራዎች የሚሰሩበት ዘዴ ነው፡፡
- በግብፅ ሃገር ከሚሰሩ የጥንት ዘመን ቅርፃ ቅርፅ ጥበባት ውስጥ አንዱ የወረቀት ቅርፃ

ቅርፅ ነው፡፡

- የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ እንዲያድግ እና እንዲታወቅ በተለይ ሲጠቀሙበት እና ከፍተኛ ሚና ሲያበረክቱ የነበሩት ሃገራት ፈረንሳይ፣ግብፅ፣መሀከለኛ ምስራቅ ሃገራት፣ሩቅ ምስራቅ ሃገራት እና የአዉሮፓ ሃገራት ናቸው፡፡
- ፐፒር ማሼ የሚል ቃል ከፈረንሳይ ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም የተቦካ ማለት ነው፡፡

## የምዕራፍ 2 መልመጃዎች

### ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ለሆነው ዓረፍተ-ነገር 'እዉነት' ትክክል ላልሆነው ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልሱ፡፡

1. የስነ-ጥበብ ባለቤት አይታወቅም፡፡
2. የስነ-ጥበብ ሥራ ለመስራት የማህበረሰብ ኑሮዉን በጥልቀት ማዋቅ ግዴታ አይደለም፡፡
3. በፈጠራ ችሎታ ውስጥ ፀሃፊዉ ችሎታዉን ለማጠናከር ሃሳብ ከትያትር በለሙያዎች በመዉሰድ የፈጠራ ችሎታዉን መጠናከር ይችላል፡፡
4. አንድ የትያትር ጥበብ ሥራ ዉበት በሚኖረዉ መልክ ወደ ተመልካች እንዲደርስ የምያደርገዉ ዳይረክተር ነው፡፡
5. በስነ-ጥበብ ሂስ ውስጥ የምተገበረዉ የስራዉ መላላትና ድክመት መገምገም ብቻ ነው፡፡
6. የሰው ልጅ ከሸክላ አፈር የተለያዩ ነገሮችን በመስራት መጠቀም ሳይጀምር በፊት፤ ዘንቢል በመስራት ሲጠቀምበት ነበር፡፡
7. የሸክላ ጥበብ ሙያ ምግብ ለማብሰል የሚያገለግል፤ እቃዎች ብቻ የሚንሰራበት ጥበብ ነው፡፡
8. የሸክላ ስራ ምርት የሆኑትን በእሳት ማሚሸት/ማቃጠል ግዴታ አይደለም፡፡
9. የሸክላ ስራ ምርት የሚሆኑ በቀላሉ ስለሚሰበር፤ ስብርባሪዉ በቀላሉ ይጠፋል፡፡
10. ከሸክላ አፈር የተሰራዉን ነገር በፀሀይ እንደ ደረቀ፤ ዉኃ ብንጨምርበት ያፈሳል፡፡
11. ሁሉም የሸክላ ስራ ምርት የሆኑት ተመሳሳይ በሆነ ቴምፕረቸር ይሚሻሉ/ ይቃጠላሉ፡፡
12. የሸክላ አፈር ከሌላ ኬሚካሎች ጋር ማብላላት እያካህዱም/አይብላሉም፡፡
13. በጥንት ዘመን ሲሰራ የነበረ የወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ፤ የሬሳ ሳጥን እና የፊት ማስክ ናቸው፡፡
14. ፐፒር ማሼ ማለት ተቆራርጠዉ በሙጫ/ኮላ የተያያዘ ማለት ነው፡፡
15. በሙዚቃ ዉስጥ ሶልፌጅዮ መሰረታዊና ወሳኝ ነዉ፡፡
16. የአምባሰልና የአንቺሆዬ ለኔ ቅኝቶች ስመሰረቱ ልዩነታቸዉ የአንድ ድምፅ ብቻ ነዉ፡፡
17. የኦሮሞ የባህል ዉዝዋዜ ከቦታ ቦታ ልዩነት አለዉ፡፡
18. የሙዚቃ ክሌፎች ሁለት ዓይነት ብቻ ናቸዉ፡፡

19. የባህል ዉዝዋዜ ስወዛወዝ ያለ ባህል ልብስ መወዛወዝ አይቻልም፡፡

## ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. በትያትር ጥበብ ፕሮደክሽን ዝግጅት የገፀ-ባህርያት ሚና ምንድነው ?

ሀ. የስክሪፕት ልምምድ ማድረግ

ለ. ገፅ-ቅብ ማዘጋጀት

ሐ. አልባሳት ማዘጋጀት

መ. በጀት መመደብ

2. ከሚከተሉት ውስጥ በጥበብ ሂስ መሰረታዊ የተሰራውን ሥራ መረጃ የሚገለፀዉ የቱ ነው?

ሀ.ግምገማ ውስጥ ለ.ዉሳኔ ውስጥ ሐ.ማብራሪያ ውስጥ መ.ፍቺ ውስጥ

3. ፀሃፊው ችሎታዉን ለማሻሻል/የማሳደግ ምን ማድረግ አለበት ?

ሀ. ማህበረሰቡን በጥልቀት ማወቅ

ለ.ማስተወሻ መያዝ

ሐ. ከግላዊ ስሜት ራሱን መቆጠብ

መ. ሁሉም

4. የዳይሬክተር ሚና ምንድነው?

ሀ. ስክሪፕት ማንበብ

ለ. የልምምድ ፕሮግራም መዘጋጀት

ሐ. የትርእት ቀን መወሰን

መ. ሁሉም

5.አንድ ፅሁፍ ሲፃፍ ምን መካተት አለበት?

ሀ. ለምፃፍበት ጉደይ

ለ. ለምፃፍበት ዓላማ

ሐ. ለተመልካች

መ. ሁሉም መካተት አለባቸው፡፡

6. ከሚከተሉት አንዱ የሸክላ ጥበብ አሰራር የሚናሳምርበት ዘዴ ነው፡፡

ሀ. እንዲፀባረቅ ማድረግ ለ. መቀባት

ሐ. ስርዓት ጥለት መስራት መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

7. ከሚከተሉት ውስጥ የሸክላ አፈር ባህሪይ የሚገልፅ የቱ ነው?
   ሀ. የመቅለጥ ነጥብ ከፍተኛ ነው፡፡
   ለ. ጥንካሬ አለዉ፡፡
   ሐ. ረጅም እድሜ አለዉ፡፡
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡.
8. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሸክላ አፈር ደካማ ጎን ነው፡፡
   ሀ. በተፈጥሮ በቀላሉ የመሰበር ባሕሪይ አለዉ፡፡
   ለ. በፍፁም አይተጣጠፍም፡፡ . ሠ.ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
   ሐ. በጣም ስስ ከሆኑ፣ጥንካሬ የላቸዉም፡፡
   መ. ቅርፅ ለማዉጣት አስቸጋሪ ነው፡፡
9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የሸክላ አፈር ጥቅም ይገልፃል፡፡
   ሀ. ለጌጥ ያገለግላል፡፡
   ለ. ቤት ውስጥ ለመጠቀም ያገለግላል፡፡
   ሐ.የኤለትርክ ኃይል ለመከላከል ያገግላል፡፡
   መ.ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
10. ከሚከተሉት ሃገራት ውስጥ ለወረቀት ቅርፃ ቅርፅ ጥበብ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የትኛዉ ነው?
    ሀ. ፈረንሳይ ለ. ግብፅ ሐ. ግሪክ መ. ሩቅ ምሰራቅ ሃገራት
11. ፐፔር ማሼ ማለት ከየትኛዉ ሃገር ቋንቋ የመጣ ነው?
    ሀ. ግብፅ ለ. ፈረንሳይ ሐ. ጃፓን መ. ቻይና
12. ከሜጀር እስኬል ዉስጥ 3ኛእና 7ኛን በማስቀራት፣ 2ኛ እና 5ኛን ድምፅ በ$^1/_2$ በመቀነስ የምሰራ ቅኝት

    ሀ. ትዝታ ለ. በቲ ሐ. አንቺሆዬ ለኔ መ. አምባሰልና

13. የአርሲ ኦሮሞ የባህል ወዝዋዜ ምን ይባላል?

    ሀ. ትርትርሳ ለ. ትሪ ሐ. ኤእያ መ. እሽኬኬ

14. የወለጋ ኦሮሞ የባህል ዉዚዋዜ ኤሞሌ ከሆነ የራያ ኦሮሞ ምን ይባላል?

    ሀ. ኤእያ ለ. ኩምኩሜ ሐ. ጉቤሎሌ መ. ሹምቤ

15. C D$^b$ F G A$^b$ C ይህ ቅኝት የቱ ነዉ?

    ሀ. አምባሰል ለ. ባቲ C. አንቺሆዬ ለኔ D. ባቲ ሚጀር

16. ከዚህ በታች ከሉት ዉስጥ የአንቺሆዬ ለኔ A ቅኝት የቱ ነዉ?

    ሀ. A$^b$ B$^{bb}$ D$^b$ E$^b$ F$^b$ A$^b$ ሐ. A, B$^b$, D$^b$, E$^b$, F, A,

    ለ. A$^b$ B$^{bb}$ D$^b$ E$^{bb}$ F A$^b$ መ. መልስ አልተሰጠም፡፡

# ምዕራፍ 3
# የስነ-ጥበባት ባህልና ታሪክ

## የመዕራፉ ትምህርት ውጤቶች

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ፣

- ሙዚቃ በባህል ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ ትለያላችሁ፡፡
- የሙዚቃ፣ሙዚቃ መሳሪያዎችና ዉዝዋዜ ግንኙነት ትረዳላችሁ፡፡
- የሃውልት፣መታሰቢ.ያ ሀዉልትና ቅርጻ ቅርጽ ምንነትና ትርጉም መካከል ያለውን ልዩነት ትረዳላችሁ፡፡
- የሃውልትን ትርጉም ትለያላችሁ፡፡
- ስለ ሞኑመንት እና የጥንት ዘመን ታርከዊ ቦታዎችን ምንነት ትረዳላችሁ፡፡
- በአከባቢ.ያችሁ የሚታቁትን ተረቶችን ወደ ትያትር ትቀይራላችሁ፡፡
- የተረት ጭብጥ ሃሳብ ትማራላችሁ፡፡

### መግቢ.ያ

በምዕራፍ ሁለት ዉስጥ የምት ጠቀሜታ በሶልፌጂዮ ዉስጥ፣እንዴት እንደምናነብ፣ የአንቺ ሆዬ ለኔና አምባሰል ቅኝት በመታገዝ መጫወት እንደሚቻል ተምራቿል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሙዚቃ፣የሙዚቃ መሣሪያና ውዝዋዜ በባህል ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ትማራላችሁ፡፡ የእጅ ስራ ሙ.ያ የተለያዩ ነገሮችን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፣ከድንጋይ የተሰሩ መሳሪያዎች፣ ከሸክላና ብረት የተሰሩ መሳሪያዎች እንደ ጦር ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ እንዲሁም ለውበት የሚውሉ ነገሮች እንደ ልብስ አዝራር/የልብስ ቅልፍና የህክምና ልብስ ያካትታል፡፡ ሐውልቶችና የመታሰቢ.ያ ሐውልቶች የተሰሩበትን ሁኔታ ልዩነት ቢ.ኖራቸውም በሚ.ያስተላልፉት መልዕክት ላይ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

ማንኛም የስነ-ጥበብ ስራ ከህብረተሰቡ ኑሮ ሁኔታ ጋር እንደሚ.ያያዝ ባለፉት ትምህርት ክፍል ከተማራችሁ ተረድታቿል፡፡ ስነ-ጥበብን ለመስራት እንደ መነሻ ሀሳብ ሊ.ሆንልን የሚ.ችለዉ የህብረተሰብችን አኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የኦሮሞን አፈ-ታሪክ የሚናውቀውን ወደ ስነ-ትያትር በመቀየር ህብረተሰቡን እንዲናስተምር ነዉ፡፡ እንዲሁም የማናዉቀዉንም በመጠየቅ እንዲንማር የሚ.ጠቁመን ነዉ፡፡ የዚህ ርዕስ ዋና ትኩረቱ የኦሮሞን ህዝብ ተረቶች ወደ ትያትርና ፊልም በመቀየር እንዲንችል ነው፡፡

## 3.1 የሙዚቃ ባህላዊ ገጽታ፣የሙዚቃ መሳሪያዎችና ውዝዋዜ

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ :

- የሙዚቃ፣ሙዚቃ መሳሪያዎችና ባህላዊ ሙዚቃንግንኙነትትገልጻላችሁ፡፡
- የሙዚቃ፣ሙዚቃ መሳሪያዎችና ባህላዊ ሙዚቃ በህብረተሰብ ዉስጥ ያለው ጥቅም ትዘረዝራላችሁ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

እንድ ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታዉ፣ባህሉ፣ልማዱና ኢኮኖሚዉን በምን መንገድ መግለጽ ይችላል?

ባህላዊ ዘፈን፣ዉዝዋዜ፣እንዲሁም የሚዘፈንበት፣ የሚወዛወዝበትና የሚንጠቀምበት የሙዚቃ መሳሪያዎች የራሱ የሆነ ምክንያት አለው፡፡ ሙዚቃ የህብረተሰቡን ቋንቋ፣ባህልና እሴት ከውስጡ የያዘ ሲሆን፤ ከውዝዋዜና ሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ይቀርባል፡፡ እንዲሁም፣ሙዚቃና ውዝዋዜ የህብረተሰባችን የእምነት ስርዓት፣ ኢኮኖሚ፣ ባህልና ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የህብረተሰቡን ልምድ ለማሳደግና ለማስተሳሰር፤ እንዲሁም ባለቤትነት እንዲሰማውና እንድሳተፍ በማድረግ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

ሙዚቃና ባህላዊ ውዝዋዜ ጀግንነት፣ ለሃገሩ ፍቅር፣ የግል ችሎታ ማድነቅና ሌሎች ስዎች እንዲሰሩ ለማነሳሳትና ለማበረታታት ህብረተሰባችን ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህም ሌላ ውዝዋዜና የሙዚቃ ታሪክን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ፣ ለህብረተሰቡ ዕድገት፣ ለሀገር ፍቅርና ደስታ ለመባል እየተከፈለበት የነበረው ትንሽ የሚባል አይደለም፡፡

ውዝዋዜ እንደ ባህላዊ ሙዚቃ እሴቶችን፣ አመለካከት፣ አስተዳደር፣ ስነ-ምግባር፣ የህብረተሰቡ ባህል እሴትን በመግለጽና በመተካትም አልፎ በመዝናናት ላይ ያለዉ ድርሻ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ይህ ማለት ስሜት ፣ህሳብ፣ታሪክ መንገር፣ፖለቲካ፣ኢኮኖሚና እንድን የህብረተሰብ ፍላጎትን በዚሁ ጥበብ መግለፅ ይቻላል፡፡

በባህላዊ ውዝዋዜ የሚገለጸው ሌላው የባህል አልባሳት ነዉ፡፡ በዉዝዋዜ የሚሳተፍ ሰው በቡድንም ሆነ በግል የባህል ልብስ በመልበስ ይወዛወዛሉ፡፡ ሀገር በቀል የሆኑት የሙዚቃ መሳሪያዎችም ይሄንን ውዝዋዜ ለማሞቅና ለማነቃቃት ይረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ የአንድ ህብረተሰብ ሙዚቃ ገጽታ ባህላዊ ባህርይ፣የሙዚቃ መሳሪያዎችና ዉዝዋዜዎች ሲሚተነተኑ፤ በአካሉንና ህሊና በማቀናጀት መስራት የህብረተሰቡን የሀገር በቀል እዉቀትን ለማሳደግና ለማንከባከብ ያስችለላል፡፡

ይህ ማለት የባህል ልብስ አለባበስ ሁኔታ፣ የሚደረገው የሰውነት እንቅስቃሴ፣ በዘፈን የሚተላለፈው መልዕክትና ህብረተሰቡ የሚያካሄደውን ስርዓት በመጥቀም፤ በሰርግ ጊዜ፣ በክብረ በዓል ፣የስራን ዝግጅት ለማስጀመር፣ በምርቃት ጊዜ የህብረተሰቡ ማንነትን የሚገልጸው መሆን አለበት፡፡

እንዲሁም ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ውዝዋዜን ተጠቅመን የጋብቻ ስነ-ስርዓት ባህል ውስጥ ያለዉን አንድነት እንመልከት፡፡

ሙሽሪቷ የምታስተላልፈዉ የርህራሄ ዜማ(መረሮ) መልዕክት፡-
በወለጋ የኦሮሞ ህዝብ ባህሉን፣ ታርኩንና ማንነቱን በተለያዩ ሁኔታዎች ይገልጸዋል፡፡ የህዝቡን ባህል ብዙ ቢሆኑም፤ ለምሳሌ ባህላዊ ምግብ ፣የባህል አልባሳት፣ የጋብቻ ስነ-ስርዓት ፣የክብረ

በዓላት፣የመረዳዳትና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡
መረሮ በወለጋ ኦሮሞ ጋብቻ ስነ ስርዓት ወክት ባህል የሚዘፈን ሲሆን፤ በወንዶች በኩልም ሆነ በሴቶች በኩል ለሰው ማራራት ኃይል አለው፡፡ የአዘፋፈኑ ሁኔታም ሆነ መልዕክቱ ሰውን ሃዘንና ስሜት የሚገልፅ ነው፡፡ በአብዛኛው ጊዜ መረሮ ሴቶች ትንሿ ከበሮ በመምታት ይጫወታሉ፡፡ በጋብቻ መታጨት ስነ ስርዓት ላይ የሚጋቡ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት የሚጋቡ ከሆነ ወይም አንዲት ሴት ሳትፈልግ በሚያገቧት ጊዜ፤ ቅሬታዋን በመረሮ(በሚያራራ ዜማ) ትገልጻለች፡፡ ይሄንን ግን የሚትገልጸው በስጦታ ቀን ከጓደኞቿ ጋር በድብቅ ወደ ጓሮ በመዞር ክብ ሰርተዉ ያዜማሉ፡፡ ሲያዜሙ እንዲህ ያላሉ፡-

ዱጉጉሩ ያ ላፌ ሆላ x2
ስጉርጉሩ ያ ሮጌ እልሞማ x2
ስጉረጉሩ ናማራርቴቱ ማርሲ ቦአ
ፉሮ ቄሩማ ያ ሮጌ እልሞማ
ህዲ ሙራኒ ያ ሮጌ እልሞማ
ዳርባቻ ዴሙ ያ ሮጌ እልሞማ
ፉሮ ሱቡማ ያ ሮጌ እልሞማ
ጉፉ ባታኒ ያሮጌ እልሞማ
ዳርባማ ዴሙ ያ ሮጌ እልሞማ
ስጉርጉሩን ናማረረቱ ማርሲ ቦአ

ሀሮ ዳማቹ
ሂናን ሀማ ያ ካሎ፣
ሀን ሀፍን አጀራዱ፣
ሴናን ዳማ ያ ሃዳኮ
ሀን ራፍን ዳጌፋዱ
ዮ ራፍቴፍ ቃልቤፋዱ
ሀርምኮ ህን ባነ ኒቂቅጠ ማሌ
ያ አዮሌ ኮ
ላን ኮ ሀን ጌኘ
ያ አዮሌ ኮ
ና ቁፍተ ማሌ ኡሌ ጌሼ ሙሩ
ማፍ ና ላታ ሀዳኮ፤ አኖ ቤኬ ሀን ቡሉ
ያ አባዬ ኮ ያ አዮሌ ኮ
ማልቱ ማል ታኤ ካን ባዲ ታኤ
ጫባዎ ሀን ቱፋኔ
ዳርባዎ ሀን ዱባኔ
ያ አዮሌ ኮ
እዶ ጪሳኮ ጉምቢ ዳባዱ
ጫባ እርባታ ኮ ድልቢ ካዋዱ
ድባ ማታኮ ሳማ ካዋዱ

ያ ኦቦሌ ኮ፣ ጋድ ባኢቲ ጎርባት ሲክሳ
ጉያ ኬና ኮ ቶርቤት ሂክሳ
ጋፋ ቶርቤ ኮ ኩርኖት ሂክሳ
ጋፋ ኩሞ ኮ ማሊ ፉኞ ኮ

ዋዴሳ ቀኤ ሙርሙርቱ ሀን ሴኔ
ሙርሙርታኒሬ ጉድፍቱ እጆሌ
ሃሶፍቱ ቄኤ ጉርጉርቱ ሀን ሴን
ጉርጉርታኒሬ?
አን ጅአን ሰኤ ላፍቶ ሃልካኒ
አን ጅራን ሰኤ ናቶ ማልታኒ
ያ አዮሌ ኮ የሙ አን ጥኖ
ስሬ ዶዶፍቴ ኡሩሩ ጀታ
አማ ማል ጎናን ባርጩማ ሀጦፍቴ ቃርሺ
ላኮፍቴ ጉርጉሩ ጀታ?
ሆሪዳፍ ጀቴ ዳላኬ ጋታ?
ቃርሽ ቅራጪ ዳርባቴ ኬሳ ጉቹማ ኬሳ
ዳል ብላቲ ኤርጋቴ ቴሳ፤ ዱሉማ ኬሳ
ጉዱሩ ስርቡ ጌምቦ ዳድሱ
ኑን ዱሩ ጅቡ ኦቦ ጫልችሱ
ኦቦን ጋራዳ ኑት ሃላጋዳ
ኦቦን ካንሳኒ ኑሞ ማልሳኒ?
ሂንዳቆን ዳልቴ ቆጢ ጃላቶ
ኦቦሌ ዲሮ ናን ሱቃታኒ ኮቲ ጃላቶ
ኮቲን ካንኬት አን ማልኬቲ?

በማለት ለጋብቻ አሳልፈዉ በመስጠታቸዉ ቅሬታዋን ታሰማለች፡፡
በአጠቃላይ ለመዳር የተዘጋጀችሁ ሴት በመረሮ(በርሀራሂ ዜማ) ሃሳቧን የምትገልጸዉ የተለያየ ቢሆንም፤ ይዘቱ ግን ተቀራራብነት አለው፡፡

ጉንዶ ቦሬ
ጉንዶ ቦሬ ዲፍቴ ጋልታሞሬ
ያ ፉቱ ኤኙ አባን ጉንዶ ፉቱ
ካና ኬሳ ሚኑ ሀንጅሩ ቃቤ ማሌ
ካና ኬሳ ዲር ሀንጅሩ ሳሬ ማሌ
ያ ፉቱ ኤኙ አባን ጉንዶ ፉቱ
ጉንዶ ቦሬ ዲፍቴ ጋልታሞሬ
ጉንዶ ዲጋ ዲፍቴ ጋልታሞሬ
ጉሮ ዲራ ዲፍቴ ጋልታሞሬ
ያ ጉርብኞ ሉካ ጭቶ
ዲፍቴ ጋልታሞሬ
ናማ ቤላ ያካቤላ
ዲፍቴ ጋልታሞሬ

እንደ ህብረተሰቡ ባህል ጉንዶ ቦሬ የሚወስደዉ፤እልህ(ቦሬ) ያለዉ ሰዉእልህና ፉክክርን ይጠይቃል፡ ፡ ነዉ፡፡ እልህ(ቦሬ) ማጣት ስም እንደመጥፋት/ ሃፍረት እንደለለው ሰው ስለሚቆጠር፣ እንደምንም ተፎካክሮ መያዝ በጉንዶ ቦሬ ይባላል፡፡
በሌሎች ኦሮሚያ ዞኖች የሚታወቁ ባህላዊ ዘፈኖች አሉ፡፡ ለምሳሌ በአርሲ ዞን "ባኤ ባኤ" የሚባለዉ የሰርግ ዘፈን ሆኖ የሚታገባው ሙሽሪትና ጓደኞቿ የሚዘፈን ነው፡፡ እርሱ ከታች ባለው መልክ የሚያገቡትን በመተቸት ወይም በመስደብ የራሳቸዉን ደግሞ በማሞገስ ያዜማሉ፡፡

ባኤ ባኤ ጋራምባ ጨጫፈሜ
ባሳን ጌኛን ጋራን ኮ ና ራፈሜ...

## ተግባር 1

ስለ ሙዚቃ፤ የሙዚቃ መሳሪያና የውዝዋዜ ታሪክን በአከባቢያችሁ የሚገኙ ታላላቆችን በመጠየቅ ያገኛችሁን ሃሳብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## 3.2. የቅርፃ ቅርፅ (ሃዉልት) እና የጥንት ዘመን የእጅ ሙያ ታሪክ

### 3.2.1. የእጅ ሙያ ጥበብ ስራዎች

ውይይት 1

የእጅ ሙያ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ተወያዩ፡፡

የእጅ ሙያ ጥበብ ማለት በአጠቃላይ በሰው ልጅ የሚሰሩ ስራዎች፣ መሳሪያዎች ወይም የስነ-ጥበብ ስራ፤ በተለይ ለአርክኦሎጂ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችን የሚገልፁ ናቸዉ፡፡ በአርክኦሎጂ የእጅ መያ ስራ የሚባል ቃል በአጠቃላይ ለመሳሪያዎች የሚንጠቀማቸው እቃ የሚል ሲሆን፤ በስነ-ጥበብ ታሪክ ደግሞ የስነ-ጥበብ ስራ ይባላል፡፡

የእጅ ጥበብ ሙያ የተለያዩ ነገሮችን ይይዛል፡፡ ለምሳሌ፡- ከድንጋይ የተሰሩ እቃዎች፣ የሸክላ ስራዎች፣ ብረታ ብረት የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም፤ ጦር፣ ጌጣ ጌጥ፣ የልብስ ቁልፎች፣ እና ሌሎችም ሊሆን ይችላሉ፡፡

የእጅ ሙያ ስራዎች የባህሪይ ለዉጥ ዉጤት ነዉ፡፡ የባህሪይ ሂደት የጥሬ እቃ ግኝት፣ ወሳኝ የሆኑትን ነገሮችን ማምረት እና ከተጠቀምንባቸው በኋላ የሚወገዱት ጭምር ይይዛል፡፡ የለውጥ ሂደት ቀጣይነት ያለው ሲሆን፤ ይህም የእጅ ሙያ በተፈጥረዉ ወይም ሰዉ-ሰራሽ ነገር ስለሚገኝ ነው፡፡ ይህ ሁለቱ ሂደቶች የእጅ ሙያ ስራዎች ይዘት ቅድመ ሁኔታዎችን ለመመዘን ያስፈልጋል፡፡

### 3.2.2. ሞኑመንት

ውይይት 2

ሞኑመንት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን ተወያዩ፡፡

ሞኑመንት ማለት የቤት አሰራር ወይም የአንድ ህብረተሰብ ጥንታዊ/ታሪካዊ ክንዉን ነዉ፡፡ ሞኑመንት ለታሪካዊ ነገር ወይም ታሪካዊ ቅርስ በጥበባዊ፣ ታሪካዊ፣ የፖሎቲካ መልዕክቶች እና ጥቅም ቀላል በሆነ አሰራር ለማስታወስ የሚሰራ ነው፡፡ ሞኑመንት የተለያዩ ስራዎችን ይይዛል፡፡

ለምሳሌ፡-የመታሰቢያ ሃዉልት፣ ሃዉልት፣ ታሪካዊ ግንባታ፣ የአርክኦሎጂ ቦታዎች፣ ቱባ ባህሎች እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ሞኑመንት የሚል ቃል ከላቲን ቋንቋ የመጣ ሲሆን፤ ትርጉሙም ማስታወስ ወይም መምከር ማለት ነዉ፡፡ ሞኑመንት ያለፈዉ ነገር ለምን ሲጠቀሙ እንደነበረ ግንዛቤ በማስጨበጥ፤ የወደፊቱን ደግሞ በደንብ አይተን ምን እንደሚሆን ለመገመት ይረዳናል፡፡ ለምሳሌ የመታሰቢያ ሃዉልት በህይወት የለሉትን ነገሮችን ለትውስታ የሚሰራ ነው፡፡

ሞኑመንት ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያየ ቦታዎች ረጅም እድሜ ያላቸው ሆነዉ፤ የሰው ልጅ የጥንት ስልጣኔ እድገት ማሳያ ነው፡፡ ስለዚህ በጥንት ዘመን የተሰሩ ትልልቅ የሆኑ ሞኑመንት በአከባቢ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር ብዛት ያላቸው እና ምንያህል በስልጣኔ እንዳደጉ እንደሆኔ የሚያሣይ ነው፡፡

ለተለያዩ ጉዳዮች የተሰሩ ግንባታዎች ከእዉቅና፣ እድሜ፣ መጠን እና ታሪካዊ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ ሞኑመንት ይቆጠራሉ፡፡ ምክንያቱም ረጅም እድሜ ያስቆጠረ እና በመጠን ትላልቅ ስለሆኑ ናቸዉ፡፡ እንዲሁም አስፈላጊነቱ እና የጥንት ዘመን እና ታሪካዊ ከመሆናቸዉ የተነሳ ነዉ፡፡ ብዙ ሃገራት ሞኑመንት እና በጥንት ዘመን የተሰሩት ሌላ ነገሮች የተጠበቁ ግንባታ እና ክነ-ህንፃ ስራዎችን ለማሳየት ያገለግላል፡፡

ሞኑመንት ታሪካዊ የሆኑ እና የፖሎቲካ መልዕክት ለማስተላለፍ ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም የህብረተሰቡ ወሳኝ ክንውኖች ለማስተማር ይረዳል፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልቶች አንደ ታሪካዊ ቅርስ ይቆጠራል፡ ፡ ነገርግን በጦርነት ወይም ከግጭት የተነሳ ታሪካዊ ቅርሶች ልወድሙ ይችላሉ፡፡

ሞኑመንት ብዙ ነገር ይይዛል ከነዚህ የተወሰኑትን እንመልከት፡-

- የመታሰቢያ ሃዉልት
- ሃዉልት
- በጥንት ጊዜ የተሰሩ ቤቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### ሀ. የመታሰቢያ ሃዉልት

ውይይት 3

የመታሰቢያ ሃውልት ማለት ምን እንደሆነ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች እና መምህራችሁ አቅርቡ፡፡

የመታሰቢያ ሃውልት ብዙ ጊዜ በህይወት ለሌሉ ሰዎች እና እንስሳቶች በአደባባይ የሚቆም/የሚሰራ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በህብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት፣ክብር፣እዉቅን እና ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ማለትም የሃገር መሪዎች፣ ጀግኖች፣የተለያዩ ግኝቶችን ያገኙ ሰዎች፣ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰዎች እና ለመሳሰሉት እሴት፣ታሪክ፣እዉቀት፣ጀግንነት እና መሪነታቸዉን ለሚቀጥለው ትዉልድ ለማስተላለፍ የሚሰራ ነው፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ሰዎች ከተሰው/ህይወታቸው ካለፈው በኋላ፤ የሚሰራ ቢሆንም፤ በሕይወት ላሉ ሰዎችም ሊሰራ ይችላል፡፡

የመታሰቢያ ሃዉልት ቅርፃ ቅርፅ የሚሰራበት ዘዴ ቢሆንም ልዩነት ይኖራቿል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ሲንል የስነ-ጥበብ ስራ ሆኖ ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ያለዉ ወይም ጠጣር የሆነው በእጅ የሚዳሰስ እና ዙሪያውን

በመዞር ማየት የሚንችል ነው፡፡ ነገር ግን ቅርፃ ቅርፅ ሲንል ጥበባዊ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሙሉ በሙሉ በባለ ሙያ/የፈጠራ ችሎታ በቀራፂ የሚሰራ ነው፡፡ ይህ የፈጠራ ስራ የመታሰቢያ ሃውልት መስራት ውስጥ አይታይም፡፡

የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ከሸክላ አፈር፣ድንጋይ እና ብረታ ብረት/ ከነሃስ ይሰራል፡፡ ቅርፃ ቅርፅ ደግሞ የስነ-ጥበብ ስራዎች የሚሰራበት ዘዴ ሆኖ፤ ቁመት፣ወርድ እና ርዝመት ያለዉን በእጅ የሚዳደስ ሲሆን፤ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ለመስራት ከሚያገለግሉ ሁሉም የሚሰራ ነዉ፡፡

የመታሰቢያ ሃውልት ስራ ሙሉበሙሉ በተፈጥሮ ያለውን ነገር በማስመሰል የሚሰራ ሲሆን፤ የሃውልት ስራ ደግሞ በተፈጥሮ ያለውን ነገር በማስመሰል የሚሰራ ቢሆንም፤ የተፈጥሮ ችሎታን ያካተተ ነው፡፡ ቀራፂ የሚሰራ የቅርፃ ቅርፅ ስራ ተመልካችን እንዲስብ/ማራኪ እንዲሆን ለማድረግ የተለያዩ ነገሮችን ይጨምርበታል፡፡

ሃውልት እና የመታሰቢያ ሃዉልት ልዩነታቸው በመጠናቸዉ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የመታሰቢያ ሃዉልት በመጠን ተለቅ ተደርጎ ይሰራል፡፡ በትንሹ የሚሰራ ከሆነም በተፈጥሮ ልክ መሆን አለበት፡፡ ሃውልት ግን በመጠን የሚወሰን አይደለም፡፡ ወሳኙ የቀራፂዉ ትኩረት ሃሳቡን እንዴት ሊገለፀው፣ በምን ልስራ፣ ከሰራዉ በኋላ ቅርፃ ቅርፁን የት አቆማለው? የሚለው ነገር ነው እንጂ፤ እንዴት ልስራ በሚለዉ ሃሳብ አይገባዉም፡፡ ይህ ማለት የሚያስተላልፈውን መልዕክት መጨመር እና ማነስ በተሰራ ነገር አይወሰንም፡፡

ቅርፃ ቅርፅ አንድን ነገር የሚገልፅ አጠቃላይ ፎርም ወይም ምስል የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚመስለዉን አስመስለን በመስራት፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት ግን ሁልጊዜ የአንድን ነገር ምስል፤በተፈጥሮ ያለዉ ወይም የነበረውን እንዳለው ለማስመሰል፤ የሚሰራ ሊሆን ይችላል፡፡ ምስል ስንል ደግሞ፤ ለምሳሌ፡-የሰዉ የመታሰቢያ ሃዉልት የሚንሰራ ከሆነ፤ሰው በተፈጥሮ ያለዉን ነገር ሁሉ አስመስለንመስራት አለብን፡፡



ስዕል.3.1.የአባገደና ሀደ ሲንቄን የምየሰይ ሃዉልት

ውይይት 4

በአከባቢያችሁ የመታሰቢያ ሃዉልት ካለ፤ ለምን መታሰቢያነት እንደተሰራ በቡድን በመወያየት ለክፍል አስረዱ፡፡

## ለ. የድንጋይ ሃዉልት

ውይይት 5

ሃዉልት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን በመወያየት ለክፍል አስረዱ፡፡

የድንጋይ ሃውልት ሁል ጊዜ ቀጭን እና በቁመት ረጅም ሆኖ ይሰራል፡፡ ለኃይማኖታዊ፣ ፖሎቲካ፣ ባህል፣ ለበላይነት፣ እሴት እና ሌሎች ምልክቶችን ለማሳየት የሚሰሩ ናቸዉ፡፡ በአንዳንድ ቦታ ህብረተሰቡ ለንጉስ ያላቸዉን ክብር ለማሳየት ንጉሱ ሲሞት በመቃብራቸዉ ላይ የሚያቆሙት ነዉ፡፡ ሃዉልት ስዕል አይደለም፡፡ የአንድን ነገር አጠቃላይ ፎርም የሚያሳይ ነዉ፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት እና የድንጋይ ሃዉልት ልዩነት፤ የድንጋይ ሃዉልት ፎርም ሲሆን የመታሰቢያ ሃዉልት ደግሞ በተፈጥሮ ያለዉ/ የነበረዉን ነገር ምስል ነዉ፡፡ እንደ ሃገር ከሚታወቀዉ የድንጋይ ሓውልት ዉስጥ አንዱ የአክሱም ሃዉልት ነዉ፡፡

በአክሱም የተሰሩ ሃዉልቶች በአብዛኛው ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለዉ የተሰሩት ናቸዉ፡፡ ምክንያቱም የፎርሙ ግንባታ ዉበት በባህላዊ ዘዴ በመጠቀም መሰራቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡

አክሱም ዉስጥ ብዙ ሃዉልቶች ነበሩ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የሚቆሙ/ያሉት በቁጥር ትንሽ ናቸዉ፡፡ ብዙዎች ተሰባብረዋል፡፡ ምክንያቱም የአሰራር ጥራት፣ በዱሮ ጊዜ በተከሰተው የእሳት ጎመራ ፍንዳታ እንዲሁም የጣሊያን ጦር በአድዋ ላይ ከመሸነፉ ጋር በተያያዘ አፀፋ ለመመለስ ባደረሰችበት ጥቃት ለ2ኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ስወሩ፤ ሃዉልቶች እና የተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶችን አውድሞ ስለነበር ተጎድቷል፡፡

አሁን በአክሱም ቆመዉ የሚገኙ ሃዉልቶች ዉብ እና ረጅም የሆነ፤ ርዝመቱ ሃያ አራት (24 ሜትር) እና አንድ መቶ ስድሳ (160 ቶን) የሚመዝን ነው፡፡ ይህ ሃውልት በውብ ሁኔታ የተሰራ እና ሰውን የሚስብ ነው፡፡ የመግቢያ በር ዲዛይን የተሰራዉ በሁለቱ በኩል እንዲሁም መስኮትን የሰሩት በሁሉም አቅጣጫ ሲሆን፤ በጫፍ ላይ ደግሞ ጎበጥ ያለው ፎርም የተዋበ ነው፡፡ የአክሱም ሃዉልት ለነገስታት መታሰቢያነት የቆሙ ነው፡፡



ስዕል. 3.2. የአክሱም ሃዉልት

## ተግባር 2

በአከባቢያችሁ የተሰራ ሃዉልት አለ? ካለ የምን ሃዉልት እንደሆነ እና ለምን እንደተሰራ ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ወይም ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል አቅርቡ ፡፡

## ሐ. የጥንት ዘመን ቤቶች

## ተግባር 3

በአከባቢያችሁ በጥንት ዘመን የተሰራ ቤት አለ? የጥንት ዘመን ቤት ምንነት እና ለምን እንደተሰራ ቤተሰቦቻችሁን ወይም ታላላቅ ሰዎችን በመጠየቅ ለክፍል አቅርቡ፡፡

በሃገራችን የተሰሩትን ጥንት ጊዜ ቤቶችን ሲንመለከት፤ በተለያዩ ቦታ የሚገኙ ቤተ-እምነቶች እና ቤተ-መንግስት ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ብዙ ስለሚገኙ ነው ፡፡


ይህ ቤቶች ወጥ ከሆነ ድንጋይ የተቀረፁ ሲሆኑ፤ በአብዛኛው በትግራይ እና በወሎ ላሊበላ ይገኛሉ፡፡ በትግራይ የሚገኝ ከድንጋይ የተቀረፁ ቤቶች የክርስትና እምነት ወደ ሃገራችን ሳይገባ በፊት የተሰሩ እና ለተለያዩ እምነት ጉዳዮች ሲገለገሉበት ነበር፡፡

በወሎ ላሊበላ አከባቢ ከአንድ ድንጋይ የተወቀረ ቤተ-እምነት መሰራት የተጀመረው፤ በ6ኛ ክፍለ ዘመን እንደሆነ ታሪክ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ያገኘው፤ በአብዛኛው በአንድ ቦታ መሰራት የጀመረው በ12ኛ ክፍለ ዘመን በላሊበላ ንጉስ ጊዜ ነበር፡፡የላሊበላ ንጉስ ከተለያየ ምክያቶች ጋር ተያይዞው፤ በአንድ ቦታ የሚገኙ ቤተ-ክርስቲያን ከአሳተ ጎመራ ድንጋይ ተፈልፍለው ሲሰራ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል፡፡

ቤተ-እምነቶችን ከድንጋይ ተዋቅሮ የሚሰሩበት ምክንያት፤ ጥንካሬ ስላለው እንዲሁም አደጋን እና የተለያዩ ሁኔታዎችና መቋቋም ስለሚችል ነው፡፡ ይህንን ቤተ-እምነት ልዩ የሚያደርገው ቤት ሲሰራ ከመሰረቱ ወደ ላይ ይሰራል፡፡ ይህ ግን ተቃራኒ የሚሰራ ነው፡፡ ወደ ታች እየተሰራ የሚሄድ እና በመጀመሪያ ከላይ ያለው ይሰራሉ፡፡ በመቀጠል፣ዝናብ ማስተላለፍያ፣ መስኮት፣ በር እና የመሳሰሉትን እያሉ ወደ ታችየተሰራ ነው፡፡

በላሊበላ የሚገኙ ቤተ-እምነቶች በሆነ በኩል ከድንጋይ ጋር የተያያዙት ሆነው በሆነ ድግሪ ፈቀቅ ብለዉ ይገኛሉ፡፡ ይህ ማለት መሰረታቸው እና በአንድ በኩል ከተፈለፈለበት ድንጋይ ጋር ተያይዟል፡፡ እንዲሁም እራሳቸውን ችለው የቆሙ እና በሁሉም አቅጣጫ መታየት የሚችሉም ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለዉ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የሚገኙ ቤተ-እምነቶች የሆኑት በላሊበላ ንጉስ ጊዜ የተሰሩ በቁጥር አስራ አንድ (11) ናቸው፡፡ የላሊበላ ንጉስ ይህንን ቤተ-እምነት ለማሰራት ሃያ አራት (24 ዓመታትን) ፈጅቷል፡፡



ስዕል.3.3. የላሊበላ ቤተ-እምነት የሚያሳይ ምስል፡፡

## 3.3 በአከባቢያችን የሚታወቁ ተረቶችን በትያትርና ፊልም ጥበብ መልክ ማቅረብ

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ የትምህርቱ ርዕስ መጨረሻ ላይ  ፡

- በአከባቢያችሁ የሚታቁትን ተረቶችን ወደ ትያትር ትቀይራላችሁ፡፡
- የተረት-ተረት ምንነትትራደላችሁ፡፡

### መግቢያ

ማንኛዉም የስነ-ጥበብ ሥራ ከማህበረሰብ ኑሮ ጋር ተዘማጅነት እንደለዉ ባለፊዉ ትምህርት ዉስጥ ተምራቿል፡፡ የስነ-ጥበብ ሥራ ለማስራት መነሻ ሀሳብ በምን ላይ እንደምንሰራ ከህበረሰባችን ነዉ፡፡ ስለዚህ በዚሁ ምዕራፍ የኦሮሞ ስነ-ቃል ወደ ትያትር በመቀየር ማህበረሰብን ለማስተማር ነው፡፡ እንዲሁም የማናዉቀዉን ደግሞ በመጠየቅ  መማር ይቻላል፡፡

**ተግባር 4**

በትያትር መልክ ማቅረብ የሚቻለውን ተረት እርስ በርሳችሁ በመነጋገር፡፡ ወደ ትያትር ቀይራችሁ ተዊኑ፡፡

ባለፈው ክፍለ ጊዜ እንደ ተማራችሁት፣ ስነ-ቃል ማለት የማህበረሰብ ቅርስ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም የአዕምሯችን ፈጠራ ችሎታ፣ ማንነት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ የማህበረሰብ አኗኗር የምያፀባርቅ ነው፡፡ ይህ ቅርፅ  ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው በቃል ወይም በተግባር በመተግበር

ሲሆን፣ የሚረሳና እንደ አዲስ የሚፈጠር፣ የሚቀያየር መሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መቀያየሩ የስነ-ቃል ዋኛው ባህሪይ ነው፡፡ ስለሆነም ስነ-ቃል ደግሞ የማህበረሰብ ሰለሆነና የፈጠራ ችሎታና ጥበብ ስለሚፈልግ በጥበብ ሥር ይመደባል፡፡ ይህ ደግሞ ስነ-ቃል በማህበረሰብ ውስጥ በተላያየ አቅጣጫ ትምህርት የሚያስተላልፍ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸውም በስነ-ቃል በመጠቀም ማህበረሰቡ እራሱን ያስተምራል፣ የማህብረሰብ እሴቶችን ያስተካክላል፣ ያሻሽላል፣ ስለ ማንነቱና ስለ ታሪኩ ለዓለም ያስተዋውቃል፣ ያዝናናል፡፡ በተጨማሪም የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ታምሳሌት፣ የሃይማኖት ስርዓተ-ህግና የፖለቲካ ሁኔታው መሠረት ያደረገው ስነ-ቃልን

በዚህ ምዕራፍ ማስተዋል የሚገባን የኦሮሞ ስነ-ቃል በትያትር መልክ መቅረብ መቻሉንና ይህንኑ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የምታወቁ ስነ-ቃላትን ከቤተሰቦቻቸው ወይም ከሌሎች በመጠየቅ በትያትር መልክ ክፍል ውስጥ ማቅረብ ወይም በትወና መልክ ለትርዕት እንዲያቀርቡ የሚል ሃሳብ ላይ የምያተኩር ነው፡፡ በዚህም የስነ-ቃል መስኮች የሆኑትን እንደ ተረት፣ ቀረርቶ፣ ዘፈን እና አፈ-ታሪክን በትያትር መልክ በመተወን እርስበርሳቸዉ እንድማማሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለዚህም የሚከተለውን እንደ ምሳሌ መዋቀስ ይቻላል፡፡

## የእርግማን ልጅ

ሦስት ልጆች ያሉ ሽማግሌ ነበሩ፡፡ ከሦስቱ የመጀመሪያ ልጃቸው በጣም ተዛኸኘ ነዉ፣ እንዲሁም የምያደርግለት እንክብካቤና ክብር ከሁለቱም ልጆች የተለየ ነው፡፡ ሲጠራ ይታዘዛል፣ ሲላክ ያለ ምንም እንብተኝነት ይላካል፡፡ አባቱም በጣም ይወዱታል፡፡ የሁለተኛ ልጃቸው ደግሞ እንደ መጀመሪያ ልጅ ባይሆንም ከመጨረሻ ልጅ ትንሽ የተሻለ ነው፡፡ የመጨረሻ ልጅ ደግሞ ሁለቱ ወንድሞቹ በሚያደርጉት የተለየ ነው፣ ሲጠራ አይተዘዝም፡፡

ይህ ተረት/ስነ-ቃል ወደ ትያትር ሲቀየር እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሽማግሌዎች፡ ልብ በል መሞትህ ሰለማይቀር፣ በኋላ የአባታችን ንብረት ነው ብለዉ እርስበርሳቸዉ ስለሚጋጩ፣ሳትሞት ንብረትህን ለልጆችህ አካፍል፡፡

የልጆቹ አባት፡ይሁን! ነገር ግን ንብረቴን እንደ ሥራቸው አካፍላቿለሁ፣ በግራና በቀኝ ያለው ህዝብ ይወቅ !

ሽማግሌዎች፡ ተዉ! እንደ አገልግሎታቸው ሳይሆን፣ ሦስቱም ልጆችህ ሰለሆኑ ያለህን ንብረት እኩል አካፍልላቸው!

የልጆቹ አባት፡አካፋልላቸዋለው! ነገር ግን ሲያካፍልላቸዉ ዝም ብላችሁ

አዳምጡኝ! እናንተም እንደላችሁ ንበረት ላይ እንዳይጣሉ አከፍላቸዋለሁ!

ሽማግሌዎች፡ እሺ!

የልጆቹ አባት፡፡ዘየመጀመሪያ ልጄ ሁሉንም መሬት፣ቤቱንም ጨምሮ ይዉሰድ!

ሽማግሌዎች፡የሁለተኛ እና ሦስተኛ ልጆችህ ምን ይሁኑ?

የልጆቹ አባት፡ የሁለተኛ ልጄ ከብቶቼን እና እህል በጠቅላላ ሰብስቦ ይዉሰድ !

ሽማግሌዎች፡ የመጨረሻ ልጅ እሱም ልጅህ ነዉ፣ ንበረትህን በሙሉ ለሁለተኛና ለሦስተኛ አካፍለሃል ለእሱ ምን አስቀርተሃል፣ ወይስ ያንተ ልጅ አይደለም ?

የልጆቹ አባት፡:አዎ ልጄ ነዉ !

ሽማግሌዎች፡ታዲያ በምን ይኑር? እሱም የአባቱን ውርስ ማግኘት ስላለበት፣ለሁለቱ ልጆች

ከካፈልከው ውጪ ንብረት አለ እንዴ?

የልጆቹ አባት፡: ሌላ ንብረት የለም፤ ነገር ግን የአባት ንብረት ማግኘት አለበት ካለቹኝ እንግዲህ በለፈው ሃኪም ቤት ሂጄ ሁለት መቶ ፍሬ መድሃኒት እና መቶ መርፌ ታዞልኝ

ነበር እሱን ይውረስ ፡፡

ይህ ተረት በተውኔት መልክ ስለቀረበ አስተማሪ ነዉ፡፡ ተረድታቸዋል አይደል? ስለዚህ በአከባቢያችሁ የሚታቁትን ተረት በመውሰድ ወደ ትያትር እና ፊልም ጥበብ መቀየር ትችላላችሁ፡፡

## የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ

- ሞኑመንት ማለት የቤት አሰራር ወይም የአንድን ማህበረሰብ የጥንት ዘመን ክንውን ነው፡፡
- ሞኑመንት የሚለው ቃል ከላቲን ቋንቋ የመጣ ሲሆን፤ ትርጉሙም ማስታወስ ወይም መምከር ማለት ነው፡፡
- ሞኑመንቶች ያለፉት ታሪክ ምን እንደሚጠቅሙን ግንዛቤ በመፍጠር፤ የወደፊቱን ደግሞ በደንብ አይተን እንዲንገምት ይጠቅማል፡፡
- የመታሰቢያ ሃዉልት አብዛኛው ጊዜ ሰዎች በህይወት ካለፉ በኋላ የሚሰሩ ናቸው፡፡
- ቅርጻ ቅርጽ ሲንል አጠቃላይ የስነ-ጥበብ ስራዎች ሆኖ፤ ቁመት፣ርዝመት እና ወርድ ያለው ወይም ጠጣር ነገር እና በእጅ መዳሰስ የሚንችል እንዲሁም በሁሉም አቅጣጫ ዞረን ማየት የሚንችል ነው፡፡
- የመታሰቢያ ሃዉልት ብዙ ጊዜ ከሸክላ አፈር፣ ድንጋይ እና ብረታ ብረት/ነሃስ በመጠቀም የሚሰራ ነው፡፡
- ቅርጻ ቅርጽ እና የመታሰቢያ ሃዉልት ልዩነት አንዱ መጠናቸው ነው፡፡
- ቅርጻ ቅርጽ አንድን ነገር ፎርም የሚገልጽ ወይም በተፈጥሮ ያለውን ነገር ምስል እንዳሌ በማስመሰል የሚሰራ ሊሆን ይችላል፡፡
- የመታሰቢያ ሃዉልት ግን ሁልጊዜ የአንድን ነገር ምስል፣በተፈጥሮ ያለዉ ወይም የነበረዉን በማስመሰል ይሰራል፡፡
- ሃዉልት ሁልጊዜ ቀጭን ሆኖ፤ በቁመት ደግሞ ረዥም ተደርገዉ ይሰራል፡፡
- እንደ ሃገራችን የሚታወቁ ሃዉልቶች አንዱ የአክሱም ሃዉልት ነው፡፡
- በአክሱም የተሰሩ ሃዉልቶች በአብዛኛው፤ ከአንድ ወጥ ድንጋይ በመሮ በመፈልፈል የተሰሩ ናቸው፡፡
- ቤተ-እምነት ከድንጋይ ተቀርፀው/ተፈልፍለው የሚሰራበት ምክንያት ጥንካሬ ስላለው እንዲሁም አደጋ አእና ማንኛውም ሁኔታ መቋቋም እንዲችል ነው፡፡.

- በላሊበላ የሚገኙ ቤተ-እምነቶች በአብዛኛው ስንመለከት፤ በሆነ አቅጣጫ ከድንጋይ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡
- በታሪክና የባህል ኩነት ተጠቅመን በትያትር እና ፊልም ታሪክን መፍጠር እንችላለን፡፡
- የታሪክና ባህልን በማገናኘት የማህበረሰቡን አኗኗር አዘል የሆነውን ነገር በትያትር እና ፊልም ማቅረብ ይቻላል፡፡
- ተረት በስነ-ቃልና የህብረተሰባችን ባህል ውስጥ ያሉትን በመጠቀም ወደ ትያትር ጥበብና ፊልም መቀየር እንችላለን፡፡
- በአጠቃላይ የአከባቢያችን ባህልና ታሪክ በተጨባጭ ሁኔታ በትያትር እና በፊልም መተወን ይቻላል፡፡

## የምዕራፍ 3 መልመጃ

ሀ. ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች የተሰጠው ሃሳብ ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ሞኑመንት የተለያዩ ስራዎችን በውስጡ ይያዛል፡፡
2. ሞኑመንት ወደ ፊት የሚሆኑ ነገሮችን እንዲንገምት ያረገናል፡፡
3. የመታሰቢያ ሃዉልት በህይወት ያለፉትን ነገር ለማስታወስ ይሰራል፡፡
4. ሞኑመንት በቅርብ ጊዜ የተሰሩትን ስራዎችን ይይዛል፡፡
5. የመታሰቢያ ሃዉልት ለእንስሳት አይሰራም፡፡
6. ቅርጻ ቅርጽ ቁመት እና ርዝመት ብቻ አለዉ፡፡
7. ቅርጻ ቅርጽ ሙሉ በሙሉ የሰዉ ልጅ የፈጠራ ችሎታ ዉጤት ነዉ፡፡
8. አብዛኛው ጊዜ የመታሰቢያ ሃዉልት በመጠን ተለቅ ተደርገው ይሰራል፡፡
9. የመታሰቢያ ሃዉልት ስዕል ነው፡፡
10. ሃዉልት ሁልጊዜ ቀጭን እና በቁመት ረዘም ተደርገው የሚሰራ ነው፡፡
11. በማህበረሰብ ውስጥ ያለው ተረቶችን ወደ ትያትር መቀየር አይቻልም፡፡

12 በታሪክና ባህል ተጨባጭነት ትያትር ከፊልም ጋር ተዘማጅነት የላቸዉም፡፡

13. በፊልም ጥበብ ታሪክ ማስተማር ቢቻልም ነገር ግን በትያትር ጥበብ ማስተማር አይቻልም፡፡

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡

1. በሞኑመንት ሥር የማይመደብ የቱ ነው?

   ሀ. የመታሰቢያ ሃዉልት ለ. ንድፍ

   ሐ. ታሪካዊ ግንባታ መ. ሃዉልት

2. የእጅ ስራ ጥበብ ያልሆነ የቱ ነዉ?

   ሀ. ከድንጋይ የሚሰሩ ነገሮች ለ. የሸክላ ስራ

   ሐ. ከብረት የሚሰራ ስራዎች መ.መልስ አልተሰጠም፡፡

3. ሞኑመንት ማለት ምን መለት ነዉ?

   ሀ. ማስታወስ ለ. መምከር

   ሐ. ማዳመጥ መ. "ሀ እእና ለ መልስ ናቸው፡፡

4. ከሚከተሉት ውስጥ በተለይ የመታሰቢያ ሃዉልት ለመስራት የማያገለግል የቱ ነው?

   ሀ. እንጨት ለ. ድንጋይ

   ሐ. ብረት መ. የሸክላ አፈር

5. የመታሰቢያ ሃዉልት በተመለከተ እውነት የሆነ የቱ ነው?

   ሀ. ሁልጊዜ በመጠን ተለቅ ተደርገው የሚሰራ መሆኑ፣

   ለ. የሚሰራበት ነገሮች ትንሽ እና የተወሰነ መሆኑ፣

   ሐ. በፎርም መልክ የሚሰራ መሆኑ ነው፡፡

   መ. ስዕል መሆኑ ነዉ፡፡

6. በአከባቢያችን የሚገኙ ስነ-ቃል ሁሉ ትያትር መሆን ይችላል፡፡

   ሀ.ሐሰት ለ.እውነት

7. በታሪክና ባህል በተጨባጭነት ትያትርና ፊልምን ለማስተሳሰር ድርሻ ያለው ምንድነዉ?

   ሀ. ተረት ለ. አባባል ሐ. ስነ-ቃል መ. ሁሉም

8. ከሚከተሉት ውስጥ በስነ-ቃል ስር የሚመደበው የትኛው ነው?

   ሀ.ቀረርቶ ለ .ተረት ሐ. አባባል መ.ሁሉም

9. የስነ-ቃል ጥቅም የትኛው ነው?

   ሀ. ለማዝናናት ለ. ሃሳብን ለመግለፅ ሐ. ለማስተማር መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

10. ስነ-ቃል ከትያትርና ፊልም ጋር መተሳሰር የሚችለው በምን ሁኔታ ነው?

   ሀ.ስሜትን በማንፀባረቅ ለ. በትወና ሐ.ታሪክን በመግለፅ መ. ሁሉም

# ምዕራፍ 4
# የስነ-ጥበብ መስህብነት

## የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤቶች፡

የምዕራፉን ትምህርት ተምራችሁ ከጨረሳችሁ ቦኋላ፤

- በተግባር የምቀርቡ ስነ-ጥባባትን ታናጻጽራላችሁ፡፡
- በአቀራረብ ስልቶቻቸዉ ላይ ያላቸዉን ልዩነት(ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትርና ፊልም ስነ-ጥበባት) ትለያላችሁ፡፡
- የሃዉልት ምልክቶች የሚያስተላልፉ መልዕክት ታስረዳለላችሁ፡፡
- የሃዉልት ስራ የሚሰራበትን ጥቅም ትነግራላችሁ፡፡

## መግቢያ

በለፈው የትምህርት ውስጥ የስነ-ጥበብ ዓይነቶችን መማራችሁ ይታወቃል፡፡ ሁሉም የስነ-ጥበብ ዓይነቶች በአቀራረበቸው እና በተደረሽነታቸው ልዩነት ብኖራቸውም ለማህበረሰቡ ከሚሰጡት ጠቃሜታ አንፃር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በተግባር የሚቀርቡ ስነ-ጥባባትን በማነፃፀር ትማራላችሁ፡፡

የስነ-ጥበብ ሥራዎች ውበት ያላቸውና የማሳብ ባህሪይ ያላቸው ስራዎች ናቸው፡፡ ጥበብ ከሰዉ ልጅ ጋር ትስስር ስላለዉ ሰዎችን ለማሳብ ጥልቅ ሚና አለዉ፡፡ ለምሳሌ ማንኛዉንም ፊልም ተመልክታችዉ የፊልሙ ዋና ገፀ-ባህርይ የምያሳየዉን ባህሪይ ወይም ስራዉን በመዉደድ መመኘታችሁ አይቀርም፡፡ ሰለዚህ የሙዚቃ ስራና የእይታ ጥበብ (ስነ ጥበብ) ከሌሎች ስራዎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸዉ፡፡ አንድን የጥበብ ሥራ ተመልክተን እንዲንወድ ያደረገዉ እንዲሁም እንዲናደንቅ ያነሳሳን አንዱ የጥበቡ ዉበት ነው፡፡

በተግባር የምከናወኑ ወይም የምታዩ ድርጊቶች በጽንስ ሀሳብ ከሚገለፁት ጋር ሲታዩ ልዩነት አላቸው፡፡ ምክንያቱም በዓይናችን ስላየንና ስለ አዳመጥን እንዲሁም ለመማርም ጉልበትና ግዜያችንን ይቆጥብልናል፡፡ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ ሀሳብ ትምህርት ውስጥ እንደ ተማራችዉት ሥዕል ተጠቅማቸዉ መደመርና መቀነስ ተምራቸዋል፡፡ምክንያቱም በተግባር ወይም በስነ-ቅርፅ ስቀርብ ተማሪዎች በቀላሉ አይተዉ በተጨባጭነት እንዲረዱ ይጠቅማቸዋል፡፡

ባለፈዉ ትምህርት ርዕስ ውስጥ ተዉኔትና የፊልም ጥበብ ተጠቅመን በትረካና በአፊ-ታሪክ መልክ ማስተማርና በሥነ-ጽሑፍ ማስተማርየሕጻናትንአእምሮ እንደሚንቀርፅ ተምራቸዋል፡፡

## 4.1. የስነ-ጥበባት ስራዎችን በተግባር የማስተማር ጥቅሞች

**ተማሪዎች ቢያንስ መነናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች :

- የስነ-ጥበባት ጥቅምን ትዘረዝራላችሁ፡፡

ስነ-ጥበባት በምንጠቀምባቸው ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተለያዩ ጥቅሞች አላቸው፡፡ ይህም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በዕድገትና ልማት ውስጥ እና በጤና አጠባበቅ ውስጥ ስነ-ጥበባት የሚሰጡት ጥቅሞች የሚደነቁ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የፈጠራ ችሎታዎችን ለማዳበር የስነ-ጥበባት ስራ ከፍተኛ ጠቃሜታ አለው፡፡ ከዚህም በላይ የስነ-ጥበባት ችሎታና ፍቅር ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለማህበራዊ ግንዘቤና ለመሳሳሉት ከፍተኛ ጠቃሜታ ስላላቸው ስነ-ጥበባትን በቅርፃ ቅርፅ፣ በሙዚቃና ውዝዋዜ፣ በትያትርና ድራማ እና በመሳሳሉት መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡

**ተግባር 1**

በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ስነ-ጥበባት የሚሰጡትን ጥቅሞች በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4.2. በተግባር የምታዩ ስነ-ጥበባትን ማነጻጸር (ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ፣የትያትር እና የፊልም ስነ-ጥበብ)

**ተማሪዎች ቢያንስ መነናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች :

- የትያትር ጥበብ ከሌሎች ጥበብ ጋር ያለዉ ግንኙነት ትረዳላችሁ፡፡

### 4.2.1. ትያትር ከሌሎች የስነ-ጥበብ ትምህርት ጋር ያለው ትስስር

የስነ-ጥበብ ዓይነቶች ሁሉ (ውዝዋዜ፣ ሙዚቃ፣ስነ-ቅርፅ እና ሌሎች) በፕሮዳክሽን ውስጥ የሚያስተላልፉት መልዕክት፣ በተዋንያን አቀራረብ፣በድርጊትና በመቼት ባህሪያቸው ከትያትር ጋር የምያመሳስላቸው ባህርይ አላቸው፡፡ ማንኛዉም የስነ-ጥበብ ዓይነት ከትያትር ጥበብ ጋር የምያዘምዳቸዉ ተጨባጭ ልምድ አሏቸዉ፡፡ ነገር ግን ከትያትር ጋር ግንኙነት ብኖራቸውም በአጀማመር ታሪካቸዉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ የስነ-ጥበብ ዓይነቶች ከትያትር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

### 4.2.2 ሙዚቃ

ሙዚቃ ማለት ከአርቶች ውስጥአንዱ ሆኖ በድምፅ እና በተለያዩ መሳሪያዎች ስሜታችንን የሚናጸባረቅበት የጥበብ ዓይነት ነው፡፡ አንድ የሙዚቃ አቀናባሪ ወይም አዘጋጅ የሙዚቃ ድረጊቱን የሚያቀርብ ሰዉ በመጠቀም የሙዚቃዉ መልዕክት እንዲተላላፍ ያደርጋል፡፡ አድማጮችም ያዳመጡትን ድምፅ ወደ

ስሜትና ፍልስፍናቸዉ በመቀየር ጭብጡን ይቀበላሉ፡፡ ስለዚህ በድምፅ የተዘጋጅዉ ሙዚቃ መድረክ ላይ ማቅረቡ ከትያትር ጋር ያለዉን ግንኙነት ያሳየናል፡፡

በተጨማሪም ባለፉት የትምህርት ክፍሎች ዉስጥ እንደተማራችሁት፣የሙዚቃ አፈጣጠርን በተመለከተ አንደንድ ምሁራን እንደምሉት በተለይ የሙዚቃ መሣሪያዎች የተፈጠሩት በአከባቢያችን የምንሰማዉን በተፈጥሮያሉ ድምፆችን በማስመሰል ነው፡፡ የሰው ልጆች ያዩትን ሁሉ እያስመሰሉ እንደምሰሩ ይታወቃል፡፡ለዚህም ጥቂት ምሳሌ ብናነሳ፣በሰማይ ላይ የሚበሩ ወፎችንና በባህር ዉስጥ የምወኙትን አሣዎችን በመመልከት፤ በጥናትና ምርምር በማደገፍ፤ አይሮፕላን መስረት እንደቻሉይታወቃል፡፡ እባብን በመመልከት ባቡሪን ሠርተዋል፡፡ ልክ እንደዚያዉ የሙዚቃ መሣሪዎችንም በጥናትና ምርምር ተደግፊዉ በአካባቢ ከሚሰሙት ድምፆች እንደ ሰሩ ግልፅ ነዉ፡፡ በምንሰማቸዉ ማራኪ ድምፆችም እያስመሰሉ ከግጥም ጋር በማቀናጀት እየተጨወቱ ተፈጥሮን ስያደንቁ እንደ ነበረ ታሪክ ያስረዳል፡፡

የወፎችምን ድምፅ እያስመሰሉ በግጥም እና ዜማ እንዴት እንደሚጨወቱ ቀጥሎ ከተሰጠው ምሳሌ ማየት ይቻላል፡፡

ጂላ፣

ጂላዬ.......(2)

ጂሊ፣ብቶ ቱሜ

ጂን ቦና ፣ዱሜ

ዮመነኬ፣ዱፉ

ራች ፣በር ፣ጋፈታ

ያን፣ወል ጋፈታ

ሰዱ፣ ጀቢ፣ ትክሳ

ጃርስ፣ሰንጋ፣ትክሳ

ሎመ፣ነዶ ገቴ፣

ሞርመ ፣ነኩቴ፣ እያላ ይቀጥላል....

## ተግባር 1

በአከባቢያቸዉ የሚሰሙትን ድምፆች ጊዜ ወስዳችዉ በትዕግስት፣

1. ጧት ማንም ሳይንቀሳቀስ
2. ማታ፣ሁሉም ፣ከተረጋጋ፣በኋላ፣ በጸጥታ ያለዉን ድምፅ ከልብ ስሙት !

ሀ. ምን ሰማችሁ?

ለ. ዱሮ ልጆች ሆናችሁ በምትሰሙት ድምፅ እና ፣በአሁኑ፣መካከል ፣ልዩነት ፣አለዉ? ምን?

ሐ. ከዱሮዉ የተለየ፣አሁን ያለ፣ካለ፣ግለጹ፡፡

2. የተፈጥሮ ድምጾች ምን ያህል፣የሰዉ ልጆችን፣እንደምማረኩ ግለጹ፡፡

3. እነኝህን የተፈጥሮ ማራኪ ድምጾችን ፣ምን ያህል ታደንቃለቸዉ?

እንግዲህ ከላይ እንደየነዉ እርግብም ኩኩ፣ ኩኩኩኩ.....እያለች ስትዘምር ሰምተን እናዉቃለን፡፡በአከባቢያችንም ያሉ ትላልቅ ሰዎች ስለ የተለያዩ አራዊት መዝሙሮች የምነግሩን ነገር አላቸዉ፡፡

ለምሳሌ

ኩኩ....ኩኩኩኩ..(2)

ጃርቲን ኤደ ዱቴ

ዲን ኬሬ፣ጉቴ

ኦቴን ፣ተቡሉቃ፣

ሙጫ ፣ሱቡሉቃ

ጉርባን ኤርጋ ዲዴ....እያሉ የድሮ ሰዎች የሙዚቃንድምጾችና፣መሣሪያ፣ፈጥሯል፡፡እነንተም በዚህ መሰረት የድሮ ትላልቅ ሰዎችን ፣ጠይቃችዉ በቡድን ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

የቤት ሥራ

በአከባቢያቸዉ በምገኙ፣ቀላል ነገሮችን ፣በመጠቀም ፣አንድ የምትወዱትን ፣የሙዚቃ መሣሪያ ፣ሠርታቸዉ አሳዩ፡፡

## 4.2.3. ዉዝዋዜ

ዉዝዋዜ ማለት ከሙዚቃ ጋር የሚተገበር ፕርፎርማንስ (ተግባር) ሆኖ በተቀናጀ አካላዊ እንቅስቃሴ በመደገፍ የሙዚቃዉን ጭብጥ ወይም መልዕክት በተዘዋወሪም ሆነ በቀጥታ የምደግፍ ነዉ፡፡ እንዲሁም በትያትር ዉስጥ ዉዝዋዜ ጥልቅ ስፍራ ከመኖሩም አልፈዉ አካለዊ ብቃት እንድጨምር ያደርጋል፡፡ዉዝዋዜ ማለት በድምፅ የምዘፈነዉን ነገር ወደ ትርጉም ያለዉ እንቅስቃሴ መቀየር ነዉ፡፡ስለዚህ የዉዝዋዜ ጥበብ በሙዚቃ ተጅቦ መድረክ ላይ ስቀርብ ዉበት ሰለምኖረዉ የበለጠ ከትያትር ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፡፡

## 4.2.4. ስነ-ጥበብ

የስነ ጥበብ ዓይነቶች ፣ሥዕል፣ስነ-ቅርፅ፣ቀለም ቅብና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን የምያስተምር ጥበብ ነዉ፡፡ብዙዉን ግዜ የጥበብ ሥራ የምያስተለልፈዉ መልዕክት በቀላሉ መገነዘብ አስቸጋሪ ነዉ፡፡ስነ ጥበብን ለመረዳት አስቀድመን የገፀ-ባህርይ ሁኔታ፣መቼትና ጭብጡን ማስተወል ግዴታ ነው፡፡ስነ-ጥበብ በትያትር ጥበብ ዉስጥ መድረክ ላይ የምቀርቡ ትያትሮችን ለማስተማር ጉልህ ሚና ይጨወታሉ፡፡ የመድረክ ገፅታ ለተማልካች እንዲያመች ዉበት የምያኖረዉ የስነ-ጥበብ ስራ ነዉ፡፡ይህም በትያትር ስራ ዉስጥ የገፀ-ባህርያት የዉስጣዊና ዉጫዊ ስሜትን ለማጉላት ይረደናል፡፡ለምሳሌ የገፀ-ባሪያት

ንዴት፣ደስታ፣ሀዘን ፣መከሳተር እና የመሳሰሉትን አጉልተዉ ለማሳየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራል፡፡ እንዲሁም በፊልም ጥበብ ሥራ ዉስጥም የስነ-ጥበብ ሚና ከፍተኛ ናዉ፡፡ይህም ደግሞ በፍልም ዉስጥ የምከናወኑ ክኒዊኖችን ተከትለዉ ከቀረጻ ቦኃላ እና የቀረጻ ግዜ የምከናወኑ ስራዎችን ዉበት ለመጨመር ስነ-ጥበብ ከትያትር ጋር ግንኙነት አሏቸዉ፡፡

ጥበብ በተግባር ስቀርብ በቀላሉ የምናገኘዉ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ትምህርት ለመማር
- የምፈለገዉን መልዕክት ለማስተላለፍ
- ሃሳባችንን ለማግለፅ
- የገቢ ምንጩ ለማግኘት
- ከሰዎች ጋር ተግባቦት ለመፍጠር እና ወዘተ ...ናቸው፡፡

## 4.3 ቅርጻ ቅርጽ፣ የሃዉልትእና የእጅ ስራ ሙያ ምልክቶች መልዕክት

**ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:**

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ፡

- የሃዉልት ምልክቶች የሚያስተላልፉ መልዕክት ታስረዳለላችሁ፡፡
- የሃዉልት ስራ የሚሰራበትን ጥቅም ትነግራላችሁ፡፡

ዉይይት 2

ሃዉልት ለምን ይሰራል ብለህ ታስባለህ? በመወያየት የዉይይት ሃሳባችሁን ለክፍል ግለፁ፡፡

ብዙ ጊዜ የመታሰቢያ ሃዉልት ለታዋቂ ሰዎች እና እንስሳት በህይወት ካለፉ በኋላ የሚሰራ ነው፡፡ በተለይ እዉቅና፣ተወዳጅነት እና ክብር ያላቸዉ ሰዎች በህይወት ሳሉ እና ከሞቱ በኋላ ሊሰራ ይችላል፡ ፡ ሃዉልት የሚያስተላልፈዉ መልዕክቶች ብዙ ቢሆኑም የተወሰኑ ታሪክ፣ዕሴት፣ጀግንነት፣ባሕል እና የመሳሰሉትን ለማስተላለፍ ይረዳል፡፡ የመታሰቢያ ሃዉልት ታሪክን ያስተምራል፡፡ እንዲሁም ያለፈዉ ታሪክ እንዳለ የሚያንፀባርቅ እና የሚያቆይ ነዉ፡፡ ታሪክ ወይም የህብረተሰቡ ክንዉን የተከናወነበት ጊዜ እና ቦታ እንዳለ ለማቆየት እና ለማሳየት ያገለግላል፡፡.

ዉይይት 3

በኦሮሚያ የሚታወቁ ሃዉልቶችን ዘረዝራችዉ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

እንደ ክልላችን ሆነ እንደ ሃገራችን ለጀግኖች የተሰራ የመታሰቢያ ሃዉልቶች ብዙ ናቸዉ፡፡ ከነዚያ ዉስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

### 4.3.1. ጫሊ ሾኖ

ጫሊ ሾኖ በ1796 በያዩ ወረዳ ተወልዶ ያደገ ሲሆን፤ በኢሉ አባ ቦር ከ1842-1874 አከባቢ ስያስተዳደር የነበረ ጫሊ ሾኖ ወይም አባ ቦር ናቸዉ፡፡ በዚህ አከባቢ በጀግንነት ሲታወቅ ነበር፡፡

የኢሉ አባ ቦር ዞን ስያሜ ያገኘዉ፣ የአራቱ ገዳ እና ዘጠኙ እሉ ሲያስተዳደረ የነበረ ሰዉ፣ አባ ጫሊ/አባ ቦር የተባሉ ሰዉ ነበሩ፡፡ ከገዳ ስርዓት ገደብ ዉጪ ያስተዳደረበት ምክኒያት፣ በስልጣን ላይ በነበረበት ዘመን ከብዙ ጠላቶች ጋር ሲዋጋ በጀግንነት ሲመራ ስለነበር በህበረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ስላተረፉ ማስተዳደር እንደቻሉ ይነገራል፡፡.

ያዮ ከተማም የአስተዳደሩ ማዕከል ስለነበረች፣ የንጉስ አባቦር/ ጫሊ ሾኖ ሃዉልት በያዮ ከተማ ህዳር 19 2013 ዓ.ም ወይም ታህሳስ 1 2020 እ.አ.አ ተመረቀ፡፡ የዚህ ታሪክ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነዉ፡፡



ስዕል 4.1. የጫሊ ሾኖ የመታሰቢያ ሃዉልት

ዉይይት 4

ከዚህ በላይ የተመለከታቹትን የመታሰቢያ ሃዉልትና ከጫሊ ሾኖ አጭር ፅሁፍ ምን እንደ ተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል ግለጹ፡፡

## 4.3.2. አብሼ ገርባ

አብሼ ገርባ የአባ ዱላ ኦዳ ቡሉቅ ልጅ ሲሆኑ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ አከባቢ የነበሩ ናቸዉ፡፡ ገርባ ሁሩባ እንደ ገዳ ስርዓት በኦዳ ቡሉቅ ተመርጠዉ፣ እንደ አባ ዱላ ከ1850-1854 ሲያገለግሉ ነበር፡፡ አራት አመት ከአገለገሉ በኋላ፣ ገርባ ህይወታቸዉ አለፈ፡፣ አብሼም ከአባቱ ሞት በዋላ ወደ ስልጣን መጥቶ የጦር መሪ ሆኑ፡፡በሆሮ አከባቢም የጎጃም ወረራ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይመጣ ነበር፡፡ አቢሼ ስዋጋ ስለነበር ከሰዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን አገኘ፡፡.

ከጎጃም የመጡ አብሼን ተዋግተዉ ማሸነፍ ስላቃታቸዉ፣ ለመያዝ ዘዴ ዘየዱ፡፡ ሰላም እንፈልጋለን በማለት፣ መልዕክት ፈረስ ከወርቅ በመስራት ላኩለት፡፡በዚህ ሁኔታ አብሼ ራስ ደረሱን የጎጃም የጦር ኃላፊ ከነበሩ ጋር ተገኛኝተዉ እንዲነጋገሩ አመቻቹ፡፡ በኦሮሞ ህግመሰረት በመማል ከጎጃም የመጡ እና አቢሼ አጠናቀቁ፡፡ ከዚያ በኋላ የጎጃም ሰዎች ሰልፈኞቻቸዉን ደብቀዉ ሆሮ ዉስጥ ስፍራ እንዲይዙ አደረጉ፡፡ አቢሼ ደግሞ በፊት የተስማሙበት ጉዳይ ስላሌ ሰልፈኞቹ

የሰፈሩበት ቦታ ወደ ጎዳ ኮኮር የተሰኘዉ ቦታ ሄዱ፡፡ እዛ ከደረሱ በኋላ፤እንደ ኦሮሞ ባህል መሰረት የታጠቁት መሳሪያ ታጥቀዉ ወደ ዉይይት ቦታ ስለማይገባ፤ ትጥቁን ፈትተዉ ወደ ድንኳን ገቡ፡፡ እሱ እንደ ገባ የተባባሉትን በመካድ፤ በደንብ አሰሩ፡፡አቢሼን እንደያዙ ለሰልፈኞቹ ለማስተዋወቅ ከበሮ መቱ፤ በቅፅበት ከተደበቁበት በመዉጣት፤ አቢሼ ይዛቸዉ ሄዶ የነበረዉን ወታደሮች መዋጋት ጀመሩ፡፡ አቢሼ ክህደት ተፈፅሞበት በመያዙ እሱም ወታደሮቹም ለአንደ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተሸነፉ፡፡

ብዙ የአቢሼ ወታደሮችም ተሰዉ፡፡ የካቲት 13 1877 አቢሼ ወደ ጎጃም በመዉሰድ አሰሩ፡፡ ካሰሩ በኋላ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ገደሉት፡፡

ለዚህ ጀግና መታሰቢያነት በሆሮ ጉዱሩ ዞን ሻምቡ ከተማ በፈረስ ላይ ተቀምጠዉ ጦር ይዘዉ፤ ጀግንነት እና ታሪኩን የሚገልጽ የመታሰቢያ ሃዉልት ተሰርቶላቸዉ፤ ግንቦት 30 2013 ዓ.ም ተመርቋል፡፡ የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል 4.2. የአቢሼ ገርባ የመታሰቢያ ሃዉልት

ዉይይት 5

ከዚህ በላይ ለአያቶች የመታሰቢያ ሃዉልት እና ስለ አቢሼ ገርባ የተጻፈ አጭር ፅሁፍ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍልአቅርቡ፡፡.

## 4.3.3. በከር ዋሬ

በከር ዋሬ የተወለዱ በምስራቅ ሃረርጌ ጃርሶ ወረዳ ነበር፡፡ በከር ዋሬ በኦሮሞ ትግል ታሪክ ዉስጥ በብዙ ነገር ይታወቃሉ፡፡ በተለይ በምስራቅ ኦሮሚያ ዉስጥ የሚኖሩ ኦሮሞዎች፤ በነፍጠኞች ወራሪ ኃይል /የሚኒልክ ወታደሮች/ በጥር 6 1887 በተደረገዉ ጦሪነት፤ የኦሮሞ ጦር መሪ ማን

እንዲሆን ከተወያዩ በኋላ፤ ባካር ዋሬ እንዲመሩ መረጧቸዉ፡፡ ይህ ጀግና ብርቱ፣ጅግንነት፣አዋቂ እና ከፍተኛ የማስተዳደር ችሎታ ነበራቸዉ፡፡

በጫል ጨለንቆ በተካሄደ ጦርነት የተነሳ ጀግናዉ የኦሮሞ ጦር መሪ ባካር ዋሬ በዚሁ በጦርነት እግሩ ተቆረጠ፡፡ እግሩ የት እና እንዴት እንደተቆረጠ የሚታወቅ ነገር ስለሌለ፤ ሃራርጌ አከባቢ ያሉ ሰዎችም እንደ ምሳሌ ሲጠቀሙ ጠፍተዉ ያልተገኘ ነገር ካለ . "እቺ ቡቴ ሚላ ባካር ዋሬ"ትርጉሙም ጠፍተዉ የቀረ የበካር ዋሬ እግር እንደ ማለት ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጦርነት ብዙ ሰዎች አልቀዉ ነበር፡፡ ይህ እልቂት እስከ ዛሬ ጫሊ ጨለንቆ በመባል ይታወቃል፡፡

ለዚህ ጀግና መታሰቢያ የሚሆን ከነ ፈረሳቸዉ የተሰራ የመታሰቢያ ሃዉልት በጨለንቆ ሰማዓታት ዉስጥ መጋቢት 25 2015 እ.አ.አ ተሰርተዉ ተመርቋል፡፡

የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነዉ፡፡



ስዕል 4.3. የበከር ዋሬ የመታሰቢያ ሃዉልት

ወይይት 6

ከዚህ በላይ ያለዉን የመታሰቢያ ሃዉልት እና ከባካር ዋሬ ታሪክ እጭር ፅሁፍ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4.3.4. የአኖሌ ሰመዓታት መታሰቢያ ሃዉልት

የአኖሌ ሃዉልት በምስራቅ አርሲ ሄጦሳ ወረዳ ይገኛል፡፡ የኦሮሞ አርሲ የነፍጠኛን ወረራ በመከላከል፤ በተለይ ከ1881-1886 እ.አ.አ ከፍተኛ ጦሪነት አድርጓል፡፤ ሚኒልክ በተለያየ ጊዜ ለ6ኛ ዙር ወደ አርሲ ሲያዘምት ነበር፡፡ አርሲን መቆጣጠር ባይችልም ከፍተኛ ዋጋ ከፍሏል፡፡ ሚኒልክ በጊዜዉ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ በግዢ እና ከአዉሮፓ በሚያገኝ ድጋፍ የበላይነት ቢኖሮዉም፤ በአርሲ ከአካሄደዉ ጦርነት ከሁሉም አደገኛ እና ደም የፈሰሰበት ነበር፡፡ በፊታቸዉ የተደቀነዉን ኃይል ለመስበር፤ ሚኒልክ የጦር መሳርያ ብቻ አልተጠቀመም ነበር፡፡ ህዝቡን ለማማረር ወንዶችን የቀኝ እጅ እና ሴቶች ደግሞ ጡታቸዉን መቁረጥ እንደ አላማ ይዘዉ ነበር፡፡

ኦሮሞ ያሳለፋቸዉን ታሪክ አዋንተዉ በማስታወስ፤ የዛሬዉን ለማጠናከር በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ የአኖል ሰማዕታት ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ የአኖሌ ሰማዕታት ሃዉልት ዲዛይን እና ስራ የነፍጠኛን ጭቁን ስርዓት በኦሮሞ ላይ የፈፀመዉን ድርጊት እንዴት እንደ ነበረ እና ቦታዉን የሚገልፅ ነዉ፡፡ የዚህ ሃዉልት ስራ ዋና አላማ፤ እንደዚ አይነት አስነዋሪ ድርጊት እንዳይደገም እና የሚቀዋነዉ ትዉልድ እንዲማሪበት ለማድረግ ነዉ፡፡

የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነዉ፡፡



ሰዕል 4.4. የአኖሌ ሰማዕታት መታሰቢያ ሃዉልት

> ዉይይት7
>
> ከዚህ በላይ ያለዉን የመታሰቢያ ሃዉልት እና ከአጭር ፅሁፉ ታሪክ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4.3.5. ብርጋዴር ጀነራል ታደሰ ብሩ

ብርጋደር ጀነራል ተደሰ ብሩ በ1920 በሰሜን ሸዋ ዞን ሰላሌ አከባቢ ተወልደዉ እንዳደጉ ለጀግኖች የተፃፉ ብዙ ፅሁፎች ይመሰክራሉ፡፡ ጣሊያንን የሚዋጉ ሽምግ ተዋጊዎች አባል ነበሩ፡፡ በመጨረሻም በሶማሊያ ሞቃዲሾ እድሜ ልክ ተበይኖበት/ተፈርዶበት ታሰረ፡፡ እንግሊዝ በ1940 ሞቃዲሾን ወርራ ነጻ እስክትወጣ ድረስ እዛ ነበሩ፡፡ ከዛ በኃላ ተፈተዉ በኬንያ የዉትድርና ስልጠና ወሰዱ፡፡ ወደ ሃገራችን በመመለስ በሆሎታ የጦር አሰልጣኝ በመሆን ሲያገለግሉ ነበር፡ ፡ በ1954 ማዕረጉን ከፍ በማድረግ በፈጥኖ ደራሽነት ተሸለሙ፡፡ በዚህ ጊዜ ሲታገል የደቡብ አፍሪካ ፕረዝደንት ነልሰን ማንዴላን አሰለጠኑ፡፡ ሰኔ 1964 ብርጋደር ጀነራል ታደሴ ብሩ የመጫ እና ቱላማ እርዳታ ድርጅት መሪ ሆኑ፡፡ በዚህ ድርጅት እርዳት ኦሮሞዎች እንዲማሩ እና እራሳቸዉን እንዲችሉ ስያስተምሩ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ኃይለ ስላሴ እና ግብርአበሮቹን በጣም አናደዳቸዉ፡፡ ይህ ድርጅት እንዲዘጋ፣ የድርጅቱ አባል የነበሩ እንዲያዙ ሌሎች እንዲገደሉ እና የቀሩት ከሃገር እንዲሰደዱ ተደረገ፡፡

ብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸዉ በኋላ፣ ወደ እድሜ ልክ እስራት ተቀየረላቸዉ፡፡ ሰኔ 1974 ኃይለ ስላሴ ከስልጣን ወርደዉ ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ፣ ብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ በገለምሶ ከታስረበት ሰብረዉ በመዉጣት ወደ ፊንፊኔ ተመለሱ፡፡

የደርግ መንግስትም በፖሊስ ኃይል ቁጥጥር ስር እንዲዉሉ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡ ብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ በመሰወር የጦርነት ንቅናቄ ወታደሮችን በሸዋ ማደራጀት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም እሱን ያዙአቸዉ፣የሞት ፍርድም ተፈረደባቸዉ፡፡ ከብዙ የኦሮሞ አመራሮች ጋር መጋቢት 18 1975 ዓ.ም ተገደሉ፡፡ ቢሞቱም ስለ ማንነት፣ባህል እና አፋን ኦሮሞ በማስተማር ያበረከቱት አስተዋፅኦ ትልቅ ነበር፡፡ ስለዚህ በሰሜን ሸዋ ዞን ፍቼ ከተማ የብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሃዉልት ግንቦት 25 2019 እ.አ.አ ተሰርቶላቸዉ ተመርቋል፡፡.

የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነው፡፡



ስዕል. 4.5. የብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የመታሰቢያ ሃዉልት

ዉይይት 8

ከዚህ በላይ ላያችሁት የመታሰቢያ ሃዉልት እና ከ ብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ የተጻፈ አጭር ፅሁፍ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4.3.6. በላይ ዘለቀ ቅልጡ

የዘር ሃረጉ ከወሎ ኦሮሞ ቦረና የሚባሉ ከኦሮሞ ቱላማ የዘር ግንድ በ1904 ተወለዱ፡፡ በላይ በሽምግ ተዋጊነት ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ዘዴ ጣሊያኖች እና ግብራበሮቻቸዉን እረፍት ሲያሳጣ ነበር፡፡በተለያዩ ጦር ሜዳዎች ጣሊያንን በማሸነፍ ጀግንነቱን አስመስክሯል፡፡ የኦሮሞ ጀግና በላይ ዘለቀ ቅልጡ የጦርነት ስልት ማሸነፍ ያቃታቸዉ ጣሊያኖች ተስፋ ቆረጡ፡፡ የዚህን እና የሌሎች ጀግኖችጥንካሬ እና ጀግንነት ሃገር ለቀዉ ወጡ፡፡

ጣሊያኖች ከተሸነፉ በኋላ ኃይለስላሴ ለአምስት (5 አመት) ሸሽተዉ ከነበረዉ ከእንግሊዝ ሃገር ሲመለሱ፣ እንደ ሌሎች ጀግኖች ወደ ስልጣን ልመጣ ይችላል በምል፣ በላይዘለቀ እንዲያዙ

አደረገ፡፡ ተይዘዉም ወደ ፊንፊኔ ተወሰደዉ እድሜ ልክ ፍርድ ተፈረደባቸዉ፡፡ ነገር ግን እስር ቤቱን ሰብረዉ ወደ ጎጃም ሲመለስ፣ ከመንገድ ተይዘዉ ወደ ፊንፊኔ ከተመለሱ በኋላ፣ በሞት እንዲቀጡ በኃይለስላሴ መንግስት ስርዓት ተፈረደባቸዉ፡፡ ተወልወደዉ በ35 አመታቸዉ ጥር 5 1937 ከሁለት ወንድሞቹ ጋር ተሰቀሉ፡፡ ስለዚህ በምስራቅ ጎጃም ዞን ቢቸና ከተማ የበላይ ዘለቀ የመታሰቢያ ሃዉልት ጥቅምት 10 2009 እ.አ.አ ተሰርቶላቸዉ ተመርቋል፡፡.

የዚህ ሃዉልት ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነዉ፡፡



ስዕል. 4.6. የበላይ ዘለቀ ቅልጡ የመታሰቢያ ሃዉልት

በአጭሩ ከመታሰቢያ ሃዉልት ልንረዳ የሚንችለዉ ነገር፣ እነዚህ ሃዉልት ለምን እንደተሰሩ እና የሚያስተላልፈዉን መልዕክት ነዉ፡፡

ዉይይት 9

ከዚህ በላይ ላያችሁት የመታሰቢያ ሃዉልት እና ስለ በላይ ዘለቀ የተጻፌ አጭር ፅሁፍ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## 4.3.7. ሃጂ አደም ሳዶ

ሃጂ አደም ሳዶ በ1877 በባሌ ዞን ጎባ ወረዳ ተወለዱ፡፡ ከ15 እድሜ ጀምረዉ ባሪነትን እምቢ በማለት ወደ ትግል ተቀላቀሉ፡፡ የሚኒልክ ጦር በሌ በወረሩ ጊዜ፣ የነፍጠኝነት ስርዓት በሃገራችን ተቀባይነት አይኖረዉም በማለት ህዝቦችን ሲያነሳሱ ነበር፡፡ ሃጂ እንደ ሌሎች ታጋዮች በጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ አያምኑም ነበር፣

"ነፃ የሚያወጣን፣የለዉጥ አዕምሮ ነዉ ይላሉ"፡፡ በባሌ የጀመረዉ የትጥቅ ትግል፣ በፊንፊኔም እንዲጠናከር የባሌ አመራሮች እና ታጋዮች እነ ጀነራል ዋቆ ጉቱ እና ጀነራል ሁሴን ቡኔ የፃፉት ደብዳቤ፣ የኦሮሞ ትግል ምስጢር ያለዉ ለብርጋደር ጀነራል ታደሰ ብሩ ለማድረስ ስል ጊዜ በመንግስት ፖሊሶች አባል/

ሰዎች ተይዘዉ ታሰሩ፡፡ በዛም ወደ ፊንፊኔ በመጡ ጊዜ የያዙት ደብዳቤ ምስጢር እዳይወጣ ወደ ሽንት ቤት በመሄድ፣አኝከዉ በመዋጥ ተመልሱ፡፡.

የተፃፈ ደብዳቤ ይህን የትጥቅ ትግል እንዴት አድርገዉ ተጋግዘዉ ከግብ እንዲያደርሱ የሚያሳይ ነበር፡፡ ሽንት ቤት ሄደዉ ሲመለሱ የመንግስት አካል/ የመንግስት ፖሊሶች ይዘዉ፣ ያመጡትን ሰነድ እንዲሰጣቸዉ ጠየቋቸዉ በዛም መፈተሽ ጀመሩ፡፡ ሃጂ ግን ደብዳቤዉን ዉጦት ስለነበሩ"ከሆዳችን የወጣዉን ነገር በሆዳችን መለስን"በማለት ምስጢሩ እዳይወጣ አደረጉ፡፡

ሃጂ አደም ሳዶ የባሌ ህዝብ በኃይለስላሴ ንጉስ ላይ ስያደርግ የነበረዉን ትግል በቀዳሚነት ድርሻዉን ሲወጣ ነበር፡፡ በመጨረሻም የመጫ እና ቱለማ ድርጅት አባል እና በተጨማሪ ኦሮምያ ዉስጥ ባሌና አርሲ መሃል ድልድይ በመሆን ሲያገናኟቸዉ እንደነበር የዚህ ጀግና ታሪክ ያስረዳል፡፡

ከሃጂ አደም ሳዶ የምንማራቸው ነገሮች፡-

- በእዉነት ለኦሮሞ ህዝብ መናገር፡፡ (ሃጂ አደም ለቆሙት እዉነት ለማደናቀፍ፣ ብዙ ጊዜ መሬት፣ገንዘብ እና በተለያዩ ነገር ለማታለል ሞክረዉ አቃታቸዉ)
- ቁርጠኝነት
- ራስን መስጠት
- ለያዙት አላማ መቆም፣ ምስጥር ጣበቂነትና ወዘተ....ነቸዉ ፡፡

ሃጂ አደም በ1981 ህይወታቸዉ ሲያልፍ፣ በትዉልድ ቦታቸዉ ተቀበሩ፡፡ እሳቸዉ ቢቀበሩም ታሪካቸዉ ግን ከዘመን ወደ ዘመን በትዉልድ ይታወሳል፡፡ ስለዚህ በባሌ ዞን ጎባ ከተማ የሃጂ አደም ሳዶ የመታሰቢያ ሃዉልት ተሰርቶላቸዉ ተመርቋል፡፡.

የዚህ ጀግና ታሪክ ፅሁፍ ምንጭ ከቢቢሲ አፋን ኦሮሞ/ BBC Afaan Oromoo የተወሰደ ነዉ፡፡



ስዕል. 4.7. የሃጂ አደም ሳዶ የመታሰቢያ ሃዉልት፡፡

ዉይይት10

ከዚህ በላይ ላለዉ የመታሰቢያ ሃዉልት እና ስለ ሃጂ አደም ሳዶ የተጻፈ አጭር ፅሁፍ ምን እንደተረዳችሁ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የትያትር ጥበብ ከሌሎች ጥበባት ጋር ግንኙነት አለዉ፡፡
- እነዚህ የስነ ጥበባት ዓይነቶች በአቀራረበቸዉ ግን ልዩነት አሏቸዉ፡፡
- ብዙ የስነ-ጥበባት ስራዎች የትያትር ስረዎችን ለማዋብ ከፍተኛ ሚና አላቸዉ፡፡
- የጥበባት ክንዉን ትምህርትን ለማስተላለፍ ይጠቅመናል፡፡
- ዉዝዋዜ ማለት በመደረክ ላይ የምቀርብ ሙዚቃን ለማወብና መስህብነቱ እንዲጨምር ለማድረግ ይረዳል፡፡.
- የሙዚቃና ትያትርግንኙነት የምንፀባረቀዉ ሙዚቃ በመድረክ ላይ ቀርቦ በአካላዊ እንቅስቀሴ ስደገፍ ነው፡፡

## የምዕራፍ አረት መጠቃልያ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች ያሉቲን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እዉነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሀሰት

በማለት መልሱ፡፡

1. የመታሰቢያ ሐዉልት የሚሰራለት ለሰዉ ብቻ ነዉ፡፡
2. የመታሰቢያ ሐዉልት ታርክን ያስተላልፋል፡፡
3. ጫሊ ሾኔ የተዎለዱት በጅማ ከተማ ነዉ፡፡
4. አቢሼ ገርባ የጦር መሪ ሆኖ የተሸሙት በ1855 ነዉ፡፡
5. የአኖሌ የሰመታት ሐዉልት የምገኘዉ በአርሲ ዞን ሂጦሳ ወረዳ ነዉ፡፡
6. ቢ/ ጄኔራል ታደሳ ብሩ ስለ ኦሮሞ ማንነት፣ በህልና ቋንቋ የስተማሩ ነበር፡፡
7. በለይ ዘለቀ የሚታዎቁት በሸምቅ ዉጊያ ነዉ፡፡
8. መታሰቢያ ሐዉልት ለምን እንደ ተሰራና የሚያስተላልፈዉ መልዕክት ማወቅ አይቻልም፡ ፡
9. የትየትር ጥበብ ዓይነቶች በአቀራረባቸዉ ልዩነት የለቸዉም፡፡
10. የትያትር እና ፊልም ጥበብ ከሌሎች ስነ- ጥበባት ጋር ግንኙነት አይኖረዉም፡፡
11. የትያትር ጥበብ ሥራዎች ከስነ-ጥበባት ሥራዎች ጋር ተቀናጅተዉ ብቀርብ የተለየ ድምቀት ልያገኝ ይችላል፡፡
12. ሙዚቃ ማለት በድምፅ ቅንብር ብቻ ሳይሆን በዉዝዋዜ መድረክ ላይ ማቅረብ ይቻላል፡፡
13. ከስነ-ጥበብ ፋይዳ አንዱ መልዕክት ማስተላለፍ መቻሉ ነው፡፡

## ለ. ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከምከተሉት ምርጫዎች ዉስጥ የመታሰቢያ ሐዉልት ጥቅም ያልሆነ የቱ ነዉ?

   ሀ. ያለፈዉን ታርክ ለማስታወስ

   ለ. ወደ ፊት የምመጣዉን ነገር ለመገመት

   ሐ. ታርክን ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ለማስተላለፍ

   መ. መልስ የለም

2.ከዚህ ባታች ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል ሃጂ አደም ሳዶ የሚንማረዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. ለኦሮሞ ነፃነትና ፍትህ መቆም ሐ. ምስጢር ጠባቂነት

   ለ. ቁርጠኝነት መ. ሁሉም

3. ከዚ በታች ስማችሁ ከተጠቀሱት ታጋዎች መካከል ነጻ የምንወጣዉ በትምህርት የደበረ አዕምሮዉ ነወ ያሉት የትኛዉ ነዉ ?

   ሀ. ጄኔራል ታደሰብሩ ለ. ሃጂ አደም ሳዶ ሐ. በላይ ዘለቀ ቂልጡ መ. በከር ዋሬ

4. የተጋይ በላይ ዘለቀ የመታሰቢየ ሐዉልት የቆመበት ------------ከተማ ነዉ

   ሀ. ፊንፊኔ ሐ. በህርዳር

   ለ. አዳማ መ. ቢቾና

5. የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላን ያሰለጠነዉ ኢትዮጵያዊ ማነዉ?

   ሀ. በላይ ዘለቀ ሐ. ሃጂ አደም ሳዶ

   ለ. ጄኔራል ታደሰ ብሩ መ. በከር ዋሬ

6. ከሚከተለዉ አንዱ የስነ-ጥበብ ዓይነት ነው፣

   ሀ. ሙዚቃ ሐ. ፊልም

   ለ. ትያትር መ. ሁሉም

7. አንዱ የስነ-ጥበብ ፋይዳ ነው?

   ሀ.ትምህርት መስጠት ለ. ሃሰብን መግለፅ

   ሐ. መልዕክት ማስተላለፍ መ. ሁሉም

8. ከትያትር ጥበብ ጋር ግንኙነት ያለዉ የትኛዉ ነው?

   ሀ. ፊልም ሐ. ዉዝዋዜ

   ለ. ሙዚቃ መ. ሁሉም

# ምዕራፍ 5
# የስነ-ጥበብት ትስስር

## የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ዉጤቶች:

ከዚህ ትምህርት በኋላ:

- ስነ-ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ጋር ያላቸዉን ትስስር በመለየት ታደንቃላችሁ፡፡
- ስነ-ጥበባት በሌሎች የትምህርት መስኮች ውስጥ ያላቸውን ጥቅም ትለያላችሁ፡፡

### መግቢያ

ስነ-ጥበባት ሌሎች ትምህርትን ለማስተማር ያላቸዉ ድርሻ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ሥነ-ጥበባት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሌላዉን ትምህርት በቀላሉ ለማስተማር እና ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ በአንደኛ ደረጃ እና ቅድመ መደበኛ ክፍል የሚማሩ ካለ ስነ-ጥበባት አይታሰብም፡፡አሳ ከዉኃ ዉስጥ ወጥታ ካለ ዉኃ መኖር እንደማትችል ሁሉ፣ ከስነ-ጥበባት ዉጪ የቅድመ መደበኛ ትምህርትም ሆነ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ማሳካት አይቻልም፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ጥበባት ለአከባቢ ጥበቃ እና በተለያዩ ጉዳዮች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለዉ ድርሻ ሰፊ ነዉ፡፡በአጭሩ በሰዉ ልጅ እለት እለት ኑሮ ምቹ እና ቀላል በማድረግ ስነ-ጥበባት ከፍተኛ ጥቅም እንዳለዉ ተማሪዎች በደንብ ልትረዱ ይገባል፡፡

## 5.1. የስነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች የትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉዳይ ጋር ማስተሳሰር

### ተማሪዎች ቢያንስ መጎናፀፍ የሚገባቸዉ የመማር ብቃት:

በዚህ ትምህርት መጨረሻ :

- ስነ-ጥበባት በሌሎች ትምህርት ዉስጥ ያላቸዉነውን ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡
- ስነ-ጥበባት ከሌሎች የትምህርት መስኮች ጋር ያላቸዉን ትስስር ታስረዳላችሁ፡፡

## 5.1.1. ስነ-ጥበብ (Visual art) ከሌሎች ትምህርት አይነት ጋር ማያያዝ

### ተግባር 1

**ስነ-ጥበብ ሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉን ምን አይነት ድርሻ አለዉ ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ፡፡**

ስነ-ጥበብ በሌሎች ትምህርት ዉስጥ ያለዉ ጥቅም ብዙ እንደሆነ ባለፈዉ ትምህርት ተምራቿል፡፡ ለምሳሌ፡-

- በምልክት እና በስዕል በመጠቀም ማስተማር፣ የመማር ተነሳሽነትን/ፍላጎት ያበለፅጋል፡፡
- ተማሪዎች የትምህርት ይዘቱን በቀላሉ እንዲረዱ ያግዛቿል፡፡
- በቀላል መንገድ ከአከባቢያቸዉ ጋር በመተዋወቅ፣ ፍላጎት እና የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ይረዳቿል፡፡.
- በሌላ ትምህርት የሚማሩ አላማ፣ ከግብ እንዲደርስ እንደ ድልድይ ያገለግላል፡፡.
- የተማሪዎችን ተሳትፎ ይጨምራል፡፡
- ሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ የስነ-ጥበብ ጥቅም ሲንመለከት፣ የተማሪዎች በራስ መተማመን ለማጎለበት እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡- ሂሳብ በመማር ዉስጥ ያለዉ የስነ-ጥበብ ድርሻ በሁለት ይዘቶች አንመልከት፡፡ እነርሱም፡-

☞ ከ1-4 የሚማሩ ይዘቶች

ከ1-4 የሚማሩ የሂሳብ ይዘት እንዱ ሰለ ሂሳብ ስሌቶች እና መሰረታዊ ምልክቶች ናቸዉ፡፡

የሂሳብ ስሌቶች አራት ናቸዉ፡፡ እነርሱም፡-

+, -, × ና ÷

መሰረታዊ ምልክቶች እንደ፡

•, >, ≤ ና ≥


ማየት እንችላለን፡፡ ስሌቶችም ሆነ ይህ ምልክቶች ቅርፅ ናቸዉ፡፡ ቅርፃቸዉ ደግሞ ከመስመር የተሰሩ ናቸዉ፡፡ ቅርፅ እና መስመር ደግሞ የስነ-ጥበብ መሰረታዊ ናቸዉ፡፡

ከ 5ኛ ክፍል በላይ ያሉ ይዘቶችን፡

ከ5ኛ ክፍል በላይ የሚሰጡ ይዘቶችና ሲንመለከት፡-

### ☞ የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች

የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆችየሚባሉ፡-





ስዕል .5.1.የጂኦ ሜትሪ ቅርፃ ቅርፆች ስዕል

እነዚህ ሁሉም ቅርፅ እና ቅርፃ ቅርፅ ናቸዉ፡፡ ቀርፅም ሆነ ቅርፃ ቅርፅ ከስነ-ጥበብ መሰረታዊ ባህሪይ ናቸዉ፡፡

### ☞ ግራፍ/graph

የግራፍመስመር ቅርፅ/ፎርም ይሰራል፡፡በአጭሩ የስነ-ጥበብ ድርሻ ከፍተኛ ነዉ፡፡.




ስዕል. 5.2. የግራፍ ሥዕል

ስነ-ጥበብ ሌሎች ትምህርት ለማስተማር ያለዉ ጥቅም ይህ ብቻአይደለም፡፡ በሌሎች ትምህርት ማስተማር ዉስጥ ይህ የማይባል ድርሻ አለዉ፣ በተጨማሪም እንደምሳሌ የህብረተሰብ ትምህርት አይነት ቢንወስድ፣ የተለያዩ ካርታዎች አለዉ፡፡ ካርታ ደግሞ ስዕል ነዉ፡፡ ሥዕል ደግሞ ከስነ-ጥበብ ስራ ዉስጥ አንዱ ነው፡፡ የስነ-ህይወት (ባዮሎጂ) ትምህርት ቢንወስድ በተለያዩ ሥዕሎች የተደገፈ ነዉ፡፡ በትምህርቱ አይነት የሚንጠቀማቸዉ ሥዕሎች ሁሉም የስነ-ጥበብ ስራዎች ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ የስነ-ጥበብ ትምህርት ሌሎች ትምህርት ማስተማር ለማሳካት ያለዉ ጥቅም ብዙ ነው፡፡

ስነ-ጥበባት ከተለያዩ ትምህርት አይነት ጋር ትስስር አለዉ፡፡ በጤና ላይ የተዘጋጀ የትያትር ስራ፣ ይዘቱ ስለ በሽታ እና የመተላለፊያ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡በመማር እና ማስተማር ላይ የተዘጋጀ ትያትር ስለ ትምህርት ይሆናል፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ስነ-ጥበባት በማንኛዉም ትምህርት አይነት ጋር ትስስር አለዉ፡፡

## .5.1.2. የስነ-ጥባባት ትምህርትን ከሌሎች ትምህርት ዓይቶችና ከወቅታዊ ጉደይ ጋር በመያያዝ መስተመር

ባለፉት ትምህርት ዉስጥ እንደተማራቹት የስነ-ጥበብ ትምህርት ማንኛዉንም የትምህርት ዓይነት ዉስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘወዋሪ ይታያል፡፡ለምሳሌ የሕሳብ ትምህርት ዉስጥ፣የሳይንስ፣የገዳ ስርዓት ዉስጥ ፣ቴክኖሎጂ ፣ሰፖርት፣የቋንቋ ትምህርትእና የመሳሰሉ ዉስጥ ይገኛሉ፡፡

በሁሉም ማስክ ወይም ዘርፍ የስነ-ጥበባት ትምህርት ከሌሎች ትምህርት ጋር ተሳስሯል፡፡በሌላ መንገድ ደግሞ በሕፃናቶች ትምህርት ዉስጥም በተለያዩ ሥዕሎች፣ቅርፃ-ቅርፆች ተጠቅመዉ ህፃናቶች የምማሩበት መንገድ ስነ-ጥበብ ስራዎችን ተጠቅመዉ ነዉ፡፡ስለዚህ ስነ ጥበብ ትምህርት በቀላሉ ሕፃናቶችን ለማስተማር ስለምረዳን ቀጥተኛ ግንኙነት አለዉ፡፡

## 5.1.3 የትያትር ትምህርትን ከተለያዩ ጉዳዮች ጋር ማዛመድ

የትያትርእና ፊልም ጥበብ አዘጋጃጀት ሁኔታ እንዲሁም ለተለያዩ አገልግሎት እንዴት እንደምዉሉ ላፉት ትምህርት ርዕስ ዉስጥ ተረድታቿል፡፡ እንዲሁም በስነ-ጥበብ ትምህርት ዉስጥም ለተለያዩ ርዕሰ ጉዳዎች እንደምዉል ማወቅ አያስቸግርም፡፡

ጥበብ የተለያዩ አገልግሎት ይኖሯል፡፡ለምሳሌ ፓሊቲካን ማስተዋወቅ፣ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊን ለማንፀባረቅ ጉልህ ሚና ይጨወታል፡፡

በፓሊቲካ ማዕዘን ስንመለከት በፍልሙ ታሪክ ዉስጥ በተላይ በሁለተኛ ዓለም ጦሪነት ዉስጥ ፍልም ጥልቅ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡

የተለያዩ ችገሮች ስከሰት ለምሳሌ ተላላፊ በሽታዎች፣ድንገተኛ ባሽታዎች ኤ.ች.አይ.ቪ.፣ ኮቪድ -19፣እና የወባ በሽታ እንዲሁም የትራፊክ አደጋ ስከሰት ስነ-ጥበብን ተጠቅመን የመከላኪያመንገዶች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይቻላል፡፡.በምንም ግዜ ስለ-ስነ ጥበብ ስነሳ በሦስት ትላልቅ ነገሮች ዉስጥ መታየት አለባቸዉ፡፡እነሱም፣

- መዝናናት
- ማስተማር
- የህበረተሰብ ችግርን መፍታት

ሰነ-ጥበብ ለተለያዩ አገልግሎት ብዉሉም ከነዚህ ከላይ በሦስት ነገሮች በተጠቀሱ ዉጭ አገልግሎት ልኖራቸዉ ይችላል፡፡. የማህበረሰብ ችግር ለማፍታት ስነ-ጥበብ ከፍታኛ ሚና አሏቸዉ፡፡

ለምሳሌ ፣ አንድን የማህበረሰብ ችግር ለመፍታት አንድ ድምፃዊ የህበረተሰቡን ችግር በሙዚቃ ምልዕክቱን በማስተላለፍ እንደ መሳሪያ ለጠቀምበት ይችላል፡፡እነዲሁም በትያትርም ሆነ በፍልም ዘዉግ ሕበረተሰባችን ያለበት የማህበረዊዉ እዉነታ የመገለጫ መንገድ የትያትርና ፍልም ጥበብ ነዉ፡፡

## 5.1.4. ስነ-ጥበብ ለኢኮኖሚያዊ ጉደይ

ጥበብ የህገራዊ ኦኮኖሚን ለማሳደግ እንዲሁም ለማበረታት ፣ለዉጥ ለማስገኘት ጉልህ ጠቀሜታ አለዉ፡፡የአንድን ሀገር እድገት በሥዕል ጥበብ፣በሥነ-ቅርፅ ፣በትያትር፣በፍልም እና በሙዚቃ ይገለፃሉ፡፡ለሰዉ ልጅ በአፍህ ከምነገርለት በስነ-ጥብብ የምማረዉ የበለጠ አይምሮዉን የምቀርፀዉና ፈጣኝ ለዉጥ የምያመጠዉ በጥበብ ስማር ነዉ፡፡ስለዚህ ጥበብ ኢኮኖሚን በማሳደግ ረገድ ዉስጥ ትልቅ ድርሻ ከመኖሩም አልፎ የአንድ ሀገር እድገት ማንፀባረቂያ ድልድይ ነዉ፡፡

## 5.1.5. ስነ-ጥበብ በጤና አገልግሎት ጉዳይ

የህበረተስብ ጤናን ለመጠበቅ የጥበብ ሚና ከፍተኛ ድርሻ አለዉ፡፡ ይህ ማለት በጤና በለሙያ የምሰጠዉ አገልግሎት ዉጭ የበለጠ የበሽተኛዉን ጤና ለማንከባከብ ጥበብ የራሱ ሚና እንደምጫወት ይተማነል፡፡ጥብብ የአዕምሮዉ ክልኒክ ሆኖዉ ያገለግላል፡፡ለበሽተኛዉ እረፍት ለመስጠት እፎይታን ይሰጣል፡፡እንዲሁም በሽተኞችን በጥበብ መገልገል ራሱን የቻለ ሳይንስ መሆኑን ስለምያሳይ የጤና ባለሙያዎች በጥበብ በሽተኛዉን ለማንከባከብ ተመራጭ ዘዴ ነዉ፡ ፡በሌላ በኩል ደግሞ የህበረተሰብ ጤናን ለማጠበቅ አልፎዉ ተላላፊ በሽታዎች ላይ ግንዛቤ ለመስጠት ተመራጭ ሳይንስ በመሆን በመዝናናት ህበረተሰብን ስለጤናን በማስተማር ከፍተኛ አስተዋፆ አለዉ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ጥበብበተለያዩጉደዮዎችዉስጥ በተላይ በፓሊቲካ፣ በኢኮኖሚያዊ ነክ ጉዳዮች ዉስጥ፤ የማህበረሰባዊ እና ጤና ዉስጥ ትልቅ አስተዋፆ አለዉ፡፡

- ጥበብን ተጠቅሜን በተግባር በማሳየት የህበረተሰባችን ችግር ማስተማርና የመፍትሔ መንገድ እናሳያለን፡፡
- ሁሉም የጥበብ ዓይነቶችን ተጠቅሜን በሽተኛን ማንከባከብ መፅናናት እንዱሁም መዝናናት እንችላለን፡፡
- ስነ-ጥበብ የህበረተሰባችን የኢኮኖሚን ለማሳደግና ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና ይጨወታል፡፡
- የጥበብ ድርሻ ህበረተሰብን ለማስተማር፣ለመዝናናትና መልዕክትን በማስተላለፍ ማንነትን ያንፀበርቃል፡፡

## የምዕራፉ መልመጃዎች

ለሚከተለዉ ጥያቄ ትክክል ለሆነዉ ዓረፍተ-ነገር 'እዉነት' ትክክል ያል ሆነዉ ደግሞ 'ዉሸት' ብለዉ ይመልሱ

1. ከስነ-ጥበባት የትያትር ጥበብ ከኢኮኖሚ ጋር ግንኙነት የለዉም፡፡
2. የፊልም ጥበብ ተጠቅመን የህበረተሰብ አናናር ማሳየት እንችላለን፣ነገር ግን በእይታ ጥበብ የህበረተሰብ አናናር መግለፅ አንችልም፡፡
3. በጥበብ ታካሚ እንከባከባለን እንዲሁም ህክምና እንዲያገኝ ማድረግ ይቻላል፡፡
4. ስለ ተላላፊ በሽታዎች ጥበብን ተጠቅሜን የመከላኪያ ዘዴንና ግንዛቤን ለመስጠት የበለጠ ይረደናል፡፡